የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

IUSHS



# የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂ









መጋቢት/2009 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂ

መጋቢት/ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ምስጋና.....IV

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት፣የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽንና ሐይጅን ግንባር ቀደም አስፈጻሚ አካላትን በጋራ ለማሰራት የሚያስችል መግባቢያ.....V

የቃላትና ሀረጋት ትርጉም.....VIII

አጠቃሎ.....XIII

1. መግቢያ.....1
   1.1. የነባራዊ ሁኔታ ትንተና.....1
   1.2. የስትራቴጂው መነሻምክንያት.....13
   1.3. የስትራቴጂው የትግበራ ወሰን /Scope/.....13
2. የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂው መርሆዎች.....15
3. ራዕይ.....18
4. ግብ.....18
5. ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች.....19
6. የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂ ይዘቶች.....20
   6.1. የሳኒቴሽንና ሀይጅን በተመለከተ ማስተዋወቅና ኢጋር ማፍራት ፣ የሳኒቴሽንና ሀይጅን ገጽታን ማሳደግ፣የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ሥራዎችን መተግበር፣ የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል.....21
   6.2. የደረቅ ቆሻሻ፣ ዓይነ ምድር ፣ ፍሳሽ ቆሻሻ እና የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አወጋገድ የአገልግሎት አሰጣጥ.....26
      6.2.1. የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ.....26
      6.2.2. የዓይነ-ምድር ዝቃጭ አወጋገድ.....35
      6.2.3. የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ.....37
      6.2.4. የፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ አገልግሎትን ማደራጀትና ውክልና መስጠት.....40
      6.2.5. የፍሳሽ/የጎርፍ መውረጃ.....41
      6.2.6. በውኃ አቅርቦት እና በሳኒቴሽን መካከል ያለ ግንኙነት.....42
   6.3. የተቋማት ሳኒቴሽን.....43

6.3.1. የጤና ተቋማት........44
6.3.2. ትምህርት ቤቶች እና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች........44
6.3.3.የምግብእናመጠጥአገልግሎትመስጫድርጅቶች........45
6.4. የድንገተኛ አደጋ የከተማ ሳኒቴሽን........46
6.5. አቅም ግንባታ........50
6.6. የአዳዲስ ፈጠራዎች ምርምር እና ስርጸት........53
6.7.የሁለገብጉዳዮችስትራቴጂ........55
6.7.1. ፍትሐዊነት........55
6.7.2. ስርዓተ- ጾታ........57
6.7.3. አካባቢ........58
6.7.4. ጤና እና ደህንነት........60
6.7.5. የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ........60
6.7.6. የማኅበረሰብ ተሳትፎ እና ባለቤትነት........62
6.7.7 ዘላቂነት........64
6.8. ፋይናንስ ለሳኒቴሽን እና የታሪፍ ትመና........66
6.8.1. ፋይናንስ ለሳኒቴሽን........66
6.8.2. ለከተማ ሳኒቴሽን ታሪፍ ትመና........70
6.9. የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂን ለመፈፀም የሚያስፈልጉ ተቋማዊ አደረጃጀቶች........71
6.10 የደንብአፈጻጸምናተግባራዊነት........90
6.11 ግምገማና ምዘና........91
7.ማጣቀሻዎች........94

# ምስጋና

የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ውኃ፣መስኖ እና ኤሌክትክ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል የከተማና ቤቶች ልማት ሚኒስቴር፣ የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ፣ ደን ልማት እና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴርእንዲሁም የፌዴራል ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ይህን ስትራቴጂ በማዘጋጀቱ ሂደት ላይ ለተሳተፉ ልዩ ልዩ ተቋማት እና ባለሙያዎች ላደረጉት አስተዋጾ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ፡፡

ይህ የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂበልዩ ልዩ ተቋማት እና ባለሙያዎች ጥረት እውን ሆኗል፡፡ ለዚህስትራቴጂ እዚህ ደረጃ መድረስበዋናነት ምስጋና የሚገባቸው ቁልፍ ተቋማትም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የከተማና ቤቶች ልማት ሚኒስቴር፣ የውሀ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ ደን ልማት እና አየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር፣ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ የውኃአቅርቦትምርምር ተቋም፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሐኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ናቸው፡፡

ይህ ስትራቴጂክ ሰነድ እንዲዘጋጅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚመሩት የከተማ ሳኒቴሽን ግብረ ኃይሎች በእጅጉ ሊመሰገኑ ይገባል፡፡ ከአባላቱ መካከል በተለይም፣ ቴክኒካዊና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ይህ የስትራቴጂ ሰነድ ይዘጋጅ ዘንድ ዓለም-አቀፍ እንዲሁም ሀገር-አቀፍ አማካሪዎችን በመቅጠር እና ሂደቱን በመከታተል ዲ.ኤፍ.አይ.ዲ እና ዩኒሴፍ ኢትዮጵያ ፣ በዓለም ባንክየውኃና ሳኒቴሽን ፕሮግራም፣ የዓለም ጤና ድርጅት፣ ወተር ኤይድ ኢትዮጵያ፣ ጂ.ኤስ.አይ እንዲሁም ፒ.ኤስ.አይ ከፍተኛ ሚና ስለነበራቸው ላደረጉት ድጋፍ ከፍተኛ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በተጨማሪም፣ “በወተር ኤንድ ሳኒቴሽን ፎር ዘ አርባን ፑር” የሚመራው የባለሙያዎች ጊዜያዊ ጥምረት ይህንን ስትራቴጂ በማዘጋጀት ሂደት ላይ ስላበረከተው አስተዋጾ ምስጋና ይገባዋል፡፡

# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት፣የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽንና ሐይጅን ግንባር ቀደም አስፈጻሚ አካላትን በጋራ ለማሰራት የሚያስችል መግባቢያ

በአገሪቱ ህገ መንግስት የተደነገገ የመኖሪያ አካባቢን ከመንከባከብና በንጽህና ከመጠበቅ ጋር በተያያዘ እያንዳንዱ የህብረተሰብ አባል ያለበትን ግዴታና የመንግስትን ኃላፊነት በመለየት ለትግበራው ያለውን ተነሳሽነት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣

የጤና፣ የከተማ ልማት፣ የውሃ ሀብት፣ የአካባቢ ጥበቃና የቱሪዝም ፖሊሲሰዎችና ስትራቴጂዎች የከተማ ሳኒቴሽን፣ ሐይጅን እና ተያያዥ ጉዳዮችን ለመፍታት ያላቸውን ፍላጎት መነሻ በማድረግ፣

በመንግስት ተቀባይነት ያገኙ ዓለም አቀፋዊና አሁጉራዊ እንቅስቃሴዎችንና ግቦችን ለማስፈጸም ያሉትን ጥረቶች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣

መንግሥት እየተተገበረ ያለውን አረንጓዴ የኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂን እውን በማድረግ እ.ኤ.አ. በ2025 አገሪቱን በዝቅተኛው የመካከለኛ ገቢ ያላቸው አገራት ተርታ እንድትደርስ ለማድረግ ያለውን ራዕይ ታሳቢ በማድረግ፣

የከተማው ነዋሪ ህብረተሰብ ዘመናዊነት የተላበሰ አገልግሎት የማግኘት እና የዘመነ የአኗኗር ዘይቤ ፍላጎት፣እንዲሁም በቀጣይ እየዳበረ እንዲሄድ የማድረግ አስፈላጊነትን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣

እያንዳንዱ ዘርፍ (ሴክተር) ያለውን የሥራ ድርሻ በተናጠልና በወል ለመወጣት ሲያደርግ የነበረውን እንቅስቃሴ ታሳቢ በማድረግ፣ ንጽህናው ያልተጠበቀና የተበከለ ከተማ በኢኮኖሚ እና በህብረተሰብ ጤንነት ላይ ያለውን ተፅእኖ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ሁላችንም በጋራና በየሥራ ዘርፉ የከተማን የሳኒቴሽንና ሐይጅን ችግር ለመፍታት በወል የመስራቱን ጠቀሜታ እንዲሁም ነዋሪዎችንም በተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን ሐይጅን ስትራቴጂና የማስፈጸሚያ ዕቅድ ለማስፈጸም በሚያስችል መልኩ ለማንቀሳቀስ ወሳኝ በመሆኑ እና በእያንዳዱ የከተማ አስተዳደር ደረጃ ላይ የሚገኙ አካላት ድጋፍ፣ ክትትል፣ግምገማና አስፈላጊ የሆኑ የቴክኒክና የፋይናንስ ፍሰት፣ ማቀናጀትና ማደራጀት አሰፈላጊነት ግምት ውስጥ በማስገባት የሚከተሉትን ቁልፍ ስልቶች አተገባባር በጋራ ለመስራትና ወደ ክልልሎችም ድጋፍ ለማውረድ ተስማመተናል፡፡

1. ሥራ ላይ ያሉትን ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ እና መመሪያዎች መነሻ በማድረግ በአጭር ጊዜ የተሳለጠ አሰራረርን በማስፈን እና በማስተባበር በረዥም ጊዜ የከተማ ሳኒቴሽን ሥራ ሊመራ የሚችልና ቀልጣፋና ወጪን ቆጣቢ በሆነ መልኩ አግልግሎት ሊሰጥ የሚችል ተቋም መፍጠር፤

2. የከተማን ሳኒቴሽንና ሐይጅን አስመልክቶ እያንዳንዱ ተቋም (የስራ ዘርፍ) የሚያቀርበውን አገልግሎት የተመለከቱ መረጃዎችን በወል የተቀመጡ አመላካቾችን መነሻ በማድረግ የመረጃ አያያዝ ሥርዓትና ዳታ ባንክ ለዕቅድ ዝግጅት፣ ግምገማና ክትትል በሚያመች መልኩ የማደራጀት እና የመለወጥ፣

3. የህብረተሰቡን ተሳትፎ የሚያጎለብቱ ለሁሉም ተደራሽ የሆኑ፣ የተሻሻሉና ዘላቂነት ያላቸው አገልግሎቶችን፣ እንዲሁም የመገልገልን ፍላጎት ሊያጎለብቱ የሚያስችሉ ስርዓቶችን የመመስረት፣

4. ከገጽታ ግንባታ፣ ከጤንነት፣ ከአካባቢ ለውጥ ኢኮኖሚ እድገትና ክብር አንጻር ያለውን አስተዋጽኦ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በልማት ዕቅዶች ውስጥ የጎላ ስፍራ እንዲይዝ ማድረግ፣

5. የግል ዘርፍን ማለትም የልማት ድርጅቶችን፣ ከሥራ ፈጠራ ጋር በማያያዝም የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን ወደ ዘርፉ እንዲገቡ ማበረታታትና ማንቀሳቀስ፣

ከላይ የተመለከቱትን ዋና ዋና ጉዳዮችና የተቀናጀ የከተማ የሳኒቴሽንና ሐይጅን ስትራቴጂ እና አገር አቀፍ የሐይጅን እና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ እስትራቴጂዎችን በጋራ ለመፈፀም መጋቢት 25 /2009 ዓ.ም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የሚንስቴር መስሪያ ቤት ሀላፊዎች በሒልተን ሆቴል በመገኘት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል፡፡

(1) የተከበሩ ዶ/ር ከበደ ወርቁ

የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ዴኤታ

(2) የተከበሩ አቶ ደምሴ ሽቶ

የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስትር ዴኤታ

③ የተከበሩ ወ/ሮ ፍሬነሽ መኩሪያ
የዉሀ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስትር ዴኤታ

④ የተከበሩ አቶ ቃሬ ጫዊቻ
የአካባቢ የደንና አየር ንብረት ለዉጥ ሚኒስትር ዴኤታ

⑤ የተከበሩ አቶ አድማሱ ነበበ
የፋይናንስና ኢኮኖሚ ትብብር ሚንስትር ዴኤታ

⑥ የተከበሩ ወ/ሮ መዓዛ ገብረ መድህን
የባህልና ቱሪዝም ሚንስትር ዴኤታ

⑦ የተከበሩ ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ
የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ

# የቃላትና ሀረጋት ትርጉም

| | |
|---|---|
| ማስተዋወቅ(Advocacy) | የተዘጋጁ ስትራቴጂዎች፣ አካሄዶችና ተግባራት በማስተዋወቅ የንጹህ መጠጥ ውኃ እና የተሻሻሉ የፅዳት አገልግሎቶች አቅርቦት እንዲሁም ከንፅህና ጋር የተያያዙ ተግባራት ይበልጥ እንዲዳብሩ የሚያግዙ የሚመለከታቸው አካላት ምቹ ፖሊሲዎች እንዲቀርፁ፣ ሀብት እንዲያሰባስቡና ምቹ ሁኔታ እንዲፈጥሩ ማድረግ |
| የባህሪ ለውጥ የሚያስከትል ተግባቦት (Behavioural Change Communication | ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተስማሚ የሆኑ አዎንታዊ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ልምዶችን ለግለሰቦች እና ለማኀበረሰብ ለማስተዋወቅ እና ዘላቂ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ የሚያስችል የተግባቦት ሂደት፡፡ |
| መሠረታዊ ሳኒቴሽን (Basic Sanitation) | እጅግ ተመጣጣኝ የሆነ ዋጋ በመክፈል በዘላቂነት ሊጠቀሙት የሚቻል፣ ደህንነቱ የሚያስተማምን፣ ጤናማ እና ምቹ የሳኒቴሽን አገልግሎት እና አቅርቦት በማግኘት ግላዊ ምቾትን እና ሰብዓዊ ክብርን በማይነካ መልኩ ዓይነ ምድርን ለማስወገድ የሚያስችል አማራጭ ሲሆን፣ በተመሳሳይ የመኖሪያ ቤትና አጎራባች አካባቢ ንጹህ እና ጤናማ እንዲሆኑ ያስችላል፡፡ |
| ማኀበረሰብን ያማከለ አካሄድ(Community-based Approach) | ማህበረሰቡ ቅድሚያ የሚሰጣቸዉን ጉዳዮች ለመለየትና ፣ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማፍለቅ፣ ሀብት ለማፈላለግ፣ የታቀዱ ስራዎችን ለመተግበር፣ የስራዎችን ሂደት ለመገምገምና የተገኙ ዉጤቶችን ለማስፋት ማህበረሰቡን በራሱ ጉዳይ ተሳታፊ በማድረግ ማህበረሰቡ የራሱን ልማት የሚመራበት አካኤድ ነዉ፡፡ |

| | |
|---|---|
| የጋራ መጸዳጃ ቤት | ከአንድ ቤተሰብ በላይ የሆኑ የቤተሰብ አካላት በጋራ የሚጠቀሙበት መጸዳጃ ቤት ሲሆን ንጽህናውን የመጠበቅ፣ ሲሞላ የማስመጠጥ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ጥገናዎችን የማድረግ ሃላፊነት ተጠቃሚ ቤተሰቦች በጋራ የሚወስዱበት የጋራ መጠቀሚያ ነው፡፡ |
| ከመኖሪያ ቤቶች የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ | በመኖሪያ አካባቢዎች ከማዕድ ቤት፣ ከመታጠቢያ ቤት፣ ከመጸዳጃ ቤት እንዲሁም ከልብስ እጣቢ የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ |
| አስቻይ ሁኔታ (Enabling Environment) | ምቹ ነባራዊ ሁኔታ ፖለቲካዊ፣ ተቋማዊ፣ ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ አካባቢያዊ እንዲሁም ሌሎች ፍላጎቶችን ጨምሮ አንድን ግብ፣ ዓላማ ወይም ተግባር ለመከወን የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ሁኔታዎች ድምር ነው፡፡ |
| ፍሳሽ ቆሻሻ (Grey water) | ከዕቃ ፣ ማጠቢያ ፤ ከመታጠቢያ ቤቶች፣ መታጠቢያ ገንዳዎች፣ የልብስ ማጠቢያ ማሽኖች እንዲሁም የልብስ ማጠቢያ ሳህኖች የሚወጣፍሳሽ ቆሻሻ ነው፡፡ ይህ ቆሻሻ ከመጸዳጃ ቤት የሚወጣውን ፍሳሽ አይጨምርም፡፡ |
| የአንድ ቤተሰብ/የግል መጸዳጃ | የአንድ ቤተሰብ አባላት ብቻ የሚጠቀሙበትመጸዳጃ ቤት፡፡ |
| ሀይጅን | ከውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ከግል ንጸህና ጉድለት ጋር የተያያዙ በሽታዎችን ስርጭት በመግታት ጤናንለመጠበቅ የሚያስችሉ አዎንታዊ ተግባራት ወይም ባህሪያት ድምር ነው፡፡ |
| ሀይጅንን ማስተዋወቅ | ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በግል እና በማኅበራዊ ጤናቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያመጡ ጉዳዮችን በተሻለ ሁኔታ እንዲያውቁ፣ እንዲገነዘቡና እንዲቆጣጠሩ የሚያስችል ሂደት ነው፡፡ |

| | |
|---|---|
| የተሻሻለ መጸዳጃ ቤት | የተሻሻለ ሳኒቴሽን የተሻሻሉና በሚገባ አየር የሚያገኙ የተሻሻሉ መጸዳጃ ቤቶችን፣ የውኃ መድፊያ የተዘጋጀላቸውን መጸዳጃ ቤቶች ይጨምራል፡፡ ሽታ አልባ የሆነና ለዝንቦች፣ ሌሎች እንስሳትና ለአካባቢ ብክለት መንስኤ ያልሆነ እንዲሁም የተጠቃሚውን ክብርና ገመናን የሚሸፍን ደህንነቱ የተጠበቀና ለማፅዳት ምቹ የሆነ መጸዳጃ ቤት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ መጸዳጃ ቤት ዓይነ ምድርን ወደ ማዳበሪያነት የሚለውጡ መጸዳጃ ቤቶችን (ኢኮ-ሳን)እንዲሁም ከሕዝብ ፍሳሽ ማስወገጃና የዓይነ ምድር ማከማቻ ጉድጓዶች ወይም ፍሳሽ ቆሻሻ ማከማቻ ጉድጓዶች ጋር የተያያዙ ውሀን በዕቃ በመድፋት ወይም ሙሉ በሙሉ ቆሻሻን ጠርጎ በሚያስወግድ/water flush/ ዘዴ የሚሰሩትን ያጠቃልላል፡፡ |
| ከኢንደስትሪ የሚወጣ ፍሳሽቆሻሻ | በማምረት እና በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ ከኢንደስትሪዎች/ ፋብሪካዎች የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ልዩ ልዩ ለጤና ጠንቅ የሆኑ ኬሚካሎችን ይይዛል፡፡ |
| የተቋማት መጸዳጃ ቤት | የትምህርት ቤቶች፣ የጤና ተቋማት፣ የማረሚያ ቤቶች፣የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ የንግድ ተቋማት፣ወዘተ.የሚገኝ መጸዳጃ ቤትን ይመለከታል፡፡ |
| የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር | ደረቅ ቆሻሻ ከምንጩ ጀምሮ እስከ መልሰ መጠቀምና ማስወገድ ያለውን ረጅምና ተከታታይ የሆነ ሂደት ሲሆን ይህም ከህዝቡ ጤናና አካባቢያዊ ስነ ምህዳር ጋር የተስማማ አዋጪ የሆነ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ስርአት አስተዳደር ነው፡፡ |

| | |
|---|---|
| ሜዳ ላይ መጸዳዳት | ቦታ ሳይመርጡ በተገኘበት (ሜዳ ላይ፣ ቁጥቋጦ/ጫካ ውስጥ፣ ወንዝ ዳር ወይም በየትኛውም መጸዳጃ ቤት ባልሆነ ስፍራ  መጸዳዳት እና ዓይነ ምድርን አጋልጦ መተው ነው:: |
| ከዓይነምድር የጸዳ አካባቢ | ዓይነምድር የማይታይበትአካባቢ ማለት ነዉ ። ይህም ማለት ሁሉም የማህበረሰብ አባል ሁልጊዜ በመጸዳጃ ቤት ብቻ የመጠቀም ልማድ ሲያዳብርና በማንኛውም መልኩ ሜዳ ላይ  የመፀዳዳት ልማዱን ሲያቆም የሚመጣ ነዉ:: |
| የሕዝብ መጸዳጃ ቤት | ለማንኛዉም  የህብረተሰብ  ክፍል  አገልግሎት ለመስጠት የተዘጋጀ መጸዳጃ ቤት ማለት ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ሊገለገሉባቸው የሚፈልጉ ሰዎች ክፍያ መክፈል ይጠበቅባቸዋል:: የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶች ውሀ፣ የእጅ መታጠቢያ ቁሳቁሶች፣ ብርሀን፣ በተለያየ አካላዊ ሁኔታ ላሉ ሰዎች ተደራሽ እንዲሆን ተደርጎ የሚሰራና በእድሜ፣ጾታ፣  የሃብት ደረጃ ምክንያት  የተነሳ ተጠቃሚዎች አንዳችም መድልዎ ሳይደርስባቸው  እንዲገለገሉበት ተደርጎ የሚሰራ መጸዳጃ ቤት ነው:: |
| ወራጅ ውኃ/የጎርፍ ውኃ | የዘነበ በረዶ ሲቀልጥ ወይም ዝናብ ከዘነበ በኋላ ወደ ፍሳሽ ማስተላለፊያ ቱቦዎች፣ ጉድጓዶች እና ወንዞች የሚገባ ውኃ ነው:: |
| ሳኒቴሽን | ሳኒቴሽን ሰዎች ከሰው በሚወጣ ዓይነ ምድር ንክኪ አማካኝነት የሚመጡ  የጤና ጠንቆችን ለመከላከል፣ ደረቅ እና ፍሳሽ (ፍሳሽ ወይም የቆሸሸ ውኃ) ቆሻሻዎችን በማከምና በተገቢው መልኩ በማስወገድ ለራሳቸው ንጹህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖራቸው የሚያደርጉበት ፍቱን የጤና አጠባበቅ ዘዴነው:: |

| | |
|---|---|
| ባለ ድርሻ አካላት | ተለይተው የወጡ ትግበራዎች አዉንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳርፉባቸው ተቋማት፣ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ሲሆኑእነዚህ ትግበራዎች የሚዘጋጁበትን ወይም የሚከናወኑበትን መንገድ በመወሰኑ እና በመተግበሩ ሂደት ላይ ድርሻ ሊኖራቸው የሚችሉ ናቸው፡፡ |
| አጠቃላይ ሳኒቴሽን | በሜዳ ላይ መጸዳዳት ሙሉ በሙሉ የሚነቀፍበት፣ ተገቢ የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ በዘላቂነት የሚከወንበት እና የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች የነዋሪዎችን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊና የጤና ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ በአግባቡ ጥቅም ላይ የሚውሉበት ሁኔታ ያመላክታል፡፡ |
| የከተማ ሳኒቴሽን | ከኢንደስትሪዎች/ፋብሪካዎች የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ፣ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጠቃላይ ሳኒቴሽንን የሚያካትት ሲሆንየሰዎች ጤና እንዳይታወክ የሚያደርጉና በአካባቢ ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ መንገዶችን በመጠቀም ዓይነ ምድርን መሰብሰብ፣ ማከማቸት/ማከም፣ ማጓጓዝ፣ መልሶ መጠቀም ወይም ማስወገድን ያጠቃልላል፡፡ |

# አጠቃሎ

የኢትዮጵያ ከተሞች ዕድገት ፍጥነት፣ መጠንና ጥልቀት በፅዳት አሰራር ላይ ስርነቀል የሆነ ለውጥ የሚጠይቅነው፡፡ የአዳዲስ አቅጣጫዎች እና አሰራሮች እንዲሁም ማስፈጸሚያ የሚውለው መዋዕለ ነዋይ ስኬታማነት የሚለካው ለኢትዮጵያ ከተሞች ነዋሪዎች መኖሪያ ቤትና የስራ ቦታ ጽዱ እና የተዋቡ ስፍራዎች በመፍጠር እንዲሁም አቅምን ባገናዘበ ክፍያ በቂና የተሻሻሉ አገልግሎቶችን በማቅረብ ብቃታቸው ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ሀገራችን የከተማ ሳኒቴሽን መሻሻልን ለማሳካት ስትከተል የቆየችውን አካሄድ በከፍተኛ ሁኔታ ማሻሻልንይጠይቃል፡፡

ይህ ስትራቴጂ፣ በከተሞች አካባቢ ያለው የሳኒቴሽን መሻሻል የገጠሩን አካባቢ የሳኒቴሽን ፍላጎት ለማሟላት ካስቻሉ አካሄዶች ያለፈ ሊሆን እንደሚገባ በግልጽ ያሳያል፡፡ የፅዳትና ንጽህና ላይ ግንዛቤ መፍጠር፣ ማበልጸግና ማስፋፋት፣ በማህበረሰቡ ዘላቂ የባህሪ ለውጥ ማምጣት እና ቤተሰቦች በመጸዳጃ ቤት አገልግሎቶች የሚጠየቀውን ወጪ አውጥተው በአግባቡመጠቀምአስፈላጊ ነው፡ ፡በተቀናጀ አገልግሎት ሰንሰለት የእያንዳንዱን ቤት ፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻዎች ተገቢ በሆነ ሁኔታ መያዝና ማስወገድሲቻልም መልሶ መጠቀም ከሚያስችሉ ውጤታማ የአሰራር ሂደቶች ጋር ማቀናጀት ያስፈልጋል፡፡

ስለሆነም በርካታ የቆሻሻ አሰባሰብ አማራጮች፣ ለተለያዩ ቦታዎችና ነባራዊ ሁኔታዎች በሚያመች የማጓጓዝና የማከም አካሄድ እንዲሁም ቆሻሻዎች ለጤና ወይም ለአካባቢ ደህንነት ጠንቅ በማይሆኑበት ሁኔታ ማስወገድ ወይም መልሶ መጠቀምን ያካተተ አጠቃላይ የአገልግሎት ሰንሰለት ተፈጻሚ ይሆን ዘንድተደራሽ በሆኑ አካባቢያዊ ማዕከላት ደረጃ የሚከወን መዋቅራዊ አካሄድ አስፈላጊ ነው፡፡

ስትራቴጂው በተጨማሪም በሳኒቴሽን መሻሻል ላይ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣የግሉ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎን ማሳደግ እንዲሁም በመንግሥት መዋቅር ውስጥ እና ከዚያም ውጪ የሥራ ፈጠራ ሁኔታዎችን ባካታተ መልኩ የተቀናጀ መሆን እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ ይህንን አካሄድ አስፍቶ በማከናወኑ ሂደት ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት ጥራት ያለው መሆኑን ለመቆጣጠር፣ ለማረጋገጥ እናየግሉን ዘርፍ ከፍተኛ ተሳትፎ እውን ለማድረግ ደንብን የተከተለ አሠራር ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ሲሆንየሕብረተሰቡን ጤና እና አካባቢያዊ ደህንነትን በተገቢው ሁኔታ ለማረጋገጥበቅንጅት መሥራት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡

የተሻሻለ የውሀ አቅርቦት፣ የፍሳሽና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ እንዲሁም ግንዛቤ ማስጨበጥና የባህሪ ለውጥ እርስ በርስ ተደጋጋፊ ናቸው፡፡ ስለዚህ የተፈለገውን ውጤት ለማግኘትበዕቅድ አዘገጃጀት፣ በአቅርቦቶች አያያዝ እንዲሁም በጀት አጠቃቀም አኳያ የተሻለ ውሳኔ ለማሳለፍ የተቀናጀ አሠራር አስፈላጊ ነው፡፡ የፌደራል እና ክልል እገዛ አስፈላጊ ቢሆንም የከተማ ሳኒቴሽን መሻሻል የሚነሳው እና የሚጀምረው ከከተማና ከከተማ ማዕከላት ሊሆን ይገባል፡፡ ይህንንም ለማድረግ እና ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን ለምሳሌ ስርዓተ-ጾታ እና ፍትሀዊነት የተመለከቱ ጉዳዮችን እና አዳዲስ የሥራ ዘይቤዎችን ለመቀየስ የአመራር አካላት ድጋፍ ውጤታማ ባለሙያዎች እና ጠንካራ አስተዳደር ያስፈልጋሉ፡፡የተመዘገበውን መሻሻል ለመከታተል እንዲሁም ዕቅዶችንና የዘርፉን ኢንቨስትመንት ለመደገፍ ጠንካራ የክትትልና የግምገማና ምዘና የአሠራር ስርዐት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

# 1. መግቢያ

ይህ የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂ ከአጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ ትንተና በኋላ የተዘጋጀ ሲሆን ስልታዊ የትግበራ ስትራቴጂም ጎን ለጎን ተዘጋጅቷል፡፡ የተጠቀሱት ሁለቱም ሰነዶች በተናጠል የተዘጋጁ ሲሆንየነባራዊ ሁኔታ ትንተና ሰነዱ በጥልቅ የሰነዶች ምርምር፣ ከከተማ ሳኒቴሽን ግብረ ኃይል ጋር በተካሄደ ምክክር እንዲሁም ከህዳር-ታህሳስ 2007 በስድስት የኢትዮጵያ ክልሎች በሚገኙ 11 ከተሞች በተካሄደ ቅኝት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

የስልታዊ ትግበራ ስትራቴጂ ሰነዱ የተዘጋጀው በስትራቴጂው ላይ በጸደቁ መርሆች እና ቁልፍና መሠረታዊ ክፍሎች ላይ ተመስርቶ እና በኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ የሳኒቴሽን እና የሀይጅን ዘርፍ እድገት እውን እንዲሆን ዝርዝር የትግበራ የጊዜ ሰሌዳን ከተቋማዊ፣ ገንዘብ ነክ፣ ከቁጥጥር፣ ከማስተዋወቅ፣ ከቴክኖሎጂ እና ከአሠራር አማራጮች ጋር መተንተንን ዓላማው በማድረግ ነው፡፡

## 1.1. የነባራዊ ሁኔታ ትንተና

ነባራዊ ሁኔታው የተተነተነው ጥናታዊ ሰነዶችን በመፈተሽ፣በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ከሚገኙ ባለ ድርሻ አካላት ጋር ምክክር በማካሄድእንዲሁም በሀገሪቱ ስድስት ክልሎች ውስጥ በሚገኙ 11 ከተሞች (ጎንደር፣ ባህር ዳር፣ ማክሰኝት፣ መቀሌ፣ ውቅሮ፣ ሀዋሳ፣ አላባ፣ ገዋኔ፣አዳማ፣ ቢሾፍቱ እና አዲስ አበባ) ላይ በተከናወነ ቅኝት አማካኝነት ነው፡፡ይህ የነባራዊ ሁኔታ ትንተና በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የከተማ ሳኒቴሽን አገልግሎት ሁኔታ ከሞላ ጎደል የሚያሳይ ሲሆንአፋጣኝ የሆኑትን ፍላጎቶች ለማሟላትና እጅግ ተጋላጭ ከሆኑ ተጠቃሚዎች አንስቶ በከተሜው መካከል በሥራ አሻራቸውን ለማስፈር እስከሚሹ የኢንደስትሪና የንግድ ዘርፍ ተሳታፊዎች ድረስ ሁሉን ያማከለ ተአማኒና ዘላቂነት ያለው የትግበራ ዕቅድ ለመንደፍ እንዲያስችል በጥልቀት የተቃኘ ነው፡፡

## የኢትዮጵያ የከተማ ሳኒቴሽን አጠቃላይ ምልከታ

በኢትዮጵያ መንግሥት በሁለተኛው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (2008-2012) አማካኝነትዘላቂ የልማት ግቦችን ባገናዘበ መልኩሀገሪቱ በግብርናው ዘርፍ ከሚመራ በገጠሩ ብቻ ላይ የተመሠረተ ምጣኔ ሀብት ወደ ኢንዱስትሪ መር የሆነና በከተማ ላይ የተመሠረተ ምጣኔ ሀብት ጭምርእንድትሸጋገር ታቅዷል፡፡ ከዚህ የእድገት ጎዳና ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ መንግሥት ሀገሪቱ

በ 2017/18 ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ እንድትሰለፍ የረዥም ጊዜ የልማት አጀንዳ ይዟል፡፡ ይህንን ግብ ማሳካትም በኢትዮጵያ ከተሞች እና የከተማ ማዕከላት ለንግድ ሥራ ተወዳዳሪነት የመጋበዝ ክህሎቶች እንዲዳብሩ የሚያስችል አምራችነት እና በነዋሪዎቻቸው የሚፈለገውን ዓይነት ለኑሮ ምቹ የመሆን አቅም ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ተገቢው የከተማ የኑሮ ደረጃ ላይ እንዲደረስ ለማስቻል ደግሞ የተሟላ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን አገልግሎት ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡

ከዚህ አንፃር የሳኒቴሽን አገልግሎትን ማቅረብ እና በገንዘብ መደገፍ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ከመጸዳጃ ቤቶች እስከ ተለያዩ የቆሻሻ ማስወገጃ አገልግሎት፣ ከደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ እስከ መልሶ መጠቀም፣ ቆሻሻ ቅነሳና ዳግም ወደ ምርት መመለስ እንዲሁም የተቀናጀ ስርዓት በማጠናከር በቂና ዘላቂነት ያለው አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችል ፤ የፖሊሲ አውጪዎችን ቁርጠኝነት እና የተጠቃሚዎችን ግንዛቤ መዳበር ይጠይቃል፡፡

እ.አ.አ የሐምሌ 2006 የዓለም ባንክ ትንበያ እንዳመላከተው ኢትዮጵያ ከ92 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ያላትና ከአፍሪካ ሀገራት በሕዝብ ብዛት ሁለተኛውን ደረጃ እንደምትሆን እና ከዚህም ውስጥ 18 በመቶ (ከ17 ሚሊዮን በላይ) የሚሆኑት የከተማ ነዋሪዎች እንደሆኑ ያመለክታል፡፡[1]ይህም ከሀገሪቱ ህዝብ ብዛት አንጻር ሲታይ አነስተኛ ቢሆንምከአንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት አጠቃላይ ሕዝብ ቁጥር የሚበልጥ ነው፡፡

ባለፉት 50 ዓመታት ውስጥ (እ.አ.አ1961-2013) የከተሞች ሕዝብ ብዛት በአማካይ በ5.84 በመቶ በማደግ ሲሆን ይህም ሲሰላ በየዕለቱ 756 ሰዎች ወደከተሞች እንደሚቀላቀሉ ቢያሳይም እ.አ.አ አቆጣጠር ከ2000 እስከ 2013 ባሉት ዓመታት ውስጥ ግን ዕድገቱ በ4.11 በመቶ ቀንሶአል የከተማ ነዋሪዎች ቁጥር ዕድገት እ.ኤ.አ ከ2013-2030 4.7 በመቶ ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡ በአሁኑ ወቅት የሚታየው የዕድገት መጠን በዚሁ ከቀጠለ እ.ኤ.አ በ2030 የከተማ ነዋሪዎች ብዛት 35% ይደርሳል ተብሎ ይገመታል፡፡[2]ከዚህ አንጻር ሲታይ የከተማ ነዋሪዎች ብዛት ከ13-15 ዓመታት በሚሆን ጊዜ ውስጥ በሁለት እጥፍ የሚያድግ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም ከአፍሪካ አህጉር አማካይ የእድገት መጠን በሰባት ዓመታት ያነሰ ነው፡፡[3]

---

[1] World Bank development Indicators , 2012

[2] Antonio Golini, Urbanization and urban population in Ethiopia based on UN, Department of Economic and Social Affairs, Population Division database

[3]Ibid.

በኢትዮጵያ 935 አካባቢ ከተሞች አሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ የከተማዎቹ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ እና የሚይዙት የሕዝብ ብዛትየሚለያይ እንደመሆኑ ዋና ከተማዋ፣ አዲስ አበባ ከማንኛውም መስፈርት አንጻር ስትታይ ሰፊ በመሆኗ በሁለተኛ ደረጃ የከተማ ማዕከል ከሆነችው ከድሬዳዋ ከተማ ጋር እንኳን ከሕዝብ ብዛት፣ ከተቋማት ብዛት እና ከተግዳሮቶች ውስብስብነትና ክብደት አንጻር ስትነጻጸር በአምስት እጥፍ የገዘፈ ሆኖ ይታያል፡፡

በአጠቃላይ 60 በመቶ የሚሆነው የከተማ ነዋሪ ሕዝብ የሚኖረው በ68 የከተማ ማዕከላት ውስጥ ነው፡፡ 850 የሚሆኑት የከተማ ማዕከላት ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ ብዛት ከ20,000 ያነሰ ሲሆንከነዚህም የከተማ ማዕከላት 507 የሚሆኑት ከ5,000 ያነሰ የህዝብ ብዛት ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር በሕዝብ ብዛት፣ የአስተዳደር ማዕከል እና የከተማ ማዕከሉ የሚገኝበትን አካባቢ መሰረት በማድረግ ማዕከላቱን በአምስት ቡድኖች ከፋፍሏቸዋል፡፡[4]

የከተማ ማዕከላቱ የሀገሪቱን ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት በማነቃቃት ላይ የጎላ ሚና ያላቸው ሲሆን ከአጠቃላይ ሀገር አቀፍ አጠቃላይ ምርት(GDP) ውስጥ 60 በመቶ የሚሆነው የከተሞች አስተዋፅኦ ነው፡፡[5] እንደ ሆቴሎች፣ የንግድ ዘርፍ እና ኢንዱስትሪ ያሉ መሠረተ ልማቶች ለከተሞች በፍጥነት ማደግ፣በከተሞችና በማዕከላት ዙሪያ ጠቃሚ የማህበራዊ እና ምጣኔ-ሀብታዊ ዕድገት መነቃቃት ቁልፍ ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ከተሞች ያለው የሳኒቴሽን እና ሃይጅን ችግሮች ከአገልግሎቶች ደረጃ ማነስ፣ ከቆሻሻ አያያዝ ግንዛቤ ማነስ እንዲሁም ተገቢ ካልሆኑ የሀይጅን ልምዶች ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ በአግባቡ ሳይታቀድ ከሚሠሩ ኢንደስትሪዎች የሚወጡ ቆሻሻዎች የተበከለ አካባቢ፣ አየር፣ የገጸ-ምድር እና የከርሰ ምድር ውኃ፣ በቂ ያልሆኑና ዘላቂነት የሌላቸው የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አሰባሰብ እና አወጋገድ መንገዶች ከፍተኛ የአካባቢ ብክለት፣ የጤና ጉዳት እና የሀብት ብክነት ከማስከተል አልፎ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖች/የህብረተሰብ ክፍሎች/ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል፡፡ የጤናና የኑሮ ደረጃ ጠቋሚዎች እንደሚያሳዩት በአብዛኞቹ የኢትዮጵያ ከተሞች ከተጓደለ የሳኒቴሽን ሁኔታ የተነሳ በተለይም እንደ ተቅማጥ ላሉ ውኃ-ወለድ በሽታዎች

---

[4] Ministry of Urban Development and Housing (MoUDH), guideline for towns clustering and classification

[5] Alen Etherington, Yemarshet Yemane, &Dr Ayele Belachew, for WaterAid Ethiopia, A review on the UWASH Context, Draft, July 19, 2009

ለሕይወት ከፍተኛ ጠንቅ መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡ እ.አ.አ በ2014 በዓለም ጤና ድርጅት እና በዩ.ኒ.ሴ.ፍ በተካሄደው የተቀናጀ የክትትል ፕሮግራም የከተማ ሳቴሽን ሽፋን እንደሚያመለክተው የተሻሻሉ የጋራ እንዲሁም ያልተሻሻሉ የመጸዳጃ መገልገያዎች እ.ኤ.አ. በ1990 20%፣ 30% እና 12% ከነበሩበት በ2015 ወደ 27%፣ 40% እና 26% አድገዋል፡፡በከተሞች አካባቢ እ.አ.አበ1990 ይታይ የነበረው 39% በሜዳ ላይ መጸዳዳትበ2015 ወደ 6% ቀንሷል፡፡

## ምቹ ሁኔታዎችና ተቋማዊ አደረጃጀት

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 43፣ 44፣ 90 እና 92 ላይ የከተማ ሳኒቴሽን አሠራርን በተመለከተየትኩረት አቅጣጫን በማስቀመጥደንግጓል፡፡ ለዚህ ስትራቴጂ መዘጋጀት መሠረት የሆኑትም እነዚህ አንቀጾች ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ከላይ የተጠቀሱት አንቀጾች ተግባራዊና ተፈጻሚ ይሆኑ ዘንድ ልዩ ልዩ አዋጆችን አውጥቷል፡፡ አዋጅ ቁጥር 197/2000 (የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ)፣ አዋጅ ቁጥር 200/2000 (የሕዝብ ጤና አጠባበቅ አዋጅ)፣ አዋጅ ቁር 300/2002 (የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ)፣ አዋጅ ቁር 661/2009 (የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ)፣ አዋጅ ቁጥር 692/2010 እንዲሁም ደንብ ቁጥር 173/2009 እና 299/2013 የዚህ ስትራተጂ ትግበራ ጽኑ መሠረቶች ናቸው፡፡ እንደ ጤና ዘርፍ የትራንስፎርሜሽን እቅድ፣ የውሀ ዘርፍ የልማትመርኃ ግብር እና የትምህርት ዘርፍ የልማት መርኃ ግብር ያሉ ልዩ ልዩ የሴክተር የትራንስፎርሜሽን መርኃግብሮች በአጠቃላይ በሁለተኛው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ከንውን ሥር ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ የከተማ ልማት እና አካባቢ ጥበቃ ዘርፎች በፖሊሲዎች፣ በደረጃዎች፣ በደምቦች፣ የሕግ ማዕቀፎች እና የልማት መርኃግብሮችቀረጻና ዝግጅት ላይተሳትፈዋል፡፡

የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር እ.ኤ.አ. ከ2014 ጀምሮ ተፈጻሚ የሆኑ ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ጋር የተያያዙ መመሪያና እቅድ አዘጋጅቷል፡፡ ሰነዱ የኢትዮጵያን ከተሞች በአምስት ዋና ቡድኖች የሚመድብ ሲሆን ዓላማውም አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችን ተሳታፊ ያደረገ ማኅበረሰብ-መር የቆሻሻ አያያዝን እና አወጋገድን ማስተዋወቅ ነው፡፡ በተጨማሪም የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ለሕንፃ ግንባታዎች የሚሆን ተግባራዊ ደንብ በማዘጋጀት ሂደት ላይ ነው፡፡ የውሃ ሀብት ዘርፍ ደግሞ የፈሳሽ ቆሻሻ አወጋገድን መመዘኛ ደረጃ እያዘጋጀ ነው፡፡

ከሳኒቴሽን እና ሀይጅን ጋር የተያያዙ እና በነባራዊ ሁኔታ ምዘናው ውስጥ የተካተቱ እጅግ ጠቃሚ የሆኑአጋዥ የፖሊሲ ሰነዶች ከዚህ በታች ተዘርዝዋል፡-

- የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ
- የውሀ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ብሔራዊ መርኃ ግብር
- የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም
- የጤናዉ ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን እቅድ

በተለይም በ1995-96 የተጀመረው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ትክክለኛው እውቀት እና ክህሎት ወደ ማኅበረሰቡ ሊተላለፍ ከቻለ ቤተሰቦች የራሳቸውን ጤና በራሳቸዉ ማምረት እንደሚችሉ ማዕከላዊ ፍልስፍና አድርጎ አስቀምጧል፡፡ ከ2010 ጀምሮ ተግባራዊ የሆነው የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ለገጠር የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን መነሻ በማድረግ 15 ፓኬጆችንና የአተገባበር ማንዋልን የተዘጋጁለት ሲሆን ከእነዚህም መካከል አራቱ በሳኒቴሽን እና ሀይጅን ላይ ያተኮሩ ፓኬጆች ናቸው፡፡

- የደረቅ እና የፈሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ
- ጤናማ የቤት አያያዝን ጨምሮ የግል እና የአካባቢ የጤና አጠባበቅ
- የምግብና የውሃ ንጽህና አጠባበቅና አያያዝ
- የመጸዳጃ ቤት ግንባታ፤ አጠቃቀም እና አያያዝ

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን የማስፋፋት ትግበራዎች በቀበሌ፤በጤና ኬላ ደረጃ መሠረታዊ የህክምና አገልግሎት እንዲሁም በቤተሰብ ደረጃ በሽታን ቀድሞ የመከላከል አገልግሎቶችን ተደራሽነት በማሻሻል ለጤና አኗኗር ምቹ የሆነ አካባቢን በመፍጠር ላይ ያተኩራሉ፡፡ እንደገጠሩ ሁሉ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምበቤተሰብ ደረጃ የተዋቀረው የ1-ለ-5 አደረጃጀት እና በጤና/በሴቶች የልማት ሠራዊት የሚደገፍ ነው፡፡

በከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ላይ የሚሠሩ በርካታ ተቋማት እና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች መኖራቸው በእጅጉ አበረታች ቢሆንም የሚመለከታቸውአካላት ጸግባርና ኃላፊነትና በሚገባ

የተለዩና ሙሉ በሙሉ የተቀናጁ ባመሆናቸው ከአፈጻጸም ጋር በተያያዘ ችግሮች ይታያሉ፡፡ በመሆኑም በሀገር-አቀፍ፣ በክልል፣ በከተማና የከተማ ማዕከላት ደረጃ እንዲሁም ከተቋማዊ ተግባራት አንጻር ክፍተቶች እንዲታዩ እና አንድ ተመሳሳይ ተግባር በተደጋጋሚ እንዲሰራ አድርጓል፡፡ በመሆኑም በቁጥራቸው ብዙ የሆኑ አዳንዶችም እርስ በርስ መቃረን የሚስተዋባቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞች፣ እቅዶች እና መመሪያዎች እንዲኖሩ አድርጓል፡፡

በከተማ ሳኒቴሽን ላይ ዐብይ ደንብ አውጪ አካላት የነበሩት አሁን በአካባቢ ጥበቃ፣ የደን ጥበቃ እና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ሥር የሚተዳደረው የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ (በአዋጅ ቁጥር 513/2007 አማካኝነት) እና ተጠሪነቱ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሆነው የምግብ፣ መድኃኒት እና ጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለሥልጣን (በአዋጅ ቁጥር 661/2002 አማካኝነት) ናቸው፡፡ በነዚህ መስሪያ ቤቶች አዋጆችና ደንቦች የተዘጋጁና የወጡ ቢሆንም ተግባራዊነታቸው እጅግ አነስተኛ ከመሆናቸውም ባሻገር እርስ በርስ የማይደጋገፉ እንዲሁም በአንድ ይዘት ላይ የሚያተኩሩ ተደጋጋሚ ጥረቶች የሚስተዋሉባቸው ናቸው፡፡ ደንቦቹን የማስፈጸም ሥልጣን ያላቸው እነዚህ ተቋማት ውጤታማነታቸውን ያላማከለ ተቋማዊ የመዋቅር ለውጥ በሚያካሂዱ ጊዜ የተግባርና ኃላፊነቶች ድግግሞሽ ተስተውሏል፡፡

በዘርፉ እድገት ውስጥ ብሔራዊ የውሃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን መርኃ ግብር ተነድፎ የውሃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ተሳታፊ አካላት በህብረት እንዲሠሩ ተመቻችቷል፡፡ ይህ መርኃ ግብር ተግባር አንድ ትልቅ የከንውን ደረጃን የሚመላከት ሲሆን አራት ዋና ዋና ዘርፎችን ይዟል፡፡- እነርሱም፡-

ሀ) የገጠር እና በከብት ማርባት የሚተዳደሩ አካባቢዎች የውሃ፣ ሳኒቴሽን እና ሐይጅን

ለ) የከተማ ውሀ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን

ሐ) ተቋማዊ የውሀ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን እና

መ) የዘርፍ አቅም ግንባታ ናቸው፡፡

ብሔራዊ የውሀ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን መርኃ ግብሩ በ2012 ዩኒቨርሳል አክሽን ፕላን እና በአንደኛው የልማት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ግቦች መሠረት በ2013 ተዘጋጅቶ ትግበራው ተጀምሯል፡፡ ከተሻሻሉት የሁለተኛው ልማት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ግቦች እና የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ዘርፍ ወሳኝ ቅድመ ሁኔታዎችን ከማሟላት እንዲሁም የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ አገልግሎትን ከማካተት አንጻር የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂው የልዩ ልዩ ዘርፎችን ትብብር እና ብቃት የሚጨምር በመሆኑ ቁልፍ ሰነድ ነው፡፡

የከተማ ሳኒቴሽን በአሁኑ ወቅት የተለያዩ ይዘቶች እና ጉዳዮችን በተመለከተ ሥልጣን በተሰጣቸው ልዩ ልዩ የዘርፍ አካላት አማካኝነት ይከናወናል፡፡ የከተማ ሳኒቴሽን በፌደራል እና በክልል ደረጃ የሚገኙ ተቋማትይብዛም ይነስም ተመሳሳይ አወቃቀር አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ አቅርቦቶችን በማስገኘት፣ አቅም ግንባታን በማካሄድ እና ተቋማትን ከማስገንባት አንጻር በዋናነት ለክልሎች ድጋፍ የሚሰጡት በዋናነትሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ናቸው፡፡ በከተማ ማዕከላት ደረጃ የሁሉም የሳኒቴሽን ተሳታፊ አካላት ሚናዎች እና ኃላፊነቶች ሙሉ በሙሉ በከተማ ማዘጋጃ ቤቶች ስልጣን ሥር የሚከናወኑ ናቸው፡፡

## ለከተማ ሳኒቴሽን የተሰጠው ትኩረት

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በከተማ ልማት እቅድ ውስጥ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን የተሰጠው ትኩረት ብዙም አትኃቢ አልነበረም፡፡ምንም እንኳ ከተሞች በጀት መድበው ሳኒቴሽንን የዋና እቅዳቸው አንድ አካል አድርገው ሊያካትቱ የሞከሩ ቢሆንምሀገር-አቀፍ በሆነ መልኩ ትግበራው አነስተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም ግንዛቤ የማስጨበጥ ሂደቱና የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ዘዴዎች የከተማ አቀፍ አቀራረብ ኖሯቸው በሚገባ የተዘጋጁ አልነበሩም፡፡ የሳኒቴሽን ኃላፊነት በቤተሰቦች ላይ ብቻ የሚጣልሆኖ ሲታሰብ ቆይቷል፡፡ በቂ የሆነ የአገልግሎት አሰጣጥ መዋቅር በአብዛኛዉ ያልነበረ ሲሆን መላውን የክንውን ሰንሰለት የሚመዘን በተገቢዉ ሁኔታ የሚመዝንአካል አልነበረም፡ ሳኒቴሽን ካሉትሌሎች ተግዳሮቶች በተጨማሪ በአጠቃላይ ከከተማ ዕድገት ጋር በተያያዘ በጤና ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ካለመረዳት አንጻር በከተማ አስተዳደሮችና በየደረጃው እንዲሁም በነዋሪዎች ዘንድ በእቅድ ውስጥ ከማካተት ባለፈ ለዘርፉ የሚያስፈልገውን በቂ በጀት ከመመደብ አኳያ ተገቢው ትኩረት ሳይሰጠው ቆይቷል፡፡

## የጋራ ስምምነት መፍጠር፣ የባህሪ ለውጥ ተግባቦት እና ማስተዋወቅ

የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ የዓለም-አቀፍ ተሞክሮዎች እንደ መነሻና ጥሩ ልምድ በመውሰድ በተቻለ መጠን መተግበርና ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የዛምቢያ የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን ንግድ ልማት እንዲሁም የሩዋንዳ ጠንካራ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በሀገራችንም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሥር በሚተገበረው በጤና ኤክስቴንሽን መርኃግብር አማካኝነት አገልግሎቱን ከማስተዋወቅ አንጻር ሰፊ ሥራ ተሰርቷል፡፡ ይህ አካሄድ በገጠር አካባቢዎች አስደናቂ ተጽዕኖን ቢያመጣም የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን መርኃግብር መተግበር ከተጀመረ አጭር ጊዜ

በመሆኑና ካለው ልዩ የከተማ ሁኔታ ጋር ሊጣጣም በሚችል መልኩ ባለመተግበሩ ዳግመኛ ሊቀረጽ እና የተሻለ ድጋፍ ሊደረግለት አስፈላጊ በመሆኑ እየተሰራ ይገኛል፡፡

## አገልግሎት አሰጣጥ

ኢትዮጵያ ባለፉት አስርት ዓመታት የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን መገልገያዎች ያሏቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች በመገንባት፣ የቆሻሻ አወጋገድ ላይ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ እንዲሁም የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን አገልግሎት ተደራሽነትን በማስፋፋት በድህነት ቅነሳ እና የከተማ ልማት ላይ አስደናቂ መሻሻልን አስመዝግባለች፡፡ የከተማ ማዕከላት ወደላይም ወደ ጎንም በፍጥነት እየተስፋፉና የገጠር መንደሮችም ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ በአነስተኛ ከተሞች ሥር እየተደራጁ ነው፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ ከተሻለ የአገልግሎት አሰጣጥ አንጻር አርዓያ የሚሆኑ ተግባራት እየተስተዋሉ ነው፡፡ ለምሳሌ እንደ አዲስ አበባ፣ ባህር ዳር፣ መቀሌ፣ ጎንደር፣ ውቅሮ እና ሀዋሳ ያሉ ከተሞች ለደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ከሚያገለግሉ ጥቃቅንና አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ጋር በሽርክና የሚሰሩበትን መንገድ ቀይሰዋል፡፡ የመቀሌ ከተማ የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶች አያያዝ፣ በባህር ዳር እና በሌሎች ከተሞች የሚስተዋለው የሚበሰብሱ የደረቅ ቆሻሻን ክፍል መለየት እና ለጥቅም የሚውልበትን መንገድ መፍጠር፣ በአዲስ አበባ ባዮ ጋዝን በጥቅም ላይ ማዋል ጅማሬ፣ በአዲስ አበባ ረጲ የደረቅ ቆሻሻ ማከማቻው ኃይል ማመንጨት መጀመሩ እና በሀዋሳ ከተማ የሚገኘው የቆሻሻ መጣያስፍራ በሌላ የመቀየር ጥረቶችን አስፋፍቶ ለመቀጠል አቅም የሚሰጡ አዎንታዊ ተሞክሮዎች ናቸው፡፡

ይህ ቢሆንም ትምህርት ልንቀስምባቸው እና በተቻለ ፍጥነት መፍትሔ ልንፈልግላቸው የሚገቡ አሉታዊ ምሳሌዎችም አሉ፡፡ የነባራዊ ሁኔታ ትንተናው እንደሚያሳየው በአብዛኞቹ የከተማ አካባቢዎች ውጤታማ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ የለም፡፡ ተግዳሮቶቹም የቆሻሻ መሰብሰቢያ ተሽከርካሪዎች፣ የመጸዳጃ ቤት ቆሻሻን የሚመጥጡ መኪናዎች እንዲሁም በአግባቡ የተዘጋጁ የቆሻሻ ማከማቻ ስፍራዎች አለመኖር፣ የጋራ እና የሕዝብ መጸዳጃ ቤት መገልገያዎችን አጠቃቀም እና አስተዳደር ችግር ፤ ደረቅ ቆሻሻዎችን በዓይነታቸው ሳይለዩ ማስወገድ፣ ፍሳሽ የኢንደስትሪ ቆሻሻዎች ሳይለዩ ወደ ውሀ አካላት መለቀቅ፣ የግልና የጋራ መጸዳጃ ቤት ለመገንባት የሚያስችል በቂ መሬት አለመኖር፣ ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻን ለመሰብሰብ የሚያስችል በቂ ቴክኖሎጂ፣ ማጓጓዣ እና ማስወገጃ መንገድ አለመኖርን ያካትታሉ፡፡

የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት መዘርጋት ኃላፊነት ያለባቸው የከተማ ማዘጋጃ ቤቶች ቢሆኑም አብዛኞቹ አስፈላጊው የገንዘብ፣ ሙያዊ (ለማጓጓዝ፣ አወጋገድ እና ማከም የሚሆኑ) እና የሰው ኃይል አቅም የላቸውም፡፡ ጥቂት ማዘጋጃ ቤቶች ወጥና የተቀናጀ የቆሻሻ አያያዝ ስርዓት የሌላቸው ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ አገልግሎት የሚሰጡት በተወሰኑ ቀበሌዎች እና አጠቃላይ ከሚመነጨው ቆሻሻ ውስጥ ለመሰብሰብ የሚችሉት የተወሰነ መጠን ያለውን ብቻ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበሰበው በየወቅቱ ባለመሆኑ አንዳንድ ጊዜ በሳምንት ወይም በወር ሊሆን ይችላል ፡፡ የቆሻሻ ማስወገጃ አገልግሎት መስጫዎች በበቂ ሁኔታ አለመኖራቸው ቤተሰቦች የሚያመነጩትን ቆሻሻ ሳይለዩ ለመጣል ወይም ለማቃጠል ይገደዳሉ፡፡

የከተሞች የቆሻሻ አወጋገድ ሰንሰለት ደንብን ተከትለው ለተቋቋሙና ላልተቋቋሙ አካላት የገቢ ምንጭ እንደመሆኑ እና ሰፊ የሰው ኃይል መኖሩ በዘርፉ አያሌ የሥራ ዕድሎች መፍጠር ያስችላል፡፡ በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ስለ ፍሳሽ ቆሻሻ ባለሙያዎችንለማሰልጠን ጥረቶች እየተደረጉ እና ለአረንጓዴ ልማት ኢኮኖሚ ይበልጥ ቅድሚያ እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመር እና ማጠራቀሚያ ጉድጓድ ባለመኖሩ ብዛት ካላቸው የከተማ ነዋሪዎችና በውኃ ግፊት የሚሠሩ የተቋማት መጸዳጃ ቤቶች ፍሳሽ ቆሻሻ ዘወትር ወደ አካባቢው ወንዝና ገላጣ ሜዳዎች በመለቀቅ ላይ ነው፡፡ በአብዛኖቹ ከተሞችበአቅም፣ በቁሳቁስ፣ በሀብት ምንጭ እና መሠረተ ልማት አለመኖር የተነሳ አግባብ የሆነ የዓይነ ምድር አወጋገድ አገልግሎት የለም፡፡ በከተሞች የመኖሪያ አካባቢ ሳኒቴሽን አገልግሎት (የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓድና የመጸዳጃ ቤት ጉድጓድ) በብዛት ጥቅም ላይ ቢውልም አሁን ያለው ሁኔታ የግንባታ፣ በአግባቡ አይነምድር የማስወገድ/ለማከም መገልገያ እጥረት እና አንዳንድ ከፍሳሽ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ ጋር የተያያዙ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ የመኖሪያ አካባቢ አይነምድር ዝቃጭ የሚወገደው በውስን ህዝብ መሰረተ ልማት መገልገያና የኅብረተሰብ ቁጥጥር ነው፡፡

አዲስ አበባ እና ጎንደር በአግባቡ የተዘረጋ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመር ካላቸው ከተሞች በምሳሌነት ቢጠቀሱም የአገልግሎታቸው ተደራሽነት ለተወሰነ የሕብረተሰብ ክፍል ብቻ ነው፡፡ በአብዛኛዎቹ ከተሞች ላይ የሚስተዋለው የውሀ እጥረት፣ ኩሪወችን አጎልብቶ ለመጠቀም መሬት እጥረት እና ለኩሬዎች ማከሚያ ከሚያስከትለው ወጪ የተነሳ በኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ መደበኛ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ስርዓትን መዘርጋት ወይም ማስፋፋት ቀላል ሥራ አይደለም፡፡

በተጨማሪም ሀገሪቱ ከግብርና መር ወደ ኢንደስትሪ መር ምጣኔ ሀብት በምትሸጋገርበት ሂደት

ውስጥከኢንደስትሪ የሚወጡ ቆሻሻዎች መጠን የሚጨምር መሆኑ አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡ እንደ አዲስ አበባ እና በዙሪያዋ ባሉ በከፍተኛ ቁጥር ኢንደስትሪዎች የሚገኙባቸው ከተሞች ውስጥ የሚገኙት እንደ አቃቂ፣ ዱከም እና ሞጆ ያሉ ወንዞች ቁጥጥር ያልተደረገበት ጠንቅ የሚያስከትል ደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ የሚደፋባቸው ሲሆን በዙሪያው ላሉት አካባቢዎች የመስኖ ውሀ ምንጭ ወደ ሆነው የአዋሽ ወንዝ ይቀላቀላሉ፡፡ ይህም የጤና እና የአካባቢ ጥበቃ ችግሮች ቅድሚያ የሚሰጣቸው አሳሳቢ ጉዳዮች እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ በከተሞች አቅራቢያ የሚገኙ ሀይቆች እና ከተሞችን የሚያቋርጡ ወንዞች እንዲሁም በኢንደስትሪዎች እና በቴክኖሎጂ የሚታገዙ የእርሻ ቦታዎች አቅራቢያ የሚገኙ ወንዞች እና ሀይቆች ቁጥጥር ያልተደረገባቸው የቆሻሻዎች ማስወገጃ እየሆኑ በመምጣታቸዉ የመበከል እድላቸው የሰፋ ነው፡፡

በአብዛኛው ከተሞች የፍሳሽ መስመሮች ከዋና መንገዶች ጎንየሚሰሩ ናቸው፡፡ የመሬት አቀማመጣቸው አባጣ ጎርባጣ የሆኑ ከተሞች ደግሞ የወንዝ ዉሃን ለተለያየ አገልግሎቶች ይጠቀማሉ፡፡ በአዲሰ አበባና በአንዳንድ ከተሞች እንደሚታየውይህየፍሳሽ መውረጃ መስመር የዝናብ ውኃን ብቻ ሳይሆን እጣቢዎችንና ከፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ የሚወጡ ፍሳሻ ቆሻዎችንና ሞልተው የሚፈሱ መጸዳጃ ቤቶች ሁሉ ይደባለቁበታል፡፡ የመሰረተ ልማቱ የመገልገያ መሳሪያዎች እንዲሁም ለዚህ ፕሮግራም የሚውል ፋይናንስ ባለመሟላቱ ፣የተቀናጀ እቅድ፣አግባብነት ያለው ቴክኖሎጂ እና የሰለጠነ የሰው ሀይል ባለመኖርሩ ምክንያት ህብረተሰቡን ለጤና ችግሮች ያጋልጣል፡፡

## የተቋማት ሳኒቴሽን

በከተሞችየማህበረሰቡ የመዋዕለ ነዋይ ፍሰት በተለይም በትምህርት ቤቶች እና በጤና ተቋማት ውስጥ በሚገኙ ተቋማዊ የሳኒቴሽን መገልገያዎች ላይ የተገደበ ነው፡፡ በአብዛኛዎቹ የተቋማት ግንባታና ጥገና እቅድ እና አተገባበር ውስጥ ሳኒቴሽን ተገቢው ትኩረት አይሰጠውም፡፡ በተቋማት ውስጥለህመምተኞች እና በእድሜያቸው ለገፉ ሰዎች የሚሆን የሳኒቴሽን መገልገያ እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የወር አበባ የንጽህና መጠበቂያ መገልገያባለመኖሩ በጤና፣ ምጣኔ ሀብት እና ትምህርት ላይ የሚያሳድረው ጫና ከፍተኛ ነው፡፡

## የዘርፎች አቅም እና የግሉ ዘርፍ

ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመቀናጀት መስራት በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እና በተሻሻሉ አገልግሎት አሰጣጥ ረገድ ለፈጠራ ጥናቶች ቁልፍ ማነቃቂያ ሆኗል፡፡ ለምሳሌየጎንደር ዩኒቨርስቲ የጉድጓድ

መጸዳጃ ቤቶችን የቆሻሻ አወጋገድ የሚያግዝ የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂን የተመለከተ ወደ ተግባር ሊቀየር የሚችል  እቅድ አዘጋጅቷል፡፡

በሌላ በኩል በማቀድ፣ መተግበር፣ መከታተል እና ምዘና እንዲሁም ያሉትን አቅርቦቶች ማስተዳደር ላይ የሚታየው የአቅም(የሙያ/ክህሎት፣ መሳሪያዎች እና አሰራሮች) ማነስ  በሁሉም ከተሞች ላይ የሚስተዋሉ አሳሳቢ ጉዳዮች ናቸው፡፡የግሉ ዘርፍ ሚና በመሠረተ ልማት እድገት ላይ የተገደበ ሲሆን ዘርፉ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተሳታፊ አይደለም፡፡ የግሉ ዘርፍ በመሰረተ ልማት ግንባታ እንጂ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚገባውን ያህል አልተሰማራም፡፡ በግሉ ዘርፍ አልፎ አልፎ የሚደረጉ የአገልግሎት አሰጣጥ እንቅስቃሴዎች ደንብ ያልወጣላቸው በመሆናቸው አብዛኛውን ጊዜ ደንብን ያልተከተሉ አሠራሮች ቀጣይነትን ያሳያሉ፡፡ ደንብን ተከትሎ ያልተዋቀረው ዘርፍ (እንደ ቆሻሻን በድግመ-ዑደት በጥቅም ላይ ማዋል በመሳሰሉ መንገዶች) በሳኒቴሽን ላይ የሚጫወተው ሚና ጠቃሚ ቢሆንምደንብ ያልወጣለት እና በዘርፉ ምዘና ወቅት የማይካተት ነው፡፡

## ሳኒቴሽንን በገንዘብ መደገፍ

የከተማ ሳኒቴሽን አገልግሎትን በገንዘብ መደገፍ እና ተገቢውን የክፍያ ስርዓት መዘርጋት በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ጠቃሚ ድርሻ አለው፡፡ ዋና ዋናዎቹ ተግዳሮቶች ለሳኒቴሽን ተለይቶ የሚያዝ በቂ በጀት አለመኖር፣ ተጠቃሚዎች ለመክፈል ፈቃደኝነት ቢኖራቸውም የአገልግሎቱ ጥራት ዝቅተኛ መሆን፣ የገቢ አሰባሰብ በተገቢው መልኩ አለመከናወን፣ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለመደገፍ የሚሆን በግልጽ የተቀመጠ መመሪያ አለመኖር፣ “የበከለው አካል ይከፍላል” የሚለው መርህ በትክክል በተግባር ላይ አለመዋል እንዲሁም ለውሀ አገልግሎት የሚውለው ክፍያ አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ ለሳኒቴሽን አገልግሎት የሚከፈለውን ክፍያ ማሳነስ አለመቻል ይጠቀሳሉ፡፡

ለሳኒቴሽን የሚውለው የገንዘብ መጠን እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ዘርፉ ያሉትን ውስን የገንዘብ አቅርቦቶች ለመጠቀም ያለመቻል ታይቶበታል፡፡ ከለጋሾች የሚገኝን ገንዘብ እንደመጠቀም ያሉ ቀድሞ የነበሩ ያልተቀናጁ አካሄዶች ለዕድገቱ ማነቆ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ የምጣኔ ሀብት ስርጭት ደንብን የተከተለ ባለመሆኑም የውሀ እና ሳኒቴሽን አገልግሎቶችን የማግኘት ዕድል በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ በሚገኙትና በተሻለ ኑሮ ደረጃ ባላቸው ቤተሰቦች መካከል እየሰፋ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም፣ወርሃዊ የገቢ ሁኔታቸው የሚዋዥቅ ቤተሰቦችን የአገልግሎቱ ተደራሽ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ለሳኒቴሽን አገልግሎት የሚቀመጡ ክፍያዎችን የመተመን ስልት በከተሞች አካባቢ የሚታየውን ደንብየቤተሰቦችን የገቢ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ ለሳኒቴሽን የሚመደብ በጀት ዝቅተኛ ቢሆንም ይህንን ሴክተሩ ከተለያዩ ምንጮች የሚያገኘውን ገንዘብ በወቅቱ ለመጠቀም ያለመቻልም ችግር ይታያል፡፡ ይኸውም ከለጋሽ ድርጅቶች የሚገኝ ገንዘብን ለመጠቀም ያለው ተቋማዊ አደረጃጀት በራሱ ለውጥ ለማምጣት ትልቅ ማነቆ መሆን ጉዳዩን ውስብስብ ያደርገዋል፡፡ ያልተመጣጠነ የምጣኔ ሀብት ዕድገቱ በሀብታምና በደሀው የከተማ ነዋሪ መካከል ያለውን የመጠጥ ውኃ አቅርቦት እና የሳኒቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለው ልዩነት እንዲሰፋ አድርጎታል፡፡ በመሆኑም ዘርፈ-ብዙና መደበኛ ያልሆኑ የቅጥር ስራ ላይ የተሰማሩትን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ የሳኒቴሽን አገልግሎት ስልት ታሳቢ በማድረግ ያልተስተካከለ የገቢ ምንጭ ያላቸዉን ወይም ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች ታሳቢ ያደረገ አገልግሎት ማስፋፋት አስፈላጊ ነው፡፡

## ሙያዊ ፈጠራ፣ ምርምር እና ልማት

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው የኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲዎች ለዘርፉ የሚሆኑ የፈጠራ ሥራዎችን እና ምርምሮችን በመስራት ረገድ አስተዋጽዖ በማድረግ ጠቃሚ ሚና ያላቸው ቢሆንም እስከአሁን ግን ሀገሪቱ ለሳኒቴሽን እና የሀይጅን ምቹና ተስማሚ ቴክኖሎጂ በማቅረብ ረገድ እጥረት ይታይባታል፡፡ለምሳሌ:- ለመጸደጃ ቤቶች፣ ቆሻሻን መልሶ መጠቀም ወይም ድግመ-ዑደት፣ የማጠራቀሚያ ታንኮች እጥበት፣ እንዲሁም በልዩ ልዩ ነባራዊ ሁኔታዎች ውስጥ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የመሣሪያዎች እና የቁሳቁስ አማራጭ የላትም፡፡ አብዛኛዎቹ ቴክኖሎጂዎች እና አሠራሮች ተግባራዊ የሚሆኑት የሀገሪቱን እና የከተሞቿን ማህበራዊ እና ባህላዊ ሁኔታዎች ሳያገናዝቡ ነው፡፡ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ሥር እየተደረጉ ያሉት ቀጣይነት ያላቸው የምርምር መርኃግብሮች ሙሉ ለሙሉ ድጋፍ የሚደረግላቸው አይደሉም፡፡፣ ግኝቶቻቸውም በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ በማድረግ በኩል ውስንነቶች አሉ፡፡

## ክትትል እና ምዘና

ለከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ተብሎ የተዘጋጀ ግልጽ እና ለብቻው የተቀመጠ የግምገማ እና የምዘና አሠራር የለም፡፡ የመጸዳጃ ቤቶች ሽፋን በተወሰነ መጠን ክትትል የሚካሄድበት ቢሆንም የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አሰባሰብ እና ማከምንያካተተ አይደለም፡፡ ይህም ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ የዕቅድ ትግበራ እንዳይካሄድ ያደርጋል፡፡ የሳኒቴሽን መገልገያዎችን እና የአገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ በሙያዊ አደረጃጀት፣ የአስተዳደር አወቃቀር እና በበጀት ረገድ ነባራዊ ሁኔታን የሚገልጽ መረጃ እጥረት ይስተዋላል፡፡

## 1.2. የስትራቴጂው መነሻ ምክንያት

የዚህ ስትራቴጂ ተግባራዊ መሆን በሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት፣ በተፈጥሯዊው የአካባቢ ይዞታ እና እጅግ ተጋላጭ የሆኑትን ጨምሮ በሁሉም የከተማ ነዋሪዎች ጤና እና ደህንነት ላይ አዎንታዊ ለውጥ እንደሚያመጣ ይጠበቃል፡፡የከተማ ሳኒቴሽን ጉዳይ በዘርፉ ተሻጋሪ ትግበራዎች፣ በከተሞች መካከል የሕዝብ ብዛት ልዩነት በመኖር፣ በመልከአ ምድራዊ አቀማመጥ ልዩነት፣ የነዋሪዎች የገቢ ምንጭ መለያየት፣ የቀረጥ ገቢ የሚያስገኙ ክንውኖች፣ የአስተዳደር አቅም፣ ወዘተ.ምክንያት የተወሳሰበ ነው፡፡ በመላው ሀገሪቱ እየተከናወነ ካለው የከተማ ልማት ጋር አብሮ የሚጓዝ ስርዓት ለመፍጠር ተፈላጊ የሆኑትን ለውጦች ማምጣት ጠቃሚ ነው፡፡ የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂው ቀጣይ ትግበራዎችን እንዲያካትት ሆኖ የተዘጋጀ እንዲሁም ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚፈለጉ ተቋማዊ፣ ገንዘብ ነክ፣ ደንብ፣ ማስተዋወቅ፣ የቴክኖሎጂ እና ክንዋኔዎችን ላይ በሚያተኩረው ስልታዊ የትግበራ እቅድንበማካተት ነው፡፡

በስልታዊ የትግበራ እቅዱ አማካኝነት የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂውን በስኬታማነት የመተግበር ሂደት በልዩ ልዩ ከተሞች የከተማ ሳኒቴሽንን ለማስተዳደር እና የመርኃ ግብሩን አፈጻጸም በተቀናጀ ሁኔታ ለመከታተል በተቋቋሙ አካላት ውጤታማነት ላይ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ስትራቴጂው ሁሉም ከሳኒቴሽን ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስራዎች ያለውን ምጣኔ ሀብት እየተጠቀሙ፣ በሀገሪቱ የሚገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን እየቀመሩና እያሰፉ፣የግሉን ዘርፍ እና ማኅበረሰቡን መሠረት ያደረጉ ኢንተርፕራይዞች እያሳተፉ በከተማ እና አነስተኛ ከተሞች ልማት ስትራቴጂላይ የተመሠረተአተገባበር እንዲኖር ያበረታታል፡፡ ለሳኒቴሽን መርኃግብር የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ በከተማ እና በአነስተኛ ከተሞች እቅድ አንድ አካል ተደርጎ ስለሚወሰድ ይህንን ለማስፈጸም የከተማ እና የከተማ ማዕከላት መስተዳድሮች አቅም መገንባት አስፈላጊ ነው፡፡ ስተራቴጃዊ የአተገባበር ዕቅድ በማዘጋጀት ይህን ስትራቴጂ እንዲተገበር ማድረግ የአገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸሙንና አቅርቦቱን ለመገምገም እና ያመጠውን ለውጥ ለመለካት ይረዳል፡፡

## 1.3. የስትራቴጂው የትግበራ ወሰን /Scope/

ይህ የስትራቴጂ ሰነድ በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በተዘጋጁት መመሪያዎች መሰረት በተከፋፈሉት ሁሉም የኢትዮጵያ ከተሞች እና የከተማ ማዕከላት ውስጥ የከተማ ሳኒቴሽን እና መርኃ ግብር አገልግሎትን ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡

በዚህ ስትራቴጂ ውስጥ የተካተቱ ዐበይት ተግባራት የሚከተሉትን ናቸው፡፡

- የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ አገልግሎት ፡- ዓይነ ምድርን፣ በሰዎች የዕለት ተዕለት ኑሮ የሚፈጠሩ (የቤት ውስጥ ፍሳሽ ቆሻሻዎችን የኢንዱስትሪ፣ ከተለያዩ ተቋማት የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻን ጨምሮ ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ማስወገድ

- የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ አገልግሎት፡- በሰዎች የዕለት ተዕለትእንቅስቃሴ (የቤት ውስጥ፣የኢንዱስትሪ፣ የንግድ እና ተቋማዊ) አማካኝነት የሚፈጠሩ ደረቅ ቆሻሻዎችን ጨምሮ ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ማስወገድ

- የማስተዋወቅ እና የባህሪ ለውጥ ሥራዎች መስራት፡- ትክክለኛ የሀይጅን ልምዶች፣ የመጸዳጃ ቤት አጠቃቀም እና አያያዝ፣ አገልግሎቶችን የመጠቀም እና ክፍያ መፈጸም፣ በሜዳ ላይ መጸዳዳትን ማስቀረት፣ የወር አበባ ንጽህና አጠባበቅ፣ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ (ማሳነስ፣ መልሶ መጠቀም፣ ድግመ-ዑደት) እንዲሁም ሌሎች ተግባራትን ያጠቃልላል፡፡

በዚህ የስትራቴጂ ሰነድ የሚከተሉት ቁልፍ ነጥቦች እና ተዛማጅ ዓላማዎች እንዲሁም አቀራረቦች ተተንትነዋል፤ይህ ስትረቴጂ የትግበራ ዕቅድ የሚከተሉትን ጉዳዮች በጥልቀት ይመለከታል፡-

- የአፈጻጸም ቅድመ ሁኔታ-አገልግሎቶች እንዴት በተሻለ መልኩ እንደሚሰጥ፣የሕዝብ እና የግል አገልግሎት ሰጪዎች ግንኙነት እና የኮንትራት ስምምነት

- ዝቅተኛ የአገልግሎት ፓኬጆች - ለእያንዳንዱ የከተማቡድን የሚሆኑ አአገልግሎቶችፓኬጆች እና ቴክኖሎጂዎች አቀራረብ ለየማዘጋጃ ቤቶቹ ተለይተው አገልግሎቱን ለማስጀመር እና ለማስፋፋት እንዲቻል

- የዋጋ ተመን እና የፋይናንስ ትንተና መመሪያ - በጥቅም ላይ ሊውሉ የታሰቡትን ቴክኖሎጂዎች የገንዘብ አዋጪነት (ከመነሻ መዋዕለ ነዋይ ፍሰት እና ሥራ ማስኬጂያ ተመኖች ጋር በተያያዘ) ለመወሰን እና ለእያንዳንዱ የከተማ ቡድን ዘላቂ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን ተስማሚነት ለማስቀመጥ

# 2. የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂው መርሆዎች

የሚከተሉት መርሆዎች በተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂው አፈጻጸም ወቅት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

- ፍትሐዊነት - የከተማ ሳኒቴሽን ከምጣኔ ሀብታዊ አቅም፣ ስርዓተ-ጾታ፣ ዕድሜ፣ የአካል ጉዳተኝነት፣መልከዓ ምድራዊ መገኛ እና ሌሎችም ጉዳዮች አንጻር ሲታይ ሰፋ ያለ ልዩነቶች የሚስተዋሉበት ነው፡፡ ስለሆነም በስትራቴጂው እቅድ ዝግጅት፣ ትግበራ እና አገልግሎት አሰጣጥ ወቅት ለሁሉም የማኅበረሰብ አካላት እና መልከዓ ምድራዊ መገኛዎች ፍትሐዊነት የተሞላበትአሰራር በተለይም ሀብትን ከማዳረስ አንጻር እንዲኖር ትኩረት ይሰጣል፡፡ ስትራቴጂው ሁሉንም ደረጃዎች እና ገጽታዎች በማየት ፍትሐዊ እንዲሆን ጥረት ይረደጋል፡፡፡፡
- አጋርነት - ስትራቴጂው በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን ባለሥልጣን የሆኑት የመንግሥት ተቋመት፣ የግሉ ዘርፍ፣ ማኅበረሰብን መሠረት ያደረጉ ተቋማት፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲሁም የልማት አጋሮች ንቁ ተሳትፎ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ስትራቴጂው በአሁኑ ወቅት በተለያየ ደረጃ እና በተለያየ መጠን በከተማ ሳኒቴሽን ክንውን ላይ ድርሻ ያላቸው ልዩ ልዩ የዘርፉ ተሳታፊ አካላት ጥምረት እንዲፈጥሩ ያግዛል፡፡ በመሆኑም ስትራቴጂው ልዩ ልዩ ወደ ላይና ወደ ታች እንዲሁም ወደ ጎን ግንኙነት ያላቸው ባለ ድርሻ አካላት ሆነ በጎንዮሽ ጠንካራ አጋርነት እንዲኖራቸው ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡
- ቅንጅታዊ አሰራር - በዚህ ስትራቴጂ አፈጻጸም ሂደት በከተማ ሳኒቴሽን የሚሳተፉ የተለያዩ አካላትበተለይም የውሀ፣ የጤና፣ የከተማ ልማት፣ የአካባቢ፣ የፋይናንስ፣ የባህል፣ የቱሪዝም እና ሌሎች አካላት ቅንጅታዊ አሰራር ቁልፍ መርህ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ ከተሞች ወደ ዘመናዊ የአኗኗር ደረጃ ማደጋቸው እና ከፍታቸው የጨመረ ህንጻዎች መሠራታቸው በውኃ የሚሠሩ መጸዳጃ ቤቶችን ቁጥር የሚጨምር በመሆኑ ተጨማሪ የውኃ አቅርቦትን መጠየቁ አይቀሬ ነው፡፡ የከተማ ሳኒቴሽንን ተግዳሮቶችን ለመፍታት የውሀ አቅርቦት ጥራት እና መጠን ተመሳሳይ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው ፡፡

- ወጥነት - የከተማ ልማት በፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ግቦች፣ የትግበራ አካሄዶች እና ዘዴዎች የሚመራ ነው፡፡ ጥቅል እቅድ እና አካባቢያዊ ማስተር ፕላኖች እንዲሁም የልማት እቅዶች ሳኒቴሽንን የልማቱ አንድ አካል አድርገው እንዲያካትቱ ይጠበቃል፡፡ በአፈጻጸም ሂደት ላይ ካሉ ወይም አዳዲስ ከሆኑ ስርዓቶች እና አካሄዶች ጋር ወጥነት ባለው መልኩ ተፈጻሚ መሆን ካልቻለ የሳኒቴሽን አገልግሎት ውጤታማ እና ተጨባጭ ለውጥ ሊመጣ አይቻልም፡፡ የአገልግሎት አሰጣጡን ጥራት እና ብቃት ለማሻሻል፣ ስትራቴጂው ከአጠቃላይ የከተማ ልማት መርኃ ግብሮች እና ሌሎች ጠቃሚ የዘርፉ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ጋር ወጥነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

- የሥራ ትብብር/ኀብረት -ዋና ክፍተት ሆኖ በቁልፍ ተግዳሮትነት የተለየው በልዩ ልዩ ባለ ድርሻ አካላት መካከል የትብብር ማነስ መኖሩ ነው፡፡ የከተማ ሳኒቴሽን ከባህሪው አንጻር በአንድ ተቋም አማካኝነት ብቻ ሊከወን የሚችል አይደለም፡፡ በተለይም እንደ ከተማ ልማት፣ ጤና፣ ውሀ፣ አካባቢ ጥበቃ፣ ፋይናንስ ያሉ የተለያየ ዘርፍ ሥር በተሰማሩ ተቋማት የጋራና የተናጠል ኃላፊነት የሚሠራ ነው፡፡ ስትራቴጂውን ለማስፈጸምምቹ አማራጭ የሚሆነው ጠንካራ እና ቀልጣፋ ቅንጅታዊ አሠራርን በመፍጠር ነው፡፡ የትብብር ዘዴው ልዩ ልዩ የሕዝብ እና የግል ዘርፍ ባለ ድርሻ አካላት እንዲሁም ማኀበረሰቡ ንቁ ተሳትፎ ሊያደርግ የሚችልበት መሆን አለበት፡፡

- ማኀበረሰቡን ማሳተፍ እና የባለቤትነት ስሜት መፍጠር፡ የከተማ ሳኒቴሽን ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ህብረተሰቡን ከእቅድ እስከ አፈፃፀም ብሎም ግምገማ ድረስ በጥልቀት ማሳተፍ እና የባለቤትነት ስሜት መፍጠር ሲቻል ነው፡፡ ፡፡ የቤተሰብ ሳኒቴሽን፣ የጋራ እና የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶች አያያዝ፣ መታጠቢያ ቤቶች፣ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ እቃዎች፣ የደረቅ ቆሻሻ የማስተላለፊያ ስፍራዎች፣ የሀይጅን አጠባበቅ ልምዶች ፣ የፍሳሽ ማስተላለፊያ ቱቦዎች አያያዝ እና ሌሎችንም ማኀበረሰቡ በበቂ ሁኔታ ካልተሳተፈባቸው እንዲሁም ስትራቴጂውን በውጤታማነት ለመተግበር የሚያስችሉትን ድርጊቶች በመከወን ላይ ሙሉ ኃላፊነት ለመውሰድ ካልቻለ የስትራቴጂዉ አፈጻጸም ስኬታማ ሊሆን አይችልም፡፡

- ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም - የከተማ ሳኒቴሽን የሚፈልገውን መጠነ ሰፊ የመዋዕለ

ነዋይ ፍሰት መቋቋም የሚያስችል ውጤታማ ዘዴዎችን እና ሂደቶችን መጠቀምን ይጠይቃል፡፡ ቀደም ብሎ ሲሰጠው የነበረው ዋጋም የሚገባውን ደረጃ ያህል የሚመጥን አልነበረም፡፡ ፍላጎቶች የተዳሰሱበትና ሀብት የተመደበበት አካሄድ የስትራቴጂው ቁልፍ ክፍል ነው፡፡

- ፈጠራ እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም- የኢትዮጵያ የከተሞች አወቃቀር በመልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ባላቸው የተፈጥሮ ሀብት ብዛት፣ የስነ ምህዳር ተጋላጭነት፣ አካላዊ አቀማመጥ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ማኅበራዊ ክንዋኔ፣ ሀይማኖት እና ባህል ብዝኃነትን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ የሚፈጠረውን የቆሻሻ ዓይነት እና መጠንእንዲሁም በሳኒቴሽን ሰንሰለቱ ውስጥ የሚያስፈልጉትን ተቋማት ዓይነት እና መጠን የሚወስኑ ናቸው፡፡ የመክፈል ፈቃደኝነት፣ ተመጣጣኝ ዋጋ፣ ያላቸው ቴክኖሎጂዎችን ማስፋፋት በሂደት የማያዳግም መፍትሔ ሊፈለግላቸው የሚገባ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂው አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ፈጠራን፣ ምርምርን እና የተገኙትን ውጤቶች ከልማት ጋር ማያያዝን የሚደግፍ ነው፡፡ ዩኒቨርስቲዎች እና የጥናትና ምርምር ተቋማት ከደንብ አውጪና አስፈጻሚ ተቋማት ጋር በቅርበት እንዲሠሩ ይበረታታሉ፡፡

- የተቀናጀ ከተማ አቀፍ አሠራር - የተቀናጀ ከተማ አቀፍ አሠራር በመላው ከተማ የሚስተዋለውን የሳኒቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ክፍተት ለመገንዘብ የሚያስችል መሣሪያ ነው፡፡ ተፈላጊውን ለውጥ ለማምጣት እንዲቻል፣ በየከተማው እና የከተማ ቡድኖች ውስጥ ያለውን ሁኔታ ከፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ጋር በማገናዘብ ምዘና ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታውን መረዳትም ለከተማዎቹ እድገት የሚያስፈልገውን ሁሉ ለመከወን መነሻ ይሆናል፡፡ ግልጽ እና ዘላቂ የሆነ የመዋዕለ ነዋይ ፍሰት እና ተቋማዊ ለውጥ ማካሄድ ይቻል ዘንድሁሉም ጠቃሚ ሚና የሚጫወቱ ባለ ድርሻ አካላትምክክር ሊያደርጉ ይገባል፡፡ የከተማ ነዋሪዎቹ የሚያስፈልጋቸውን ዓይነት ለውጥ ለማምጣት የከተማ እና የከተማ ማዕከላት አመራሮች ሊሠሩ ያስፈልጋል፡፡ የተቀናጀ ከተማ አቀፍ አሠራር የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጂን ትግበራን በማከናወኑ ሂደት ውስጥ ዋነኛ መርህ ነው፡፡

- በቅደም ተከተል የማቀድ አካሄድ- በከተማ እና በአነስተኛ ከተሞች ደረጃ የሚደረግ

እቅድ ሁሉንም የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ገጽታዎች ለማካተት ይችል ዘንድ ሁሉን አቀፍ ሊሆን ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ ለውጡ በአንድ ምሽት የማይመጣና የማስፈጸሚያ ሀብትም በተፈለገው መጠን ላይገኝ ይችላል፡፡ ስለዚህየትግበራ ዕቅዶች በዐበይት ጉዳዮች ላይ አተኩረው ደረጃ በደረጃ ሊቀመጡ ያስፈልጋል፡፡ እንዲህ ያሉት ቁልፍ ጉዳዮች በቤተሰብ ደረጃ የተሻሻለ የቆሻሻ አያያዝ፣ አነስተኛ ቴክኖሎጂን በሚጠይቅ መሣሪያ አማካኝነት የቆሻሻ አሰባሰቡን ማከናወን፣ ማህበረሰቡን እና ጥቃቅን፣ መካከለኛ እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ማሳተፍ፣ ቆሻሻ የማከሙን ሂደት በልዩ ልዩ ማዕከላት ማከናወን፣ ማጓጓዝ ፣የመሳሰለት ናቸው፡፡

- ዘላቂነት- በከተማ ሳኒቴሽን እቅድ እና ትግበራ ደረጃዎች ላይ ዘላቂነት ከፍተኛ ትኩረትሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ዘላቂነትን ለማረጋገጥ ደግሞ ከኢኮኖሚ ፣ ከቴክኒክ ፣ ከተቋማዊ፣ ከማኅበራዊ እንዲሁም ከአካባቢያዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ትንተና ማካሄድ ይገባል፡፡ ከፋይናንስ ጋር በተያያዘ ትንተና ማድረግ በተመጣጣኝ ዋጋ ሊሰጡ የሚችሉ የሳኒቴሽን አገልግሎቶችን ደረጃ እና የሚያስፈልገውን የዋጋ ቅነሳ ቀድሞ ለመገመት ይረዳል፡

## 3. ራዕይ

መንግሥት ተግባራዊ ለማድረግ ያቀደውን መካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር የመገንባት እቅድ እውን ለማድረግ አስተዋጾ የሚያበረክቱ፣ ለነዋሪዎቻቸው ምቹ፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ጤናማ የከተማ ማዕከላትን ተገንብተዉ ማየት፡፡

## 4. ግብ

የዚህ ስትራቴጂ አጠቃላይ ግብ የከተማ ሳኒቴሽን ከጤና፣ ከአካባቢ፣ ከማኅበረሰብ፣ ከትምህርት እና ከኢኮኖሚ ጋር በተያያዘ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመፍታት የፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻን ከአሰባሰብ እስከ አወጋገድ ድረስ ዘላቂ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት በማዘጋጀት፣ የአገልግሎቶቹን ተቀባይነት በመጨመር፣ የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ሥራዎችን በማስፋት ፣ የዘርፎች ቅንጅትን በማጠናከር እንዲሁም ተቋማዊ ብቃትን በመጨመር እና ደንቦችን ተፈጻሚ በማድረግ የተሟላ የሳኒቴሽን ስርዓትን በመዘርጋት የሕብረተሰቡን ጤናና የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል ነው፡፡

# 5. ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች

ቀጥሎ የተዘረዘሩት ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች ከተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂው እና ስልታዊ የተግባር ምዘናው አፈጻጸም ጋር ተያይዘው በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረዥም ጊዜ የሚፈጸሙ በሚል ተለይተው የተቀመጡ ናቸው፡፡ አፈጻጸማቸውን መደበኛ በሆነ መልኩ ማየትና መገምገም ግቦች ለመከለስ ይረዳል፡፡

- በ2020 የተሻለ የሀይጅን ልምድ፣ የሳኒቴሽን መገልገያዎች ግንባታ እና የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲሁም የሳኒቴሽን አገልግሎት ተቀባይነትን ለማምጣት የሚያስችል ዘላቂ የባህሪ ለውጥን እውን ማድረግ፤

- በአሁኑ ወቅት ስድስት በመቶ የሆነውን በሜዳ ላይ የመጸዳዳት ልማድ በማስወገድ በ2020 ሙሉ በሙሉ በሜዳ ላይ ከመጸዳዳት የጸዱ ከተሞች እንዲኖሩ ማስቻል፣

- በ2020 በየትኛውም ከተማ (አነስተኛ ከተሞችን ጨምሮ) የሚኖሩ አባወራዎች 100 % የተሻሻለ መጸዳጃ ቤት አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ

- በ2025 የዓይነ ምድር ዝቃጭ አወጋገድ ስርዓትን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የማስወገድ፣ የማከም እና የድግመ ዑደትን ሥራ የማከናወን አቅም አሁን ካለበት 70 በመቶ እንዲደርስ ማስቻል (በ2020 ሽፋኑን ወደ 30% ከፍ ማድረግ)

- በ2025 ለአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ በሚያመች መልኩ ፍሳሽን እና ዓይነ ምድርን ወዲያውኑ ወይም ከጥቂት ሂደት በኋላ ማከም የሚያስችሉ በየማዕከሉ የተሰራጩ 1000 የቆሸሸ ውኃ ማከሚያ ስርዓቶች መዘርጋት (በ2020 ቁጥራቸው 200 እንዲደርስ ታቅዷል)፡፡

- በ2025 በመካከለኛና ትልልቅ ከተሞች ከሚፈጠረው ደረቅ ቆሻሻ ውስጥ 50 በመቶ ያህሉን እንዲቀንስ ማድረግ፣መልሶ መጠቀም ወይም በድግመ-ዑደት ጥቅም ላይ ማዋል (በ2020 20% እንዲደርስ ታቅዷል)

- በ2014 በወጣው መመሪያ መሰረት በ2030 ደረቅ ቆሻሻን 100 % ቁጥጥር በሚደረግባቸው የቆሻሻ መቅበሪያ ሥፍራዎች ማስወገድ (በ2020 50% እንዲደርስ ታቅዷል)፡፡

- በ2025 ከሁሉም የጤና ክብካቤ ተቋማት ውስጥ የሚጣውን ቆሻሻ 100% ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማስወገድ (በ2020 95% እንዲደርስ ታቅዷል)፡፡በ2035 በሰዎች፤ ግብርና ስራ እና አካባቢያዊ ስነ ምህዳር ላይ ላይ ጠንቅ በማያስከትል መልኩ ከኢንዱስትሪዎች የሚወጣውን ፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲታከም፣ መልሶ በጥቅም ላይ እንዲውል ወይም እንዲወገድ ማስቻል (በ2020 30% እንዲደርስ ታቅዷል)፡፡

- በአቅም ግንባታ ጥረቶች ግለሰቦችን፣ የተደራጁ ማዘጋጃ ቤቶችን፣ መገልገያዎችን እና የግንባታ አገልግሎት ሰጪ አካላትን በሚያሳትፍ መልኩ እንዲተዳደሩና የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ የሚያስችል "አስተባባሪ አካል"ን በማቋቋም የዘርፉን የክንውን ብቃት ማጠናከር፡፡ ይህ አስተባባሪ አካል በ2020 ሙሉ በሙሉ ይዋቀራል (በ2016 የትብብር አካሄዱ ተዘጋጅቶ የሚጠናቀቅ ይሆናል)፡፡

- የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂው እንዲሁም ስልታዊ የትግበራ እቅዱ አፈጻጸም በውጤታማነት ይካሄድ ዘንድ ተጽዕኖ የማሳደር አቅምን እና አቅርቦቶችን በአመርቂ ሁኔታ መጠቀምን ተግባራዊ ማድረግ

  በ2016 ውጤታማና ተአማኒ የሆነ የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት የሳኒቴሽን መሰረታዊ መረጃ እንዲኖር ማድረግ

# 6. የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂ ይዘቶች

የሚከተሉት 10 ስትራቴጃዊ ይዘቶች የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂን ተግባራዊ ለማድረግ ቁልፍ ናቸው፡፡

- የሳኒቴሽንና ሀይጅን በተመለከተ ማስተዋወቅና አጋር ማፍራት ፣ የሳኒቴሽንና ሀይጅን ገጽታን ማሳደግ፣ ፣የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ሥራዎችን በመተግበር፣የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል

- የደረቅ ቆሻሻ፣ ዓይነ ምድር፣ ፍሳሽ ቆሻሻ እና የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አወጋገድ የአገልግሎት አሰጣጥ

- የተቋማት ሳኒቴሽን
- ድንገተኛ የከተማ ሳኒቴሽን
- የአቅም ግንባታ
- ሙያዊ ፈጠራ፣ ምርምር እና ዕድገት
- ዘርፍ ተሻጋሪ ጉዳዮች
- ለሳኒቴሽን የገንዘብ ድጋፍ እና የክፍያ ተመን
- የተቋማትአደረጃጀት
- የደንብ አፈጻጸም
- ክትትል እና ምዘና

## 6.1. የሳኒቴሽንና ሀይጅን በተመለከተ ማስተዋወቅና አጋር ማፍራት ፤ የሳኒቴሽንና ሀይጅን ገጽታን ማሳደግ፣የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ሥራዎችን መተግበር፣ የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል

ውጤታማ የመረጃ፣ ትምህርት እና ተግባቦት እቅድ ማዘጋጀት፣ የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ማከናወን እና የተሸሻለ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን አገልግሎን ማስተዋወቅ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ ማዘጋጃ ቤቶች እና አገልግሎት ሰጪዎችን ጨምሮ የዘርፉ ባለ ድርሻ አካላት ኃላፊነት ነው፡፡

በኢትዮጵያ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን የባህሪ ለውጥ ማምጣት ላይ የተካሄዱ በርካታ ተሞክሮዎች አሉ፡፡ ሆኖም የነበሩት አካሄዶች በዋናነት የሚያተኩሩት በገጠሩ የሀገሪቱ ክፍል ላይ በተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን የስትራቴጂ ትግበራ እቅድ አማካኝነት የሚሰጡ የተሻሻሉ የአገልግሎት ደረጃዎች ስለሆኑ የንግድ እና ማህበራዊ ገጽታ ለመጠቀም ይቻል ዘንድ እነዚህ አገልግሎቶች ለተጠቃሚዎች ሊተዋወቁ ይገባል፡፡ ማንኛውንም አገልግሎት ከየትኛውም አካል በላቀ ሁኔታ ሊያስተዋውቁ የሚችሉት ደግሞ አገልግሎት ሰጪዎች ራሳቸው ናቸው፡፡ እነዚህ አገልግሎት ሰጪዎችም መገልገያ ተቋማቱ፣ ተቋማትን በባለቤትነት የሚያስተዳድሩት ማዘጋጃ ቤቶች፣ የሕንፃ ተቋራጮች፣ ውክልና የተሰጣቸው ማህበረሰብ ተኮር ኢንተርፕራይዞች እና የግል አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ናቸው፡፡የሀይጅን እና ሳኒቴሽን መሻሻል ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ፤

- የማዘጋጃ ቤት አስፈጻሚዎች እና አገልግሎት መስጫዎች ዘላቂነት ያላቸው አገልግሎቶችን መስጠት እና ማስተዳደር እንዲችሉ ማበረታታት እና ማገዝ

- የከተማ ነዋሪ የሆኑ ማኅበረሰቦች እና አባወራዎች የመጸዳጃ ቤት፣ የዓይነ ምድርና የፍሳሽቆሻሻ ማጠራቀሚያጉድጓድ፣ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች፣ ደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ እና በመሳሰሉ የተሻሻለ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን መገልገያዎች ውስጥ በአገልግሎት አሰጣጥና በአግባቡ መጠቀምን በተመለከተ እንዲሳተፉ ማበረታታትና መምራት

እነዚህና የመሳሰሉት እርምጃዎች በሳኒቴሽን እና ሀይጅን ጉድለት የተነሳ የሚተላለፉ በሽታዎችን ስርጭት በመግታት እና ተፈጥሯዊውን አካባቢ በማሻሻል ጠቃሚነታቸው እጅግ የጎላ ነው፡፡ የጤና ሁኔታን በተጨባጭ እንዲሻሻል እንዲህ ያሉ አሰራሮች እና ቀጣይ የሚያደርጓቸው ባህሪያት የሁሉንም ኅብረተሰብ ክፍል ክብር፣ ይዞታ እና ደህንነት የሚያስጠብቁ ናቸው፡፡

በመሆኑም በአግባቡ የተቀረጸ የተግባቦት እና አገልግሎት ማስተዋወቂያ አካሄድ ለለስትራቴጂውተግባራዊነትቁልፍ ሚና ይኖረዋል፡፡

ጠቃሚ በሆኑት የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ በራሪ ወረቀቶች፣ የህብረተሰቡን ተኩረት የሚስቡ ታሪኮችን በመጠቀም በተግባር የተሞከረ የቅስቀሳ ፓኬጅ ይዘጋጃል፡፡ ፓኬጁም የሀይጅን እና ሳኒቴሽን ጉዳዮች ትግበራን ለመደገፍ እና የአመራር አካላትን ለማነሳሳት በማህበረሰብ ተወካዮች እና በፖሊሲ አውጪዎች መካከል በሚካሄዱ የአንድ ለአንድ ስብሰባዎች እና ቡድን ውይይቶች ወቅት በጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ቅስቀሳው እና ተጽዕኖ ማሳደሩ እንደተመረጠው አካሄድ እና በየደረጃው የሚገኙ (የፌዴራል፣ የክልል እና የከተማ አስተዳደር) ባለ ድርሻ አካላት ዓይነት የሚለያይ ይሆናል፡፡ ተጠቃሚዎች የተሻለ ጥራት ያላቸውን አገልግሎቶች ለመጠቀም እንዲፈልጉ የሚያነሳሱ ፓኬጆችም በጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

ለሳኒቴሽን የሚሰጠውን ትኩረት ለመጨመር እና የአገልግሎቶቹን ተጠቃሚነት ለመስፋፋት ከመረጃ፣ ትምህርት እና ተግባቦት ጋር በተያያዘ ያሉትን መድረኮች ለመጠቀም መሰረታዊ ጥናቶች ይደረጋሉ፡፡ የተግባቦት እቅዶች እና ፈጠራ የታከለባቸው ጽንሰ ሀሳቦች ከተዘጋጁ በኋላ ከሀገር ውስጥና እና በዓለማቀፍ ደረጃ በዘርፉ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡ የተግባቦት እቅዶቹም ቢያንስ የሚከተሉትን ያካተቱ መሆን አለባቸው፡፡

መገናኛ ብዙሃን፡ መገናኛ ብዙሃን መረጃን ለማስተላለፍ ቁልፍ መንገድ እንደ ሆኑ ይታመናል፡፡ በኢትዮጵያ የከተማ ነዋሪዎችን የሚደርሱና በማስተዋወቅ እና በግንዛቤ ማስጨበጥ አንጻር እጅግ ጠቀሜታ ያላቸው ብዙ የኤፍ.ኤም ሬዲዮዎች እና ክልላዊ የቴሌቭዥን ፕሮግሞች አሉ፡፡ ከቤት ውጪ የሚገኙ እንደ የግድግዳ ላይ ስዕሎች፣ በመንገድ ዳር የሚሰቀሉ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች እንዲሁም ባህላዊ ስብሰባዎች/ዝግጅቶችን ማሕበረሰቡን ለመቀስቀስ እና ለማስተማር መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በብዙ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ የተለመዱና ስኬታማ የሆኑ እንደ ቴአትር ዓይነት መሣሪያዎችም በጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ሌሎች በጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የመገናኛ ብዙሀን መሣሪያዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡

- የስልክ የጽሑፍ መልዕክቶች፡- ከኢትዮ-ቴሌኮም ጋር አጋርነትን በመፍጠር በጽሐፍ መልዕክቶች አማካኝነት የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ጉዳዮችን ለሁሉም ነዋሪዎች ለማዳረስ የሚካሄድ ዘመቻን ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ መልዕክቶቹም ለተንቀሳቃሽ ስልክ ተጠቃሚዎች ምላሽ መስጠት የሚችሉባቸውን አማራጮች ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡

- የማኅበራዊ ትስስር ድረ ገጽ፡- የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ አካላት በተለይም ደግሞ ወጣቶችን ለመድረስ እና ዘመቻዎችን አስተዋውቆ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የማህበራዊ ትስስር ድረ ገጾችን መጠቀም ዓይነተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

- የሕትመት ውጤቶች ፡- ጋዜጣዊ መግለጫ እና ጋዜጦች የተግባቦት መሣሪያዎች ሆነው በጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡

- የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የጥሪ ማዕከል፡-የፌዴራልየጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የጥሪ ማዕከል የስልክ መስመር የሆነውን 952 በመጠቀም ከሕዝቡ በሐይጅን እና ሳኒቴሽን ዙሪያ ጠቃሚመረጃ መቀበልና ምላሽ መስጠትይቻላል፡፡

- በተጨማሪም፣ መገናኛ ብዙሀን የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን እድገት እና ውጤታማነት ሊደግፉ ይችላሉ፡፡ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት መፍጠር ፡-በየደረጃው የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ትንተና እና የስትራቴጂ ጽንሰ ሀሳብ ላይ ያተኮሩ ስብሰባዎችን፣ ውይይቶችንለምሣሌ፡-የፓናል ውይይቶችን በየደረጃው ማካሄድ፡፡

በትምህርት ቤቶች እና የማህበረሰብ አቀፍ ፕሮግራሞች ፡-በተለያዩ ከተሞች ምናልባትም በልዩ ልዩ

የሀገሪቱ ክፍሎች የሙከራ ቅኝት የሚካሄደባቸውን ምስሎችን ፣ ሎጎዎች እና የተለመዱ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ማስታወቂያዎችን በመጠቀም የማስተዋወቅ ስራዎችን መስራት፡፡

የሳኒቴሽን ግብይት፡ ለሳኒቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ የሚሆኑ ፈጠራ የታከለባቸው አዋጭነት ያላቸው ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ ማድረግ ፡፡

የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያዎች ፡-በተለያዩ ቋንቋዎች የተሰሩ ስራዎችን በሀገርአቀፍ ደረጃ ታወቂ የሆኑ ሰዎችን በመጠቀም በመገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ እንዲደርሱ ማድርግ፡፡

ታዋቂ ሰዎችን እንደ አምባሳደር መጠቀም፡ታዋቂ ሰዎችን የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ቀዳሚ አራማጆች በማድረግ የተለያዩ መድረኮችንና ዘመቻዎችን ተጠቅመውሰለ ሳኒቴሽን እና ሀይጅንን እንዲያስተዋውቁ ማድረግ፡፡

ማበረታቻ፡ ለውጥን ዘላቂ የማድረጊያው ዋነኛ ዘዴ በመደበኛነት መዋቅሩን ተከትሎ የሚመጣን በግልጽ የሚታወቅ እና በተዘዋዋሪ የሚገኘ መረጃ እንዲሁም ግብረመልስ ለህዝብ ግልጽ ማድረግ በሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲዎች፣ የግሉ ዘርፍ አገልግሎት ሰጪዎች እንደሁም አባዎራዎች እና ማኅበረሰቦች ዘንድ ተመሳሳይ የሆነ ተጽእኖ በመፍጠር ትግበራውን ዘላቂነት ያለው ማድረግ ነው፡፡ ማበረታቻ ዘላቂነት ያለው ስራ እንዲሰራ በማነሳሳት መሻሻል እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ከተማዎችን፣ የከተማ ማዕከላትን እንዲሁም የማዘጋጃ ቤቶችንለምሳሌ፡- ለሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች እንዲሁም ተያያዥነት ላላቸው የውሀ ፕሮጀክቶች የሚሆን የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ ለመስጠት ቃል መግባት ከተሞች እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲደራጁና አመርቂ ውጤት እንዲያሳዩ ያደርጋል፡፡

ውጤታማ የሆነው የገጠሩ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምም ሆነበመጠናከር ላይ የሚገኘው የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም እንዲሁም ሌሎች ፕሮግራሞችና አደረጃጀቶች የማህበረሰብ የባህሪ ለውጥ ተግባቦት እና የአገልግሎት አሰጣጥን የማስተዋወቅ ትግበራዎችን በማሳደግ እና በመመዘን አንጻር ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ በማኅበረሰብ ደረጃ ከሚካሄዱ ፕሮግራሞች በዋናነት ከሚጠቀሱት መካከል የሆነው የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ነው፡፡ በመሆኑም የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙዎች ከሴቶች የልማት ቡድን አባላት እና ከሌሎች ዘርፎች እና ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ቤተሰቦች ውሀን አከመው ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማከማቸታቸውን፣ የተሻሻለ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ተቋማት በከተማ ነዋሪዎች እና ማህበረሰቦች ዘንድ መኖራቸውን

እና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸው ይከታተላሉ፤ በሳኒቴሽንና ሀይጂን ላይ ፓኬጆቹን መሰረት አድርገው የተሟላና የጤና አጠባበቅ ትምህርት እና መረጃ ይሰጣሉ፡፡

ቀጥሎ የተዘረዘሩት በአሁኑ ወቅት በስራላይ የዋሉ ወይም የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂው አካል እንዲሆኑ የታቀዱ የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አካሄድ ስልቶች ናቸው፡

- የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን እና የጤና ልማት ሠራዊትን ማጠናከር እንዲሁም የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሀዶችን መልሶ ማዋቀር በጤናው ዘርፍ የከተማውን ሕዝብ የጤና ችግሮች ማስወገድ

- የሳኒቴሽንን ገጽታ በብሔራዊ ደረጃ ከፍ ማድረግ እና አገልግሎቶቹን ለማስተዋወቅ የሚያስችሉ ዘመቻዎችን ማካሄድ፡፡ የሀይጅን ልምዶችን እና ያሉትን የሳኒቴሽን መገልገያ ተቋማት በአግባቡ መጠቀምን የሚያስተዋውቁ ስራዎችን ማዘጋጀትና ማስተዋወቅ፡

- ያሉትን ወይም በቀጣይነት የሚጀምሩትን የተሻሻሉ የአገልግሎት ደረጃዎች የንግድ እና ማኅበራዊ ጥቅም ማስተዋወቅ እና ግንዛቤ ማስጨበጥ፡፡ እነዚህ አገልግሎቶች በሁሉም የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ለሚገኙ ውሳኔ ሰጪዎች እና ደንበኞች ሊተዋወቁ ስለሚያስፈልግ ከላይ ከተጠቀሱት የባህሪ ለውጥ እና የማስተዋወቅ መሣሪያዎች መካከል የተወሰኑት ወይም ሁሉም በጥቅም ላይ ማዋል፡፡

- ለተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂእንዲሁም ለከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምጋር በተያያዘ በቀጣይነት ሊዳሰሱ ወይም በጥቅም ላይ ሊውሉ የሚገባቸው መድረኮች የሚከተሉትን ያካትታል፡

  - ማኅበረሰብ መር የከተማ አካባቢያዊ ሳኒቴሽን
  - ማህበሰብ መር አጠቃላይ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን
  - ትምህርት ቤት መር አጠቃላይ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን
  - ተቋም መር አጠቃላይ ሳኒቴሽን

- የማህበረሰብ ውይይት
- የቡና ስነ ስርዓት
- የጤና ክበባት
- ንጹህና ደህንነታቸው የተጠበቀ የጤና ተቋማት

## 6.2. የደረቅ ቆሻሻ፣ ዓይነ ምድር ፣ ፍሳሽ ቆሻሻ እና የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አወጋገድ የአገልግሎት አሰጣጥ

### 6.2.1. የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ

የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ትግበራ አሁን ያለውንና እና ወደፊት ይኖራል ተብሎበሚገመተው ቆሻሻ መጠን እና ዓይነት ፣ ደጋፊ የሆነ የፓሊሲ ማዕቀፍ ፣ የማቀድን/የአሰራር ስርዓት የማዘጋጀትን፣ እውቀት እና ችሎታ፣ ለለአካባቢው ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ መጠቀምንእንዲሁም ትግበራውን ለመደገፍ የሚውል የገንዘብ አቅምን በተመለከተ አጠቃላይ መረጃን የሚፈልግ ነው፡፡ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ እና አያያዝ አወጋገድ ትግበራ ከዚህ በታች በቀረበው የቆሻሻ አወጋገድ ቅደም ተከተል ላይ የተመሠረተ ነው፡

በይበልጥ ተመራጭ የሆነው




በጥቂቱ ተመራጭ የሆነው

የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ቆሻሻው በተቻለ መጠን እንዲቀንስ፣ በድግመ ዑደት እንዲቀየርእና መልሶ ለመጠቀም የሚያስችል የተቀናጀ ዘዴ ነው፡፡ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ የሚከተሉትን ዋና ዋና ክፍሎች ያካትታል፡

- **የቆሻሻ መጠን እና ይዘትን መለየት :-** በተገቢ የሆነ እቅድ እና አተገባበር እንዲኖር ለማስቻልየቆሻሻውን ምንጭ ለይቶ ማውጣት፣ የልዩ ልዩ ቆሻሻዎችን(ከኢንዱስትሪ፣ የማዘጋጃ ውኃ እና ፍሳሽ፣ ንግድ፣ ግብርና፣ እና ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎችንጨምሮ) መጠን የመለየት ስራ የወደፊት የቆሻሻ መጠን ትንበያዎችን አካቶ በያንዳንዱ ከተማ ሊካወናን ይገባዋል፡፡
- **ማስተዋወቅ :-** ቀጣይነት ያላቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአቅም ግንባታ ስራዎችንበከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም እንዲተገበሩ እንዲሁም በአገልግሎት ሰጪዎች (ማዘጋጃ ቤት፣ ውኃ እና ፍሳሽ አገልግሎት፣ተባባሪ ተቋማት እና ወኪሎች) አማካኝነት የማስተዋወቅ ስራ ሊሰራ ይችላል፡፡
- **ቆሻሻን ከምንጩ በአግባቡ ማከማቸት:-**ቆሻሻን በአግባቡ ማከማቸት እና የመለየት

ሥራ ከምንጩ መጀመር አለበት፡፡ ቆሻሻ አመንጪዎችሌላው ቢቀር ሁለት የተለያዩ ማጠራቀሚያዎችን በመጠቀም በስባሽ የሆነና ያልሆነን ቆሻሻበመለየት ሊያከማቹ ይገባል፡፡ ይህንንም በመንግስት እና የግሉ ዘርፍ አገልግሎት ሰጪዎች በኩል አስፈላጊውን መገልገያ ቁሳቁስ በማቅረብ ማሳካት ይቻላል፡፡ ይህም ሥራ በአንድ በተለይም ብዙ ሕዝብ በሚኖርበት ስፍራ በሚገኙና በተመረጡ ቤተሰቦች ከተሞከረ በኋላ ሊስፋፋ ይችላል፡፡ ቆሻሻን ለማጠራቀም የሚውለው ዘዴ አስተማማኝ፣ ጤናማ፣ፅዱ እና ወጪ ቆጣቢ መሆን አለበት፡፡

- የመጀመሪያ ደረጃ የቆሻሻ አሰባሰብ፡ በአብዛኞቹ ከተሞች የመጀመሪያ ደረጃ የቆሻሻ አሰባሰብ (ከቤት ወደ የጋራ ቆሻሻ ማከማቻ ገንዳ ወይም ቆሻሻ አንሺ መኪናዎች) የሚካሄደው በአነስተኛ፣ጥቃቅንና መካከለኛ ኢንተርፐራይዞች አማካኝነት ነው፡፡ ነገርግን ስራው በአብዛኛው የሚተገበረው ውል ሳይፈጸም ስለሆነ በአሰራር ሂደቱ በኃላፊነት የሚጠየቅ አካል ያለም፡፡ ደግሞም የወጣውን ወጪ የመሸፈኑ ሁኔታ እምብዛም አጥጋቢ አይደለም፡፡ ይህንን ሁኔታ ለመቀየር አነስተኛ፣ጥቃቅን እና መካከለኛ ኢንተርፐራይዞች ያላቸው ጥቅም የማይናቅ ቢሆንም ስራውን ለማሻሻል ልዩ ልዩ እርምጃዎችን መውሰድ ተገቢ ይሆናል፣ከነዚህም መካከል፣

  - አቅምን ለማሻሻል እና ወጪውን ለመሸፈን እንዲሁም ተጠያቂነትን ለመጨመር ግልፅ የክንውን ወሰን እና ስምምነቶችን ማበጀት፤
  - የስራውን ሁኔታ እና የስራውን ውልበ ተመለከተማብራሪያ መስጠት፤
  - በጤና እና በደህንነት ዙሪያ ስልጠና መስጠት፤
  - በሥራ ወቅት አስፈላጊ የግል ደህንነት መጠበቂያ እና የስራ መሳሪያዎችን ማቅረብ
  - በተሰበሰበው ቆሻሻ ክብደት ወይም ይዘት ላይ ተመስርቶ ክፍያ መፈጸም፡፡ ይህ እርምጃ መውሰድ አነስተኛ ፣ጥቃቅን እና መካከለኛ ኢንተርፐራይዞች ሥራቸውን ብዙ ክፍያ በሚሰጧቸው ቤተሰቦች ላይ በማተኮር ፋንታ በተከለለላቸው አካባቢ ሁሉ እንዲሰሩ ስለሚያስችል የበለጠ ቆሻሻ

አንዲሰበስቡ ያበረታታል፡፡

- በእጅ በሚገፋና በአህያ የሚሳቡ ጋሪዎችን እና ባጃጆችን በአጭር ርቀት ቆሻሻን ከየቤቱ ወደ መዘዋወሪያ ጣቢያዎች ለመሰብሰብ መጠቀም ተገቢ እና ወጪ ቆጣቢ ቢሆንም ቅልጥፍናን ለመጨመር እና አደጋን ለማስወገድ መገልገያው መሻሻል ሊኖርበት ይገባል፡፡

- ረጅም ርቀት ለማጓጓዝ እና ከንግድ አካባቢዎች ለሚሰበሰቡት ቆሻሻዎች በሞተር የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን መጠቀም የበለጠ ተስማሚ እና ወጪ ቆጣቢ ናቸው፡፡

- ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች በሚገኙበት አካባቢ ቆሻሻን መሰብሰብ መጠነኛ የመንግስት ድጎማ ሊደረግበት የሚችል ቢሆንም፣ ለንግድ አካባቢዎች የሚደረገው የቆሻሻ ማሰብሰብ አገልግሎት ግን ሙሉ በሙሉ ወጪን የሚሸፍን ሊሆን ይገባዋል፡፡

- መልሶ-መጠቀም :- በኢትዮጵያ ቆሻሻን እና የወዳደቁ ምርቶችን መልሶ-መጠቀም መደበኛ የሥራ ዘርፍ ተደርጎ በማይቆጠረውና ቃል በቃል “ቆርቆሮ-ያለው” ተብለው በሚጠሩ ሰዎች አማካኝነት ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ይህ አገልግሎትም ተገቢ የገበያ ቦታዎች እና ስልጠናዎችን በመስጠት ሊደገፍ ይገባዋል፡፡ በቅርቡ በተወሰኑ ከተሞች ብረታ ብረቶችን፣ፕላስቲኮችን፣ጠርሙሶችን እና ወረቀቶችን መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል ስራ ሲሰራነበረ፡፡ይህን አሠራር ለማጠናከር በመጀመሪያ ቆሻሻውን ለሚሰበስቡ ሰዎች ሥልጠና፣ የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ፣እንዲሁም ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ከሚያውሉ ድርጅቶች ጋር በማገናኘት ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ ጥናቶች እንዳሚያሳዩት በኢትዮጵያ ትላልቅ እና ትናንሽ ከተሞች ውስጥ የሚመነጨው አብዛኛው ቆሻሻ በስባሽ እንደመሆኑ መጠን በቤተሰብ፣ አነስተኛ፣ጥቃቅን እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም በማዘጋጃ ቤትደረጃ ቆሻሻውን ወደ ማዳበሪያ ለውጦ የመጠቀም ተግባር ሊበረታታ ይገባዋል፡፡ ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ኬሚካላዊ የሆኑ ማዳበሪያዎችመጠን መቀነስ የሁለቱንም ማለትም አካባቢያዊ ምጣኔ ሀብት እና ሀገራዊ ምጣኔ ሀብት መሻሻልን እንዲመጣ ያግዛል፡፡ ነገር ግን ማዳበሪያ ማዘጋጀቱ

ደረጃውን ሊጠብቅና በቴክኖሎጂ የታገዘ ሊሆን ይገባዋል፡፡ቆሻሻ መለየቱ በቤት ለቤት ደረጃ ሊከናወን የሚገባው ሲሆን በማዘዋወሪያ ጣቢያዎቹ ጊዜያዊ ማከማቻ ሊቀርብ ይችላል ፡፡ቆሻሻን ወደ ማዳበሪያነት የመለወጡ ስራ ከከተማ ማስዋብ እና አካባቢያዊ የግብይት ስርዓት ከሚፈጥሩ የግብርና ስራዎች (የአበባ እርሻዎችን ጨምሮ) ጋር በማያያዝ ማስተዋወቅ ይቻላል፡፡ ቆሻሻን ወደ ሀይል መለወጥ ምናልባትም በትልልቅ ከተሞች ወይም በክላስተር በተደራጁ ትናንሽ ከተሞች ውስጥ አዋጭ ሊሆን ይችላል፡፡

- ሁለተኛ ደረጃ የቆሻሻ አሰባሰብ/ማጓጓዝ፡-የሁለተኛ ደረጃ የቆሻሻ አሰባሰብ በአነስተኛ እና ጥቃቅንኢንተርፕራይዞች፣በግል የስራ ተቋራጮች ወይም በማዘጋጃ ቤት አማካኝነት መካሄድ አለበት፡፡የሁለተኛ ደረጃ የቆሻሻ አሰባሰቡ ለዚሁ ተግባር ተለይተው በተዘጋጁ እና አስፈላጊው መሣሪያ በሚገኝባቸው የማስተላለፊያ ጣቢያዎች ውስጥ ለሁለቱም አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ሰብሳቢዎች በሚያመች የጊዜ ሰሌዳ አማካኝነት፣ አካባቢውን በማይበክል እና ተጽዕኖ በማያመጣ መልኩ መካሄድ ያለበት ሲሆንእንዲህ ባለ ሁኔታ መከናወኑ ቆሻሻውን ለማከማቸት ወይም ለማንሳት በሚደረግ መጠባበቅ ውስጥ አቅም እና ጊዜ እንዳይባክን ያደርጋል፡፡

በማዘዋወሪያ ጣቢያዎች እና የመጨረሻ  የቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ መካከል ያለው ርቀት ተገቢው መሣሪያ በተገጠመላቸው እና ረዥም መንገድ የማያዳግታቸው መኪናዎች ሊከናወን እንደሚገባ ይጠበቃል፡፡የተሻለ አቅም፣ደህንነቱ የተጠበቀ አስተማማኝ ክንውን፣ አካባቢያዊ ተጽዕኖ እንዲሁም የወጪ ሽፋን ሊሻሻሉ ይገባል፡፡

የማጓጓዝ እና የመጨረሻ የማስወገድ ሂደት አገልግሎቱን በአቅራቢያው በሚገኙ ትላልቅ እና ትናንሽ ከተሞች ውስጥ በማስፋፋት የምጣኔ ሀብት ዕድገት ሊገኝበት ይችላል፡፡ ለመሰብሰብ /ለማጓጓዣነት በጥቅም ላይ የሚውለው መሣሪያ በከተሞቹ አደረጃጀት መሠረት ሊዘጋጁ ያስፈልጋል፡፡

- ትናንሽ ከተሞች (ቡድን 5)፡ከእነዚህ ከተሞች የሚገኘው የቆሻሻ መጠን ዝቅተኛ እንደሚሆንና የማስወገጃ አካባቢውም እንደማይርቅ ይገመታል፡፡ ዋጋን ያገናዘቡ የመሰብሰቢያ አማራጮችን (ቴክኖሎጂዎችን) ማለትም እንደየ አህያ /የፈረስ/ የበቅሎጋሪዎችን መጠቀም ተስማሚ ሊሆን ይችላል፡፡ የማዘዋወሪያ ጣቢያዎች መኖር በትናንሽ ከተሞች አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡ የጋራ የማጠራቀሚያ የቆሻሻ ገንዳዎችን

መጠቀም ለአሠራር ላይመች ይችላል፣ በተጨማሪም ቆሻሻን የመለየት ሥራን የበለጠ አስቸጋሪ ሊያደርገው ስለሚችል የተሻለውና ወጪ ቆጣቢ የሆነው አማራጭ ከመጀመሪያ መሰብሰቢያው በቀጥታ ወደ መጨረሻ ቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ ማጓጓዝ ነው፡፡ በእነዚህ ከተሞች የመሰብሰቡ እና የመጨረሻ የማስወገድ ሂደት በጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች አማካኝነት ሊተገበር የሚችል ሲሆን፣ግልፅ በሆነ የሥራ ውል ስምምነት እና ወጪውን መሸፈን በሚያስችል ክፍያ አማካኝነት ሊከናወን ይገባል፡፡ አነስተኛ ከተማ በመሆኑ ብቻ ከላይ የተገለጹት የስልጠና እና የንግድ ስራ እቅዶች መጓደል የለባቸውም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፣ በመጨረሻ የማስወገጃ ቦታ የሚኖረው ደህንነትን የመጠበቅ፣ ጤና እና አካባቢ ላይ ተፅእኖን ማሳደር እና ወጪ የመሸፈን ሁኔታም ሊሻሻል ይገባል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች እና ገደቦች ባሉበት ሁኔታ በማስፋፊያ አማካኝነት የሚገኝ የምጣኔ ሀብት መሻሻል እና በተደራጁ ትልልቅ እና አነስተኛ ከተሞች ውስጥ አገልግሎት የመስጠቱ ጥቅም ግልጽ ይሆናል፡፡

- መካከለኛ (ቡድን 4) እና ሰፈፊ (ቡድን 3) ከተሞች፡-በእነዚህ ከተሞች የሚፈጠረው የቆሻሻ መጠን ከፍ ያለ ሲሆን የማስወገጃ ቦታው ራቅ ያለ ሊሆን ይችላል፡፡ ባለ ሞተር ተሽከርካሪዎችን ለሁለተኛ ደረጃ ቆሻሻ ማጓጓዝ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

- ለሁሉም ከተሞች ተግባራዊ እንደሚሆነው ሁሉ፣ ግልፅ በሆነ የሥራ ውል ስምምነት እና ወጪ ሸፋኝ ክፍያ አማካኝነት ሊከናወን ይገባል፡፡ በተጨማሪም፣ በስራው ዙሪያ የሚሠጥ ስልጠና፣ የንግድ ስራ እቅድ፣የጤናና የስራ ደህንነት በቸልታ ሊታለፉ አይገባም፡ ፡በመጨረሻ የማስወገጃ ቦታ የሚኖረው ደህንነትን የመጠበቅ፣ ጤና እና አካባቢ ላይ ተፅእኖን የሚያሳድሩ ሁኔታዎችን ለመካላከል ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ለአነስተኛ ከተሞች እንደሚሆነው ሁሉ፣ እነዚህ ሁኔታዎች እና ገደቦች ባሉበት ሁኔታ በማስፋፊያ አማካኝነት የሚገኝ የምጣኔ ሀብት መሻሻል እና በክላስተር በተደራጁ ትልልቅ እና አነስተኛ ከተሞች ውስጥ አገልግሎት የመስጠቱ ጥቅም ግልጽ ይሆናል፡፡

- ትልልቅ (ቡድን 2) እና ግዙፍ ከተሞች (ቡድን1)፡- በእነዚህ ትላልቅ ከተሞች የሚሰበሰበው የቆሻሻ መጠን ከፍተኛ ስለሆነ የማስወገጃ ቦታውም ሩቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ እንደ ቆሻሻ ማንሻ ማሽን ያላቸው ወይም ለዚሁ ተብለው የተዘጋጁ የመሰብሰቢያ መኪናዎችን

መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ አብዛኞቹ ከተሞች ባለ ሞተር ተሽከርካሪዎችን ለማስተላለፍ የሚያስችሉ የጥርብ ድንጋይ መንገዶች ስላሏቸው የቆሻሻ ዓይነቶችን መለየቱ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እየተደረገ የጋራ ማጠራቀሚያ ገንዳዎችን መጠቀም አማራጭ ሊሆን ይችላል፡፡

- የመንገድ ጽዳት፡- የመንገድ ላይ ጽዳት በማዘጋጃቤትወይም በጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች አማካኝነት ግልጽ የስራ ውል ስምምነት ባለበት እንዲሁም ቆሻሻው የሚሰበሰበው የሚገፉና ክዳን ባላቸው ተሽከርካሪዎች አማካኝነት መሆኑ ተረጋግጦ ሊከናወን ይገባል፡፡ የቤት ለቤት ቆሻሻ አሰባሰብን በተለመለከተ ስልጠና፣ የንግድ ስራ እቅድ እና በሥራ ላይ የሚከሰት ጉዳትን የሚከላከል መሣሪያ በጥቅም ላይ ማዋሉ አስፈላጊ ነው፡፡ የመንገድ ማጽዳት ሥራው በዚያው አካባቢ የቤት ለቤት ማሰባሰብን በሚሰሩ ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች አማካኝነት ሊተገበር ይችላል፡፡

- የመጨረሻ የቆሻሻ አወጋገድ፡- ከዚህ በታች እንደተገለጸው በትላልቅ እና ትናንሽ ከተሞች መካከል የሚደረገውን የቆሻሻ አወጋገድ አገልግሎት ክላስተር ማጠናከር ለስራው መስፋፋት ጥቅም እንደሚኖረው ይታወቃል፡፡ በአጠቃላይመርሆቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ትናንሽ (ቡድን 5) እና መካከለኛ ከተሞች (ቡድን 4) ፡-በነዚህ ከተሞች የሚፈጠረው ቆሻሻ ውስን እና የህብረተሰቡ ግንዛቤም ዝቅተኛ ስለሚሆን በአንድ ጊዜ በየሜዳው ቆሻሻን ከመጣል ወደ ቆሻሻን በሳኒተሪ ላንድ ፊል ቴክኖሎጂ ወደ ማስወገድ መሸጋገር ሊከብድ ይችላል፡፡ ስለዚህ የአወጋገድ ሂደቱን ማሻሻል በሂደት እየተጠናከረ ቢሄድ ይመረጣል፡፡ የመጀመሪው እርምጃ የማከማቻ ቦታውን በማጠር እና በቀላሉ ቆሻሻን ማጓጓዝ በሚቻልበት መንገድ መገንባት ነው፡፡ቆሻሻውን በአፈር መሸፈን (በቀላል እና ለመጠቀም ቀላል በሆኑ ማሽኖች አማካኝነት ሊከወን የሚችል) ብክለትን ለመቀነስ እና የአካባቢውን እይታ ለማሻሻል ይረዳል፡፡ በማስወገጃ አካባቢ ቆሻሻን ወደ ማዳበሪያ ለመለወጥ ማበስበሻ ስፍራዎችን ማዘጋጀት የሚወገደውን የቆሻሻ መጠን ለመቀነስ እና ተገቢውን ቁጥጥር የሚደረግበት ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታ ለረዥም ጊዜ አገልግሎት የሚሰጥ እንዲሆን ያስችላል፡፡

- ትላልቅ ( ቡድን 2)እና ግዙፍ (ቡድን1)ከተሞች ፡- በእነዚህ ከተሞች የሚሰበሰበው የቆሻሻ መጠን ከፍያ ሲሆን የማስወገጃው ቦታም በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ ሊሆን ይችላል፡፡

ስለዚህ የአካባቢውን ፅዳት ለመጠበቅ በማዘጋጃ ቤት አልያም ልዩ ፍቃድ ባላቸው ጥቃቅን፣ መካከለኛና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አማካኝነት ቆሻሻውን "በሳኒተሪ ላንድ ፊል" ማስወገድ ይቻላል፡፡ቆሻሻን" በሳኒተሪ ላንድ ፊል" የማስወገድ ስራ መገልገያ መሳሪያዎችን እና የሰው ኃይልን በከፍተኛ ሁኔታ የሚፈልግ የዕለት ተዕለት ክንውንስለሚጠይቅ፣ እንደዚህ ያለውን የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት ተግባራዊ ከማድረግ በፊት አሠራሩን በዝርዝር ማቀድ ያስፈልጋል፡፡ ሥራዎቹን አቅም ባገናዘበ ሁኔታ ለማከናወን እጅግ ከፍተኛ መጠን ያለው ቆሻሻ የሚወገድበት ሁኔታን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

አራቱ ቆሻሻን "በሳኒተሪ ላንድ ፊል" የማስወገጃ ደረጃዎች ቦታ መምረጥ፣ ቦታን ማዘጋጀት፡ ትግበራ እና የድህረ-መዝጊያ አያያዝ ናቸው ፡፡

1. ቦታ መምረጥ፡ ለሳኒተሪ ላንድ ፊል ቦታ በሚመረጥበት ወቅት መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ስነምድር እና የውኃ መገኛዎች፣ የመሬትአጠቃቀም፣ቆሻሻከሚመነጭበት ቦታ የሚኖረውርቀት፣ቦታውን ከነዚህ ማዕከሎች ጋር የሚያገናኙ የመጓጓዣ መስመሮች እንዲሁም ከመኖሪያ ሰፈሮች እና የአየር ማረፊያ ያለውን ርቀት ግምት ውስጥ በማስገባት በጥንቃቄ ሊመረጥ ይገባዋል፡፡

2. ቦታ ማዘጋጀት ፡- ቆሻሻን በሳኒተሪ ላንድ ፊል የማስወገድ ሂደት በሚነደፍበትና በሚገነባበት ጊዜ አያሌ ጉዳዮችን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡ በቅድሚያ ሊታሰብባቸው ከሚገቡ ጉዳዮች መካከል የውኃ  እና የአካባቢ ብክለት፣ጤና እና በሥራው ሂደት የደህንነት መጠበቅ እና የአተገባበር ብቃት ናቸው፡፡ከቆሻሻው ውስጥ የሚወጣው የተበከለ ውኃ ከውሀ ምንጭ ጋር እንዳይገናኝ የሚከላከል ውሀ የማያሰርግ ከሸክላ የሚሰራ መከለያ ከማጠራቀሚያው በታች ሊዘጋጅ ወይም ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገባ ሸክላ፣ ፕላስቲክ ንጣፍ፣ "ቢቱሚን" ወይም ከአፈር በተዋሀደ ቤንቶናይት አማካኝነት ሊሰራ ይችላል፡፡ በአንፃራዊ መልኩ ንፁህ ውኃ ብቻ ወደ አካባቢው እንዲለቀቅ ውሀ በማያሰርገው መከለያ አማካኝነት ተይዞ የሚቆየው ጥሌት በፍሳሽ ማስወገጃ መስመር አማካኝነት ተጠራቅሞ መታከም ያስፈልጋዋል፡፡

በተቻለ መጠን መሬት እያጠበ የሚፈስ ውሀ ዳገታማ ስፍራዎች ላይ በሚቆፈር ጉድጓድ እና በመሳሰሉ ዘዴዎች ወደ ቆሻሻው እንዳይቀላቀል በመከላከል የሚበከለውን የውሀ መጠን መቀነስ ይቻላል፡፡

3.ትግበራ ፡- "በሳኒተሪ ላንድ ፊል" በመጠቀም ቀጣይነት ባለው መልኩ ቆሻሻን መጠቅጠቅ ተጨማሪ ቦታ ከመስጠቱም ባሻገር የመበስበስ ሂደቱን ያፋጥናል፡፡ "በሳኒተሪ ላንድ ፊል" ውስጥ የሚጨመሩት

ንቆሻሻዎች አይነት በጥብቅ ለመቆጣጠር የሚያስችል ከፍተኛ የአሠራር ሂደትን የሚያስጠብቅ አስተዳደር ይፈልጋል። በሳኒተሪ ላንድ ፊል” ስፍራው ለግልጋሎት ከሚውሉ መሣሪያዎች መካከል የአፈር መግፊያ፣ማንሻ፣ የቁፋሮ እና የጭነት ተሽከርካሪዎች ይጠቀሳሉ፡፡መደበኛ የዕለት ተዕለት ተግባራት ቆሻሻዎቹን መበታተን፣ በማመቅ ማሳነስ፣ መደልደል እና በየዕለቱ የታፈገውን ቆሻሻ ስስ የአፈር ሽፋን ማልበስ ናቸው፡፡

4. የሳንድ ፊሉ አገልግሎት ዘመን ሲያበቃ፡- ቦታው ተጨማሪ የቆሻሻ ክምችት መያዝ በማይችልበት ጊዜ ወደ ተፈጥሯዊ ገጽታው ሊመለስ ይገባዋል፡፡ቆሻሻው ወደ ማዳበሪያነት መለወጡን ስለሚቀጥል “ሜቴን” እና ጥሌቶችን ማመንጨቱ የማይቀር ስለሆነ ቁጥጥር ሊደረግበት እና አስፈላጊውየማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

### ቆሻሻን መቀነስ፣ መልሶ መጠቀም እና እንደገና በድግመ-ዑደት ጥቅም ላይ ማዋልን መተግበር

የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ስትራቴጂ ውስጥ መቀነስ፣መልሶ መጠቀም እና ድግመ-ዑደት መካተታቸው ጠቀሜታው እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ሦስቱን ሂደቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉት እና ሌሎችም ዝግጅቶች ያስፈልጋሉ፡፡

- ጥቅል የሆኑ የቆሻሻ ማስወጋገድ ተግባራትን በማከናወን እና ውስን የሆናውን ሀብት በተሻለ ሁኔታ ለመጠቀም እንዲሁም ትርፋማ ለመሆን ሥራውን በክላስተር ማደራጀትና ማከናወን
- የጥቃቅን እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ደረጃ እና የንግድ ክህሎት በማሳደግ ሶስቱን ሂደቶች በመተገበር የገንዘብ አቅማቸውን ማሳደግ እንዲችሉ ማድረግ
- መጠነ ሰፊ የሆነ መልሶ የመጠቀም አሠራርን እንዲከተሉ ማበረታት /ለምሳሌ፡- የቤት ዕቃዎችን እና ጥቅም ላይ ከዋሉ ፕላስቲኮች የተሰሩ ልብሶችን መጠምን ማበረታታት/ ደንብን ተከትለውም ሆነ ሳይከተሉ ለተዋቀሩ ኢንተርፕራይዞች ማበረታቻ እና ድጋፍ ማድረግ፡፡
- እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ነገሮችን በሚያመርቱ እና የሚጠቀሙ አካላት መካከል ስምምነት እንዲኖር ማድረግ

### አደገኛ/ከኢንዱስትሪዎች የሚወጡ ደረቅ ቆሻሻዎች አያያዝ

- አደገኛ/ከኢንዱስትሪ የሚወጡ ደረቅ ቆሻሻዎች የሚባሉት ከባድ ብረታ ብረቶች (heavy metals)፣ ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች፣ ከኤሌክትሮኒክ ምርቶች ጋር የተያያዙ ቆሻሻዎች እና ከኢንዱስትሪ የሚወጡ ቆሻሻዎችን ኑ ከሚያስከትሉት የጤና ችግር አንጻር ከሌሎች ቆሻሻዎች በተለየ መልኩ የሚያዙና የሚወገዱ ይሆናሉ፡፡
    - ደንቦችን ተፈጻሚ እንዲሆኑማድረግ፣ በፋብሪካው ውስጥ ቆሻሻ በተገቢው መልኩ እንዲለይ እና እንዲያዝ እንዲሁም ቆሻሻዎች እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉበት ሂደት እንዲፈጠር ለማበረታታት የገንዘብ መቀጫ እንዲኖር ማድረግ እና ችግሩን ለማስወገድም ከፍ ያለ ክፍያ እንዲከፍሉ ማድረግ ፡፡
    - በእነዚህ የቆሻሻ ዓይነቶች አያያዝ ወቅት ብክለት ያስከተለው አካል ላስከተለው ጉዳት የሚሆን ካሳ ሙሉ በሙሉ እንዲከፍል ማድረጉ የበለጠ ተመራጭነት አለው፡፡ የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮም የሚያሳያውም ይህንኑ ነው፡፡ኢንዱስትሪዎቹ ለቆሻሻ አሰባሰብ እና አወጋገድ ኃላፊነትን ወስደው ከማዘጋጃ ቤት ወይም ከአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ጋር የስራ ውል መፈራረም ይገባቸዋል፡፡ በተጨማሪም እነዚህን ቆሻሻዎች በማስወገዱ ሂደት ውስጥ የሚኖረውን ወጪ ሙሉ በሙሉ መሸፈን ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 6.2.2. የዓይነ-ምድር ዝቃጭ አወጋገድ

መፀዳጃ ቤት መገንባት የእያንዳንዱ ቤተሰብ ኃላፊነት ቢሆንም ንፅህናው የተጠበቀ ሆኖ እንዲሰራ ማስተማር፣ ማስተዋወቅ፣ ደረጃ ማውጣት እና ማስፈጸም የተላላፊ በሽታዎችን ስርጭት ይገታል፡፡ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ለሁሉም ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ እንዲሁም ከገጸ ምድርና ከርሰ ምድር ውሃ አያያዝ ጋር የማይጋጭ ዓለም አቀፋዊ የመፀዳጃ ቤት አሰራር መርህ የለም፡፡ በዚህም ምክንያት ለተለያየ ነባራዊ ሁኔታ አመቺ የሆኑ ልዩ ልዩ የመፀዳጃ ቤት አሰራር ዘዴዎች ያስፈልጋሉ፡፡

እነዚህ ዘዴዎች የሰው ዓይነ ምድር ከአካባቢው ጋር እንዳይገናኝ በማድረግ እንዲሁም ዝንብ እና የተለያዩ ነፍሳትን ብሎም ሽታን ከአካባቢው ማስወገድ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ ይህም ህብረተሰቡ እነዚህን መፀዳጃ ቤቶች የመጠቀም ልምድ እንዲያዳብር እና ፍላጎቱ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ የተሻሻሉ የመፀዳጃ ቤት ግንባታ ቴክኖሎጂዎች በሳኒቴሽን ማርኬቲንግ መርሃ ግብር

አማካኝነት በማስተዋወቅ እንዲሁም በአዳዲስ የመኖሪያ ቦታዎች ግንባታ ጊዜ እንዲተገበር በማድረግ ማስለመድ ይቻላል፡፡ መንግስት ዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ላይ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች በነዚህ መፀዳጃ ቤቶች ግንባታ ላይ የራሱን እገዛ ማድረጉ አስፈላጊ ነው፡፡

ማንም ሰው በሜዳ ላይ የሚፀዳዳበት ሁኔታ እንዳይኖር ሁሉም የከተማ ነዋሪዎች ንፅህናቸው የተጠበቁ መጸዳጃ ቤቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ግብ እውን ለማድረግ የጋራ እና የህዝብ መፀዳጃ ቤቶችን መገንባት አስፈላጊ ነው፡፡ ዓላማውም በአንድ የጋራ መፀዳጃ ቤት ከአምስት ቤተሰብ በላይ እንዳይጠቀም ማድረግ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች በተለያዩ ህዝብ በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች ሊገነቡ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች ቀጣይነት ያለው አገልግሎት መስጠት ስለሚገባቸው የራሳቸውን ገቢ ማግኛ መፍጠር ያስፈልጋቸዋል፡፡ ከመፀዳጃ ቤት አገልግሎት በተጨማሪም የህዝብ መታጠቢያ ቤቶችን አያይዞ መገንባት ይቻላል፡፡ እነዚሁ የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች ደረቅ መፀዳጃ ቤቶች፣ ከፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ (septic tank) ጋር የተገናኙ ወይም ውሀ በመድፋት ወይም በመልቀቅ የሚጸዱ ዓይነቶች ተደርገው ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ የግል መፀዳጃ ቤቶችም በዚሁ መልክ ከፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ (septic tank) ጋር ተያይዘው መሰራት ይችላሉ፡፡

ደረቅ መፀዳጃ ቤቶችን በየጊዜው ማስመጠጥ ተገቢ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ተጠቃሚዎችተመልሰው ሜዳ ላይ ወደ መፀዳዳት ወይም በጉድጓድ ውስጥ የተጠራቀመውን ቆሻሻ በየሜዳው ወደ ማስወገድ ሊያመሩ ይችላሉ፡፡ የመፀዳጃ ቤቶቹ ዓይነትፍሳሽ ቆሻሻን ወደ ማድረቂያ የሚያስተላልፍ ማጠራቀሚያ (Baffled Septic tank) ከሆነ መፀዳጃ ቤቶቹን በተጠቃሚዎች ብዛት ላይ ተመስርቶ በየጊዜው ዓይነምድሩን ማስወገድ ይገባል፡፡ ቆሻሻን በፍሳሽ መልክ የሚያስወግዱ (Cesspits) ግን ዝግ፣ ፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻን በአንድ ላይ ስለሚይዝ በተጠቃሚዎች ብዛት ላይ ተመስርቶ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው መመጠጥ ይኖረበታል፡፡

ባለው ነባራዊ ሁኔታ ግን በየቤቱ የሚገኙት ቆሻሻን በፍሳሽ መልክ የሚያጠራቅሙት (Cesspits) በ አብዛኛው ሁሉንም ዓይነት ፍሳሽ ወደ መጸዳጃ ቤት መጨመር የሚያስከትለውን የማስመጠጫ ወጪ በመፍራት ከህግ ውጪ ተሸንቁረው የሚፈሱ ናቸዉ፡፡

በአሁኑ ወቅት በትላልቅ ከተሞች ውስጥ እየተገነቡ ያሉት ህንፃዎች ትላልቅ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ አላቸው፡፡ እነዚህን የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች በተገቢው ጊዜ ቆሻሻውን

ለማስመጠጥ የሚያስፈልጉት የፍሳሽ ቆሻሻ ማንሻ መኪኖች እጥረት እንዲሁም የአገልግሎት ክፍያ ውድነት ሁኔታውን አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡

የፍሳሽ ቆሻሻ አገልግሎት የፍሳሽ ቆሻሻ እና ሌሎች ተጓዳኝ ፍሳሾች የሚጓጓዙበት እና የሚወገዱበት ስርዓት ነው፡፡ የፍሳሽ ቆሻሻ አገልግሎት ከላይ ከተገለጸው የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ጋር ብዙ የሚያመሳስላቸው ነገሮች አሉ፡፡ በዋናነት የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ስርዓትን በመጠቀም በአነስተኛና ጥቃቅን የፍሳሽ ቆሻሻን ከከተማ ውጪ ወዳሉ የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ ጣቢያ በመዉሰድ በተፈጥሮ ሂደት እነዲብላላ በማድረግ ጎጂነታቸውን የመቀነስ ስራ መስራት ይኖርበታል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ፍሳሽ ቆሻሻን የማጣራት ስራ የሚወሰደው ጎጂነትን የመቀነስ ሂደት ደግሞ ፍሳሽ ቆሻሻን በማድረቅ እና በሽታ አምጪ ተዋህሲያንን በማጥፋት ወደ አካባቢው ቢለቀቅ ጉዳት እንዳያመጣ ማድረግ ሲሆን እነዚህ ሁለት ሂደቶች የሚከናኑባቸውም ቦታዎች ከከተማ በእጅጉ እንዳይርቁ በማድረግ ወጪን መቀነስ ይቻላል፡፡ ለፍሳሽ ቆሻሻ አገልግሎት ስርዓት የሚያስፈልገው የሰው ሀይልም ሆነ መሣሪዎች የከተማውን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘቡና አዋጪነታቸውም የተረጋገጠ መሆን ይገባቸዋል፡፡ የፍሳሽ ቆሻሻ አገልግሎት ክፍያ በብዛት ማስወገጃ ቦታውም በራቀ ቁጥር የአስወጋጅ አካሉን የገንዘብ አቅም ከማዳከም ባለፈም ለማዳበሪያነት ሊውል ከሚችልበት አካባቢም ይርቃል፡፡

### 6.2.3 የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ

የሳኒቴሽን ችግሮች በመላው ሀገሪቱ ከተሞች በአብዛኛው ተመሳሳይ ናቸው፡፡ አብዛኛውን የከተማ ክፍል የሚደርስ ዋና የፍሳሽ ማስወገጃ ስርዓት የሚገኘው በአዲስ አበባ ብቻ ነው፡፡ እንደ ጎንደር ያሉ ከተሞች በከፊል የሚያገለግል የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመር ተዘርግቶላቸዋል፡፡

ሌሎች ከተሞች ደግሞ ያላቸው ደረቅ መጸዳጃ ቤቶችና እና የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ብቻ ነው፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚጠቀሙበት መንገድ እንደየከተሞቹ ስፋት፣ አቀማመጥ እና የእድገት ደረጃ ከከተማ ከተማ ይለያያል፡፡ በዚህም መሠረት ከተሞች ሊጠቀሙባቸው የሚገባቸውን የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መንገዶች የከተሞቹን ነባራዊ ሁኔታ በማየት በአምስት ተከፍለው ቀርበዋል፡፡

ትናንሽ ከተሞች (ደረጃ 5) ፡- በነዚህ ከተሞች ውስጥ በስርዓት የተዘጋጀ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ከማንኛውም ግንባታ ጋር አብረው እንዲሰሩ ደንብ ማውጣት የስፈልጋል፡፡ ቆሻሻ ማንሻ መኪኖች

ላይኖሩ ስለሚችሉ ከላይ በዓይነ-ምድር ቆሻሻ አወጋገድ ርዕስ እንደተገለፀው በዓይነ ምድር አሰባሰብ፣ ማከም እና መልሶ መጠቀም አማካኝነት ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ ስራዎች ተገቢው ምዘና ሊካሄድባቸው ይገባል፡፡ ከፍሳሽ ማጠራቀሚያዎች ውስጥ የሚገኘው ፍሳሽ ቆሻሻ ደግሞ እዚያው በተጠራቀመበት ስፍራ ሊታከም የሚችል ቢሆንም ይህ አሠራር ውሀ የማያሰርግ አፈር ወይም ከፍተኛ ጠለል ላይ የሚገኝ የከርሰ ምድር ውሀ በሚገኝባቸው አካባቢዎች ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡ በዓይነ-ምድር አወጋገድ የሚወጣዉንና የታከመዉን ፍሳሽ ቆሻሻ በትነት፣ በማስረግ ወይም ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ በማዘጋጃ ቤት ሥር ለሚከናወኑ ተግባራት ወይም ለእፅዋት ማብቀያ አገልግሎት በማዋል መጠቀም ይቻላል፡፡ የቆሻሻ ማከሚያ ወይም ማስወገጃ ቦታዎችን በደንብ አጥሮ በመከለል እንስሳት እና ሰዎች እንዳይደርሱባቸው መከላከል ያስፈልጋል፡፡ ያልታከመ የመፀዳጃ ቤት ቆሻሻን በግብርና ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ ማዋል ሊበረታታ አይገባም፡፡

መካከለኛ (ደረጃ 4) እና ሰፊ ከተሞች (ደረጃ 3)፡- በነዚህ ከተሞች ውስጥ ተገቢው ንድፍ የወጣላቸው መጸዳጃ ቤቶች እና የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ከማንኛውም ግንባታ ጋር አብረው እንዲሰሩ ደንብ መውጣት አለበት፡፡ አነስ ያሉ የፍሳሽ ማስወገጃ መኪናዎችንም መጠቀም ይቻላል፡፡ ይህም አግልግሎት በቀጥታ በውሀ እና ፍሳሽ አገልግሎት አማካኝነት ወይም ውክልና በተሰጣቸው ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ወይም በግል ባለንብረትነት የሚተዳደሩ ኢንተርፕራይዞች አማካኝነት እንዲከናወን ማድረግ ይቻላል፡፡ ቆሻሻው የሚሰበሰብበት እና የሚታከምበት መንገድ ዘላቂ የሆነ የገንዘብ አቅም እና መልሶ መጠቀምን እንዲሁም ከከተማ እቅድ ጋር በሚስማማ መልኩ አካባቢያዊ፣ የጤና እና የደህንነት መስፈርቶችን ባሟላ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡ ለዓይነ ምድር አወጋገድ ከላይ የተቀመጡት መርሆዎች በሁሉም የከተሞች ነባራዊ ሁኔታ ላይ ተመስረተዉ ተግባራዊ መሆን ይገባቸዋል፡፡ የቆሻሻ ማከሚያ ወይም ማስወገጃ ቦታዎችን በደንብ አጥሮ በመከለል እንስሳት እና ሰዎች እንዳይደርሱባቸው መከላከል ያስፈልጋል፡፡ ያልታከመ የመፀዳጃ ቤት ቆሻሻን ለግብርና ሰራ ጥቅም ላይ ማዋል አይበረታታም፡

ትልቅ (ደረጃ 2) እና ዋና ዋና (ደረጃ 1) ከተሞች፡- በእነዚህ ከተሞች ውስጥ ደንቡን በተከተለ መልኩ የተዘጋጁ መጸዳጃ ቤቶች እና የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ከማንኛውም ግንባታ ጋር አብረው እንዲሰሩ ደንብ መውጣት አለበት፡፡ በተፈጥሮ ፍሳሽ ቆሻሻን የሚያጣራ የተደራጀና ከፍተኛ ኃይል ያለዉ ማብላያ (biological) እና በቂ ቦታ ባለበት ደግሞ ባለ አነስተኛ ኃይል የቆሻሻ ማብላያ ኩሬዎችን ማዘጋጀት የሚቻል ሲሆን እንዲህ ያለው አሠራር ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ከመጸዳጃ ቤት የሚወጣውን

ቆሻሻ ለማስወገድ የሚያስችል የሚለቀቅ ውሀ አቅርቦት እና አቅርቦቱን የመጠቀም አቅም ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ትልልቅ የፍሳሽ ማስወገጃ መኪኖችንም መጠቀም ይቻላል፡፡ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎችን ለመገንባትና የተሰበሰበው ዓይነ ምድር በማብላያ፣ "የአክስዴሽን ኩሬ" እና በመሳሰለው ሂደት ውስጥ አልፎ በጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ባላቸው የማድረቂያ መደቦች አማካኝነት የመጨረሻ ደረጃ ህክምና ይካሄድበታል፡፡ የውኃ እጥረት ባለባቸው ቦታዎች ደግሞ፣ የገንዘብ አቅምን ባገናዘበ መልኩ በልዩ ልዩ ማዕከላት የሚደረግ የቆሻሻ ማከም ስርዓት ተዘርግቶ ደረቅም ሆነ ፍሳሽ ቆሻሻን በማከም ለመልሶ መጠቀም በማዋል ተጨማሪ ገቢ መፍጠር ይቻላል፡፡ እነዚህ ማጣሪያ ማዕከላት የሚገነቡት በከተማው ውስጥ ከሕንፃዎች (መካከለኛ ቁመት ያላቸው የጋራ መኖሪያዎች እና ተቋማት) ፊት ለፊት ስለሚሆን፣ የሚጠቀሙበት የማጣሪያ ቴክኖሎጂ እና የመልሶ መጠቀም ሂደት በቅድሚያ ዘላቂ የገንዘብ አቅም መኖሩን፣ የህብረተሰቡን ተቀባይነት፣ የደህንነትና የጤንነት፣ በልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች መካከል የሚደረግ ትብብር (ለምሳሌ በማጣሪያው የሥራ ሂደት እና የቆሻሻ ተጠቃሚ መካከል ጥሩ ግንኙነት መፍጠር) እና የምጣኔ ሀብት እሴት አንጻር ሊገመገም ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከላይ የተጠቀሱት የዓይነ ምድር አወጋገድ መርሆዎች በከተማ ውስጥ የዓይነ ምድር አሰባሰብ እና ማከም ሂደት ውስጥ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ የቆሻሻ ማከሚያ ወይም ማስወገጃ ቦታዎችን በደንብ አጥሮ በመከለል እንስሳት እና ሰዎች እንዳይደርሱባቸው መከላከል ያስፈልጋል፡፡

## አደገኛና ከኢንዱስትሪዎች የሚወጡ ፍሳሽ ቆሻሻዎች፡-

ለጤና /ጠንቅ የሚያስከትሉ ቆሻሻዎች የሚባሉት በውስጣቸው ጎጂ ተፅዕኖ የሚያመጡ ንጥረ ነገሮችን የሚይዙ ሲሆኑ በልዩ ሁኔታ በማከም ጎጅነታቸውን መቀነስ ይገባል፡፡ ጠንቅ የሚያስከትሉ ንጥረ ነገሮች ቀለሞች፣ ነዳጅ፣ ዘይት፣ የፍሳሽ ማፅጃ፣ ለእርሻ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ጠንቅ የሚያስከትሉ ንጥረ ነገሮችን የያዙ ቆሻሻዎች የሚመነጩት ከከተሞች ስለሆነ በፍሳሽ ማስወገጃ ተቋም ወይም በማዘጋጃ ቤት ባለስልጣን በተረጋገጠ መንገድ ከመወገዳቸው በፊት በማምረቻው ስፍራ ወይም በሌላ ቦታ አስፈላጊውን ጎጂነት የመቀነስ ሂደት ማለፍ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ከታከሙ በኋላ የሚወገዱበት መንገድ እና ጊዜ ከደንብ አውጪ እና የአካባቢ ክብካቤ አካላት ጋር በሚደረግ ምክክር አማካኝነት በማዘጋጃ ቤት ኃላፊዎች አማካኝነት ሊጸድቅ ያስፈልጋል፡፡

### 6.2.4. የፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ አገልግሎትን ማደራጀትና ውክልና መስጠት

የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ አገልግሎት ሠጪ አካላት የሚሠራውን የሥራ መጠን በመጨመር የሚገኝ የምጣኔ ሀብት ጥቅም በሚኖርበት መልኩ አገልግሎቶችን በማደራጀት ይጠቀማሉ፡፡ ለምሳሌ ሀ) ብዙ ከተሞችን ለማገልገል የሚችሉ ፈጣን የሁለተኛ ደረጃ መሰብሰቢያ ተሸከርካሪዎችን ማዘጋጀትለ) ወጪ ሽፈናን ጨምሮ አንድ በደንብ የሚሰራ የፍሳሽ ማስወገጃ ስፍራን ማዘጋጀት ወይም ሐ) ለጋራ ግልጋሎት የሚውሉ የቆሻሻ ማንሻ ተሽከርካሪዎችን ማዘጋጀት መ) በተደራጁ ከተሞች ውስጥ ማእከላዊ ያልሆነ የዓይነ ምድር አወጋገድ እና ፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያ ጣቢያዎችን ማስተዳደር እና ሠ) በፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ደረጃ ወጪ ሽፈናን ተግባራዊ በሚያደርግ መልኩ መልሶ መጠቀምን ማቀናጀት፡፡ ይህም ቁልፍ የብቃት አመላካቾችን ጨምሮ ግልጽ የአገልግሎት ውሎችን (የአገልግሎት አስተዳደር ውሎች፣ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን) ባካተተ ግልጽ በሆነ ስምምነት የሚተዳደር መሆን አለበት፡፡ ይህ በአሁኑ ወቅት እየሠሩ ያሉ/ወደፊት አገልግሎት መስጠት የሚጀምሩ የሕዝብ ንብረት በሆኑ አገልግሎት ሰጪዎችም ሆነ በግል አገልግሎት ሰጪዎች (የተሻለ አገልግሎት ለማቅረብ እንደሚችሉ የታመነባቸው) ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

በጠቅላላው ትልልቅ የግል ድርጅቶች አገልግሎት ለመስጠት ብቁ ሆነው የሚቆጠሩት ስርዓቱ ሙሉ በሙሉ ከተዘረጋና ዘላቂ የገንዘብ አቅም እንዳለ ከተረጋገጠ በኋላ ሊሆን ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም የግል ድርጅቶች ከኢንተርናሽናል ፋይናንሺያል ኢንስቲቲዩሽን የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት የማይችሉ ስለሆነና ድርጅቶቹ የሚከሰትባቸውን ወጪ ፍራቻ ተጨማሪ የአገልግሎት ክፍያ በተጠቃሚዎቻቸው ላይ ሊጭኑ ይችላሉ፡፡

በመጀመሪያ የሚታሰበው የተደራጀ የሳኒቴሽን የሥራ ሂደቱ በሕዝብ ባለቤትነት የሚተዳደር ሆኖ በማዘጋጃ ቤቶች ህብረት (የንብረቶቹ ባለቤቶች ለአገልግሎት አሰጣጡ ኃላፊነት ያለባቸው) አማካኝነት በሚገባ የአገልግሎት አስተዳደር ውል አማካኝነት የሚከወን ነው፡፡ በዚህ አካሄድ የክፍያን ተመጣጣኝነት መቆጣጠር አያይዞም በሌሎች የሚደረግን የመነሻ ካፒታል ወጪ እና የሥራ ማካሄጃ ወጪ የገንዘብ ድጎማን ለመቀነስ ያግዛል፡፡ የአገልግሎት አስተዳደር ውል በባለንብረቶቹ (ማለትም የማዘጋጃ ቤቶች ህብረት ተብሎ በሚጠራው) እና ኃላፊነቱ በተሰጣቸው አገልግሎት ሰጪ አካላት መካከል የሚፈረም ይሆናል፡፡

ትልልቅ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የተወሰኑ ስራዎችን በተወሰነ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ

(ለደንበኞች የሚሰጠው የአገልግሎት ጥራት እና የኃላፊነት መጠን በእጅጉ በሚሻሻልበት መንገድ) ወይም ልዩ ሙያ የሚፈልጉ የቴክኒክ ተግባራት (ለምሳሌ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ጣቢያው ላይ ለሚከናወኑ ሥራዎች) ለዚህ ሥራ ተብሎ የሚቀርበው ገንዘብም ሆነ አቅርቦት ለሌላ ሥራ እንደማይውል ባረጋገጠ መልኩ በውክልና ለሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች መሥጠት ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜኃላፊነቱ ያለባቸው አገልግሎት ሰጪዎች ውክልና ከሚሰጣቸው አገልግሎት ሰጪዎች ጋር የውክልና አገልግሎት አስተዳደር ውል መዋዋል ይኖርባቸዋል፡፡

የውክልና አገልግሎት አስተዳደር ውሉ የሚያስገኘው ዋነኛ ጥቅም ለዚህ ሥራ ተብሎ የሚመደበው ገንዘብም ሆነ አቅርቦት ለሌላ ሥራ እንዳይውል የሚያግድ ከመሆኑም ባሻገር አገልግሎቱን ለማስተዋወቅም ሆነ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ግልጽ የሆነ የትርፍ ገደብ የሚያበጅ መሆኑ ነው፡ ፡ በሁለቱም በአገልግሎት አስተዳደር ውል እና የውክልና አገልግሎት አስተዳደር ውስጥ ለተቀጣሪዎች የሚሆን ማበረታቻ መስጠት የአገልግሎት ጥራት እና ደረጃ የተሻሻለ እንዲሆን ያስችላል፡፡ ለምሳሌ፣ በውኃ እና የሳኒቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ከፍተኛውን ቁልፍ የክንውን አመላካች ያስመዘገቡ ሰራተኞች የገንዘብ ጉርሻ ወይም ሌላ ማበረታቻ ቢያገኙ አሠራሩ የተቀላጠፈ ይሆናል፡፡

- ✓ የአደረጃጀት (clustering) መርሆዎች፡- አደራጀጀቱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተና ጠቃሚ የሆኑ አካሄዶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የቴክኒክ እገዛዎችን በማበረታቻ መልኩ በማቅረብ፣ ለአገልግሎት አሰጣጥ የሚውል የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት የሚያስችሉ ንድፈ-ዕቅዶችን (proposals) እና የፕሮጀክት በመከታተል እና የአገልግሎቱን ተቀባይነት በማመቻቸት አማካኝነት ሊደረግ ይገባል፡፡ በመርህ ደረጃ አደረጃጀት ልዩ ልዩ ማዘጋጃ ቤቶች ከቴክኒካዊ፣ የገንዘብ እና ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ጥናቶች አንጻር ያላቸውን ቅርበት ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡

## 6.2.5. የፍሳሽ/የጎርፍ መውረጃ

በአብዛኛው ከተማ የፍሳሽ መውረጃ በቀለበት መንገዶች ዳርና ዳር ብቻ የሚገኝ ነው፡፡ አባጣ ጎርባጣ ወይም ተራራማ መልከአ ምድር ባላቸው ከተሞች ደግሞ በአካባቢው የሚገኙ የውሀ ምንጮች እንደ ፍሳሽ መውረጃ ያገለግላሉ፡፡ ቱቦዎቹ  የዝናብ ውኃን ብቻ ሳይሆን የተለያዩ እጣቢዎችን እና ከተለያዩ የመፀዳጃ ቤት ጉድጓድ ወይም ከቆሻሻ ማጠራቀሚያ የሚወጡ ፍሳሾችን ሊያስተናግዱ ይችላሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ዋና ከተማዋን አዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎች ትላልቅ ከተሞች እንዲሁም

ደረቅ መጸዳጃ ቤቶች ሞልተው በሚፈሱባች ቦታዎችም የሚታይ ነው፡፡ ፍሳሾቹ ከተለያዩ ምንጮች የሚወጡ ቆሻሻዎችን ይዘው ከዝናብ ውሀ ጋር መቀላቀላቸው ዋነኛው ችግር ነው፡፡ የሚመለከታቸው ደንብ አውጪና አሰፈጻሚ አካላት ለዚህ ችግር ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው ፍሳሾች በተገቢው ሁኔታ የሚወገዱበትን መንገድ ሊያመቻቹ ይገባል፡፡

ስለዚህም የፍሳሽ መውረጃ ቱቦዎች መንገዶችን እና ሌሎች ተያያዥ መሠረተ ልማቶችን የሚያካትተው የከተማ መሠረተ ልማት ግንባታ ስትራቴጂ ውስጥ ሊካተቱ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን አገልግሎት አሰጣጡ፣ በተለይም ደረቅ ቆሻሻን ከፍሳሽ ቆሻሻ ውስጥ የማስወገድ ሂደቱ በማዘጋጃ ቤት ወይም መንገድ በማጽዳት ሥራ ላይ በሚሳተፉ ጥቃቅን ኢንተርፐራይዞች አማካኝት ሊከናወን ይገባዋል፡፡

## 6.2.6. በውኃ አቅርቦት እና በሳኒቴሽን መካከል ያለ ግንኙነት

የሳኒቴሽንን አገልግሎት ከማስተዋወቅና ከመሸጥ በተጨማሪ የንፁህ፣ አስተማማኝ እና የታከመ ውኃ አቅርቦትን ማስተዋወቅ እና ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ በንፁህ እና በቂ የውኃ አቅርቦት፣ የተሻሻለ ሳኒቴሽን እና ሀይጂን እንዲሁም በባህሪ ለውጥ መካከል የጤና ሁኔታ መሻሻልን ሊያስከትል የሚችል ግልጽ የሆነ ግንኙነት አለ፡፡ የውኃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን የማይነጣጠሉ ጉዳዮች ስለሆኑ በተቀናጀ ሁኔታ መተግበር አለባቸው፡፡

ህብረተሰቡን ከሳኒቴሽን አገልግሎቶች ይልቅ ለንፁህ ውኃ አቅርቦት ክፍያ የመክፈል ፍላጎቱ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለዚህ የውኃ አቅርቦትን እና የቆሻሻ አወጋገድ አገልግሎትን ማቀናጀት የቴክኒክ እና ምጣኔ-ሀብታዊ ጥቅሞችን ያስገኛል፡

አብዛኛዎቹ የሀገራችን ከተሞች ከውኃ አቅርቦት እጥረት ወይም ከመሰረተ ልማት እጥረት አልያም ከሁለቱም የተነሳ የውኃ እጥረት ይስተዋልባቸዋል፡፡ በቂ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገኝ እና ተደራሽ የሆነ የሳኒቴሽን አገልግሎት እና ተገቢ የሀይጅን ልምድ ይዳብር ዘንድ፣ ያሉትን የውሀ ምንጮች በውሀ-ከርሰ ምድር አቅም ግንባታ (hydro geological capacity building) በታገዘ መልኩ በዘላቂነት መጠቀም፣ እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጡ በተወከሉ አካላት አማካኝነት እንዲከናወን ከማድረግ በተጨማሪ በሕንጻዎች ውስጥ ውሀ ቆጣቢ መገልገያዎችን መጠቀም በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡

## 6.3. የተቋማት ሳኒቴሽን

የተቋማት ማለትም(የመንግስት ቢሮዎች፣ትምህርት ቤቶች እና ጤና ተቋማት) ሳኒቴሽን ሁኔታ ከከተማ ከተማ የሚለያይ ቢሆንም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በነባራዊ ሁኔታ ምዘናው አማካኝነት በተገለጸው መልኩ ተግዳሮቶቹን ሙሉ በሙሉ ለመፍታት የሚቻለው ተቋማት ከሳኒቴሽን ጋር በተያያዘ ያለባቸው ኃላፊነቶች ዳግመኛ ሲተነተኑና አቅርቦቶች በተገቢው ሁኔታ ሲዳረሱ ነው፡፡ ለምሳሌ የትምህርት ቤት ሳኒቴሽን መተዳደር ያለበት በክልሉ ትምህርት ቢሮ፣ የጤና ተቋማት ሳኒቴሽን በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አማካኝነት እንዲሁም በየአካባቢው የሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሳኒቴሽን መገልገያዎች በአካባቢያው የመንግስት መዋቅሮች አማካኝነት መሆን አለበት፡፡ እነዚህ አካላት በተደራጀ የማዘጋጃ ቤት እቅዶች እና የገንዘብ አቅርቦት ማመልከቻዎች አማካኝነት የገንዘብ አቅርቦት ማግኘት እና ከመመሪያዎች እንዲሁም የአካባቢ፣ ጤና እና ደህንነት ደንቦች ጋር በተስማማ መልኩ መተግበራቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ስትራቴጂው ከታች በተዘረዘሩት አካሄዶች አማካኝነት የቴክኒክ እና ማኅበራዊ ጉዳዮችን ክንውን ያግዛል፡፡ ቀጥሎ የተዘረዘሩት የሳኒቴሽንና ሀይጅን ተቋማት ደረጃዎችን እና/ወይም አገልግሎቶችን እና የተሻሻሉ የሀይጅን ባህሪ ደረጃዎችን ያመለከታሉ፡-

- ሁሉም ተቋማት ስርዓተ ጾታን፣ የአካል ጉዳተኝነትን የማካሉ ንፁህ፣ ጽዳታቸው የተጠበቀ መፀዳጃ ቤቶች እና የሳሙና ማስቀመጫን ጨምሮ የመታጠቢያ መገልገያዎች እንዲሁም አመቺ የቆሻሻ መጣያ መገልገያዎች ሊኖሯቸው ያስፈልጋል፡፡

- ሁሉም ትምህርት ቤቶች ህፃናትን፣ ስርዓተ ጾታን እና የአካል ጉዳተኞችን ያማከለ የውኃ፣ የመጸዳጃ እንዲሁም ሳሙናዎችን የሚይዝ የመታጠቢያ አገልግሎት እንዲሁም የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ስፍራ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በተለይ ለታዳጊ ወጣቶች በሚመች መልኩ ስለ ወር አበባ ንጽህና አጠባበቅ ጉዳዮች የሚያወሳ ግንዛቤ የማስጨበጥ ተግባር ሊሰራ ይገባል፡፡ ትምህርት ቤቶችም በግቢያቸው ውስጥ ለሚበሰብስ እና ለማይበሰብስ ቆሻሻ ተለያይቶ የተዘጋጀ የቆሻሻ መጣያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

- የእምነትስፍራዎች፣ ገበያዎች፣ የአውቶቢስ መናሀርያዎች፣ እና ማረሚያ ቤቶችን ጨምሮ ሁሉም ተቋማት ተገቢው የሳኒቴሽን መገልገያ እንዲኖራቸው እና በንጹህ እና ጤናማ ሁኔታ እንዲያዙ ያስፈልጋል፡፡

### 6.3.1. የጤና ተቋማት

- እንደ እትብት መቅበሪያ ጉድጓዶች፣ ቆሻሻ ማቃጠያዎች፣ መጸዳጃ ቤቶች፣ መታጠቢያ ቤቶች፣ የእጅ መታጠቢያ ሳህኖች ወዘተ ያሉትን መገልገያዎች መገንባት፣ መጠገን፣ ማደስ ወይም አገልግሎት የማይሰጡትን መልሶ በመገንባት ማስተካከል ይኖርባቸዋል

- ሁሉም የጤና ተቋማት (ጤና ጣቢያዎች፣ የጤና ኬላዎች እንዲሁም ሆስፒታሎች) ንጹህ እና በቂ የውሀ አቅርቦት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል

- የአካል ጉዳተኞችን እና የተለያየ የጤና ችግር ያለባቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች ባማከለ መልኩ ንጹህ እና በቂ የውሀ አቅርቦት፣ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን አቅርቦት ሊኖራቸው ያስፈልጋል

- የንጹህ ውሀ አቅርቦት፣ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን አገልግሎቶችን ፍላጎት ሙሉ በሙሉ ለማርካት በሚያስችል መልኩ ተጨማሪ የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን መገንባት ያስፈልጋል፡፡

- ንጹህ እና አስተማማኝ የጤና ተቋማትን እርምጃ (CASH intiative) ተግባራዊ ማድረግ

- በሄልዝ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም እና በኮምፕረንሲቭ ሞዴል ኦፍ ኢንፎርሜሽን ሲስተም አማካኝነት የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ይዞታን የሚከታተል ስርዓት መዘርጋት

### 6.3.2. ትምህርት ቤቶች እና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች

- እንደ መጸዳጃ ቤቶች፣ የእጅ መታጠቢያ መገልገያዎች እና ቆሻሻ ማቃጠያ ጉድጓዶች ያሉ መገልገያዎችን መገንባት፣ መጠገን ማደስ ወይም አገልግሎት የማይሰጡትን አገልግሎት በሚሰጡት መተካት

- የአካል ጉዳተኞችን እና የተለያየ የጤና ችግር ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ባማከለ

መልኩ ንጹህ እና በቂ የውሀ አቅርቦት፣ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ተቋማት ሊኖራቸው ያስፈልጋል

- ለታዳጊ ልጃገረዶችና ሴቶች የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ መገልገያዎችን ማዘጋጀት
- ሁሉም ትምህርት ቤቶች ንጹህ እና በቂ የውሀ አቅርቦት የሚሰጡ መገልገዎች ሊኖሯቸው ይገባል
- የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ የንጹህ ውሀ አቅርቦት፣ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን አገልግሎቶችን ፍላጎት ለማሟላት በሚያስችል መልኩ በቂ መገልገያዎችን መገንባት ይኖርበታል
- በትምህርት ቤቶች የሳኒቴሽንና ሀይጂን ስራዎችን ማስተዋወቅ፤ ሳኒቴሽንና ሀይጂን በካሪኩለም በማካተት በመማር ማስተማሩ ሂደት ዉስጥ ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ
- በትምህርት ቤቶች ግምገማና ምዘና ሂደት ውስጥ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ይዞታ አመላካች ዘዴዎችን መካተት አለባቸው

### 6.3.3. የምግብ እና መጠጥ አገልግሎት መስጫ ድርጅቶች

ሁሉም የምግብ እና መጠጥ አቅራቢ ተቋማት አገልግሎት መስጠት ከመጀመራቸው በፊት የሳኒቴሽን እና ሀይጅን መገልገያዎችን ማሟላታቸውን እና መገልገያዎቹም በትክክል የሚሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ፍተሻ ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ በማስከተል የተዘረዘረው ሂደትም ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

- አዲስ የምግብ እና መጠጥ አገልግሎት አቅራቢዎች የሥራ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የሳኒቴሽን እና ሀይጅን መገልገያዎች በበቂ ሁኔታ መሟላታቸውን ማረጋገጥ፡፡ የሚያረጋገጠው በጤና ዘርፍ ፤ከንግድና እና ቱሪዝም ዘርፍ ጋር በቅንጅት ይሆናል ፡፡ በሁሉም የምግብ እና የመጠጥ አገልግሎት አቅራቢዎች ላይ መደበኛ ቁጥጥርና ፍተሻ ከጤና፤እና ንግድ እና ቱሪዝም ዘርፍ በተውጣጡ ኤክስፐርቶች/መርማሪዎች ቡድን አማካኝነት ማከናወን እና ተገቢውን እርምጃ ያለማወላወል መውሰድ፡፡

እንደ እስር/ማራሚያ ቤት፣ የወታደር መኖሪያዎች፣ ካምፖች ወዘተ የመሳሰሉ ተቋማትም በተመሳሳይ መልኩ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ደንቦችን ማሟላታቸውንቁጥጥር ይካሄዳል፡፡

## 6.4. የድንገተኛ አደጋ የከተማ ሳኒቴሽን

ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር በቅርቡ ያወጣቸው መመሪያዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚያስፈልጋቸው ቢሆንም አንዳንድ ዝርዝር መመሪያዎች ከዚህ በታች ተካትተዋል፡፡

በድንገተኛ አደጋ ምላሽ ወቅት ሊተኮርባቸው የሚገባ ሦስት ዋና ዋና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባራት በቂ መጠን ያለው ንጹህ ውኃ፣ መሠረታዊ የሳኒቴሽን አገልግሎትን ማዘጋጀት እና የሀይጅን ባህሪያትን ማስተዋወቅ ናቸው፡፡ የአደጋ ጊዜ መርኃ ግብሮች በአጭር ድንገተኛ አደጋ ጊዜ ከሚካሄዱ ፈጣን እና ውስን ትግበራዎች እስከ የውስብስብ አደጋ ጊዜ አጠቃላይ እና የረዥም ጊዜ ትግበራዎች የሚያካትቱ ናቸው፡፡

### 1. ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ዓይነ ምድርን ማስወገድ

በአብዛኛዎቹ የድንገተኛ አደጋ ሁኔታዎች ውስጥ አይነ ምድርን ደህነንቱ በተጠበቀ መንገድ ማስወገድ ልክ እንደ ንጹህ ውኃ አቅርቦት ሁሉ በፍጥነት እና ተገቢውን ጥረት ባካተተ መልኩ ሊከናወን የሚገባው ተግባር ነው፡፡ ድንገተኛ አደጋ ለደረሰባቸው ሰዎች ክብር፣ ደህነነት እና ጤና ሲባል ለመጸዳጃ የሚሆኑ ተገቢ መገልገያዎችን ማቅረብ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ዓይነ ምድርን ማስወገድ አካባቢውን በዓይነ ምድር እንዳይበከል ይከላከላል፡፡ ድንገተኛ አደጋ ከደረሰ በኋላ ወዲያውኑ እንዲሁም የዓይነ ምድር አወጋገድ አገልግሎት በመዘጋጀት ላይ ሳለ፣ በመጀመሪያ ዘመቻ፣ ሰዎች የተጸዳዱባቸውን ቦታዎችን መለየት እና ሰዎች ወደዚያ እንዳይቀርቡ ማድረግ፣ የጋራ መጸዳጃ ቤቶች የሚገነቡበትን ቦታ መለየት እና ግንባታ ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ ቀድሞ የነበሩ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች ላይ ጉዳት ባስከተሉ የከተማ ድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ሁኔታውን ማጥናትና ተገቢ የሆነ አማራጭ መፈለግ ለምሣሌ ተንቀሳቃሽ ሽንት ቤቶችን በጥቅም ላይ ማዋል ወይም በመደበኛ ሁኔታ ሊጸዱ የሚችሉ ጋኖችን በአገልግሎት ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡ የዓይነ ምድር ዝቃጭን ማጽዳት፣ በአግባቡ መያዝ፣ ማጓጓዝ እና ማስወገድ ትኩረት ሊደረግባቸው ያስፈልጋል፡፡

ስለዚህ የሚከተሉት ተግባራት ሊከናወኑ ያስፈልጋል፡-

- ዓይነ ምድር በአግባቡ ሊከማች የሚችልበት መንገድ መመቻቸቱን የሚያረጋግጡ

መለኪያዎችን ማዘጋጀት

- ስለ ደህንነቱ የተጠበቀ የዓይነ ምድር አወጋገድ እና ሀይጅን ከተጠቂ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በፍጥነት ውይይት ማድረግ
- ስለ ደህንነቱ የተጠበቀ የዓይነ ምድር አወጋገድ እና ተገቢዎችን መገልገያዎች መጠቀም የሚያወሱ የተቀናጁ የሀይጅን ማስተዋወቅ ዘመቻዎችን ማካሄድ
- የሳኒቴሽን መገልገያዎች ስፍራ፣ ዲዛይን እና ተገቢነትን በተመለከተ የሁሉንም ተጠቃሚዎች (በተለይም የሴቶች እና የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች) አስተያየት መቀበል እና ተስማሚ መሆኑን ማረጋገጥ
- የችግሩ ተጠቂ የሆኑ ሰዎች የመጸዳጃ መገልገያዎቻቸውን የሚገነቡበት፣ የሚያድሱበት እና የሚያጸዱበት መንገድ፣ መሳሪያ እና አቅርቦቶችን ማመቻቸት
- ለእጅ መታጠቢያ እንዲሁም መጸዳጃ ቤቶች ውስጥ ለማፍሰስ ወይም/እና ጤናማ በሆነ መንገድ ለማጽዳት የሚሆን የውኃ አቅርቦት እንዲኖር ማስቻል፣ በመደበኛዎቹ የጉድጓድ መጸዳጃ ቤቶች ከተጸዳዱ በኋላ ፊንጢጣን ለማጽዳት የሚውሉ መገልገያዎችን ማቅረብ
- እንደ ገበያ፣ የማሰራጫ ማዕከላት፣ የጤና ጣቢያ፣ ትምህርት ቤቶች ወዘተ ያሉ የሕዝብ መገልገያ ስፍራዎች ውስጥ የሚገኙ መጸዳጃ ቤቶች ለወንዶች እና ለሴቶች ተብለው የተለያዩ እንዲሁም ከውስጥ የሚቆለፉ መሆናቸውን ማረጋገጥ
- የመጸዳጃ ቤቶች አጠቃቀም በቤቶች ወይም/እና በጾታ አማካኝነት የተከፋፈሉ እንዲሆኑ አድርጎ ማዘጋጀት

| | ደህንነቱ የተጠበቀ የዓይነ ምድር አወጋገድ ዓይነት | የትግበራ ማመሳከሪያ |
|---|---|---|
| 1 | ተለይቶ የተከለለ የመጸዳጃ ስፍራ (ለምሳሌ በመጋረጃ የተከፋፈለ) | በመጀመሪያው ደረጃ፡ እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ወዲያውኑ ሊገለገሉባቸው የሚያስፈልጉ መጸዳጃዎች በሚያስፈልጉባቸው የመጀመሪያዎቹ ሁለት እና ሦስት ቀናት |
| 2 | በጊዜያዊነት የተቆፈሩ የቦይ መጸዳጃ ቤቶች (ትሬንች ላትሪን) | በመጀመሪያው አንስቶ፡ እስከ ሁለት ወራት ድረስ |
| 3 | ቀላል የጉድጓድ መጸዳጃ ቤቶች | ከመጀመሪያው አንስቶ የረዥም ጊዜ አገልግሎት ሊሰጡ እስከሚችሉበት ድረስ |
| 4 | የተሻሻለና በበቂ ሁኔታ አየር የሚያናፍስ ጉድጓድ ያላቸው መጸዳጃ ቤቶች | ከመካከለኛ እስከ ረዥም ጊዜ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉና በነባራዊው ሁኔታ ላይ የተመሰረቱ |
| 5 | ሽንትን በተለየ አቅጣጫ የሚያስወገድ ስነ-ምህዳራዊ (ኢኮሎጂካል) ሳኒቴሽን | ነባራዊውን ሁኔታ ያማከሉ ከፍተኛ የከርሰ ምድር የውኃ ጠለል ያላቸው እና በጎርፍ መጥለቅለቅ የተከሰተባቸው ሁኔታዎች ላይ ከመጀመሪያው አንስቶ ወይም ከመካከለኛ እስከ ረዥም ጊዜ በጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ |
| 6 | የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ (ሴፕቲክ ታንክ) | ከመካከለኛ እስከ ረዥም ጊዜ ሊያገለግሉ ይችላሉ |

## II. የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ

በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ወቅት የሚከተሉት ሊደረጉ ያስፈልጋል

- የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ መርሀ ግብር በሚዘጋጅበት ጊዜ ተጎጂው ሕብረተሰብ በአዘገጃጀቱና ትግበራው ላይ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ
- በወቅታዊነት የሚካሄድ የደረቅ ቆሻሻ የጽዳት ዘመቻ እንዲካሄድ ማቀናጀት
- አነስተኛ መጠን ያላቸው የንግድ ሥራዎች የሚከናወኑበትን እድል ወይም ቆሻሻን ለድግመ-ዑደት በማዋል የሚገኘውን ተጨማሪ/ደጋፊ ገቢ ከግምት ውስጥ ማስገባት

ቆሻሻን ለድግመ-ዑደት ማዋል ለአነስተኛና ጥቃቅን የንግድ ተቋማት እንደ ተጨማሪ የስራ እድል መቁጠር

- ከችግሩ ተጠቂ ማህበረሰብ ጋር በመተባበር ከየቤቱ የሚወጣው ቆሻሻ ለመደበኛ አሰባሰብ በሚያመች መልኩ እንዲቃጠል ወይም እንዲቀበር በሚያስችል መልኩ በቆሻሻ ማከማቻ ውስጥ መጠራቀሙን እንዲሁም ሌሎች ከጤና ተቋማት የሚወጡና ሌሎች አደገኛ ቆሻሻዎች ከአጠቃላይ የቆሻሻ አወጋገድ ሂደቱ ተነጥለው መቀመጣቸውን ማረጋገጥ
- የጤና ጠንቅ ወይም ሰዎችን የሚረብሽ ከመሆኑ በፊት ቆሻሻው ከአካባቢው እንዲወገድ ማድረግ
- በድንገተኛ አደጋ ወቅት የሚፈጠረውን ተጨማሪ ቆሻሻ ከግምት ውስጥ በማስገባት አደጋዉን በሚያስተናግዱ ቤተሰቦች መኖሪያ ቤት አካባቢ ተጨማሪ የቆሻሻ ማከማቻና መሰብሰቢያ አገልግሎቶችን ማመቻቸት
- እንደ ገበያ ስፍራዎች፣ የአሳ ማከፋፈያዎች፣ የእርድ ቦታዎች ባሉ የሕዝብ መገልገያ ቦታዎች ተገቢው ምልክት ያለባቸው እና በሚገባ አጥር የተሠራላቸው የቆሻሻ ማስወገጃ ጉድጓዶች፣ ቅርጫቶች ወይም ለአካባቢው እንዲያመቹ ሆነው የተዘጋጁ የቆሻሻ ማከማቻዎች ማዘጋጀት
- መደበኛ የቆሻሻ አሰባሰብ ስርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ
- ደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ እና አወጋገድ ላይ እንዲሁም ለድግመ-ዑደት (ለሪሳይክሊንግ) የሚውለውን ቆሻሻ በመለየት የሚሳተፉ ሰራተኞች ተገቢው ሰውነት ላይ አደጋ እንዳይደርስ የሚከላከል አልባሳት እንዲያገኙና የቴታነስ እና የሄፓታይተስ ቢ ክትባቶችን እንዲከተቡ ማድረግ
- የሰዎች በድን ክብራቸውን በጠበቀ እና ተገቢ በሆነ መልኩ የሚቀበርበትን መንገድ ከሚመለከታቸው ኤጀንሲዎች እና ባለስልጣናት ጋር በመተባበር ማመቻቸት

## III. ማፋሰሻ (የዉሀ መዉረጃ)

በፍሳሽ አወጋገድ ሂደት ውስጥ የሚከተሉት ተግባራዊ ሊሆኑ ያስፈልጋል፡-

- የመኖሪያ አካባቢዎች እና የውኃ ማሰራጫ ቦታዎች ያቆረ ውኃ ከምችት እንዳይኖርባቸውና የጎርፍ ውኃ የሚተላለፍባቸው የውኃ መዉረጃ ቦዮች ክፍት እንዲሆኑ ማድረግ
- የፍሳሽ ቆሻሻን ችግር ለመፍታት የሚያመች ስምምነት ጉዳቱ ከደረሰበት ሕዝብ ጋር ማድረግ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ለአነስተኛ የፍሳሽ ማስወገድ እና ጥገና የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን ማቅረብ
- ሁሉም የውኃ ማቅረቢያ ስፍራዎች እና የመታጠቢያ መገልገያዎች ጭቃ እንዳይፈጥሩ አመቺ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴ መኖሩን ማረጋገጥ

### IV. ሀይጅንን ማስተዋወቅ

ሀይጅንን ማስተዋወቅ በድንገተኛ አደጋዎች ጊዜ የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን አንድ አካል ሆኖ ሊተገበር ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የሚከተሉት እርምጃዎች ሊወሰዱ ያስፈልጋል፡-

- ብዙ ሕዝብን ለመድረስ የሚያስችሉ ተገቢ የመገናኛ ዘዴዎችን በመፍጠር ከሀይጅን ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮች እና የመከላከያ መንገድ በተመለከተ መረጃን ማስጨበጥ
- ልዩ ልዩ የማህበረሰቡን ክፍል ሊያነሳሱ የሚችሉ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ ጉዳዮችን ለይቶ ማወቅና ሀይጅንን ለማስተዋወቅ የተግባቦት ስልት አድርጎ መጠቀም
- ጉዳቱ ከደረሰባቸው ጋር ቀጣይነት ያለው ውይይት ለማካሄድ በሚያችል መልኩ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበት መንገድ በሚኖር ጊዜ ሁሉ አሳታፊ የሀይጅን ተግባቦት ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ

ከተጎጂው ማኅበረሰብ ጋር በመተባበር ቁልፍ የሀይጅን ተግባራትን እና የቀረቡትን መገልገያዎች አጠቃቀም በመደበኛነት መገምገም፡፡

## 6.5. አቅም ግንባታ

አቅም ግንባታ በፌደራል፣ ክልል፣ ዞን (እንደ አስፈላጊነቱ) እና በከተማ ደረጃ ያለውን የእቅድ፣ ትግበራና ግምገማ ክፍተት የሚመለከት ሁለንታዊ አቀራረብ ነው፡፡ አቅምን በሚመለከት ያለው ክፍተት የፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት አሰጣጥን፣ ማስተዋወቅ፣ ደንብ እና የደንብ አፈጻጸምን

በሚዳስስና ሁሉን ባጠቃለለ መልኩ ይፈተሻል፡፡ የአቅም ግንባታ የስርዓት እድገትን፣ የፋይናንስ ምዘናን፣ የመገልገያዎች ግዢ፣ የስራ ሂደት፣ የሠራተኞች ስልጠና እንዲሁም የአመራር መርኃ ግብሮች እድገትን ያካተተ ይሆናል፡፡

አቅምን ለመፍጠር እና ለመጨመር በጥቅም ላይ የሚውለው ስትራቴጂ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- ስልጣኑ የተሰጣቸው ተቋማት አገልግሎቶችን እና ቅድሚያ የተሰጣቸው ጉዳዮችን ለማከናወን ያላቸውን አቅም በአጠቃላይ መመዘን
- በከተማ ወይም በተደራጀ ከተማ ደረጃ ለአጭር፣ ረዥም እና መካከለኛ ጊዜ አጠቃላይ እቅድ ማውጣት፡፡ እቅዶቹም ስልጣኑ ለተሰጣቸው አካላት በሚሆን መልኩ የአጠቃላዩ የልማት እቅድ አካል ሆነው በከተማ አስተዳደር ሊጸድቁ ያስፈልጋል፡፡
- በኢትዮጵያ ውስጥ አቅም ግንባታን ለማስተዋወቅ ተሞክረው ውጤታማ የሆኑትን ተሞክሮዎች ለሌሎች ማካፈል የሚቻልበት ሀገር አቀፍ መድረክ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡
- ሁሉም ኃላፊነት ያለባቸው ተቋማት ለአቅም ግንባታ የሚሆን በጀት መመደብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የአቅርቦት እጥረት ያለባቸው ከተሞች አቅርቦቶችን የሚያገኙበትን መንገድ ከመነሻ የገንዘብ አቅም ወይም ከሥራ ማስኬጃ ወጪ እቅድ ጋር በማያያዝ ሊያፈላልጉ ይገባል፡፡
- ለዚህ የአቅም ግንባታ ሥራ የሚያስፈልጉ ከክልል ወይም የማዘጋጃ ቤት በጀት ውጪ የሆኑ ተጨማሪ አቅርቦቶች ማዕከላዊ እንዲሁም አለም አቀፍ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ሊወዳደሩ በሚችሉበት መንገድ ከተደራጁ ማዘጋጃ ቤቶች ለቴክኒካዊ ድጋፍ በሚሆን መንገድ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡
- የሚሠራውን የሥራ መጠን በማብዛት እና አምራችነትን በመጨመር የሚገኘውን ትርፍ ለማብዛት እንደ ተቋማዊ ልማት፣ አቅርቦቶችን እና ሙያን በማጋራት እና የእቃዎች እና መገልገያዎች እና በዚህ ጽንሰ ሀሳብ ዙሪያ አቅም ግንባታን በማካሄድ ሊከናወን ይችላል፡፡
- በጨረታ ተወዳድረው የሚቀጠሩ የግል አማካሪዎች ከተሞችን፣ ክልሎችን እና ፌደራላዊውን መንግሥት የአቅም ክፍተቶች ምዘና እንዲያካሂዱ፣ የአቅም ግንባታ እቅድ

እንዲያዘጋጁ፣ ስልጠና እንዲያካሂዱ፣ የምህንድስና እቅዶችን እንዲያወጡና አዳዲስ የሥራ አካሄድ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ሊያግዙ ይችላሉ፡፡

- ለአጭር ጊዜ የሚዘጋጁ ስልጠናዎች እና ወርክሾፖች አዳዲስ አካሄዶችን ለማስተዋቅ፣ ተለይተው የታወቁ የአቅም ክፍተቶችን ለማስተካከል፣ አሰራሮችን ለማስገንዘብ፣ አዳዲስ ሠራተኞችን ከሥራ ሂደቱ ጋር ለማስተዋወቅ እና ለልምድ ልውውጥ ያገለግላሉ፡፡ የፌዴራል እና የክልል ተቋማት ክልሎችን እና ከተማዎችን የሚያሳትፉ ስልጠናዎችን እና ወርክሾፖችን በማዘጋጀት ከተማዎችን ያግዛሉ፡፡

- መሠረታዊ ሥልጠና በከተማ ደረጃ በቆሻሻ አሰባሰብ ላይ የሚሳተፉ፣ መገልገያዎችን የሚገነቡ፣ የሚያጓጉዙና ለሁሉም የሥራ ክንውን ባልደረቦች የሚሠጥ ይሆናል፡፡ በጤና እና ደህንነት፣ ቆሻሻ አያያዝ፣ ቆሻሻ መለየት፣ ቴክኖሎጂን መጠቀም እና የደንብና የደንብ አፈጻጸምን በተመለከተ ለማሰልጠኛ የሚውሉ መመሪያዎች የሚዘጋጁት በፌደራል ወይም በክልል ደረጃ ኃላፊነቱ በተሰጣቸው ተቋማት አማካኝነት ይሆናል፡፡

- ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም ለሌሎች የሚሰጡ ስልጠናዎች ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ቢዘጋጅ ተመራጭ ይሆናሉ፡፡

- የቴክኒክ እና በልዩ ልዩ ሙያ የሚሳተፉ ሠራተኞችን እንዲሁም የአመራር አካላትን ለማፍራት ታስቦ የሚዘጋጅ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ ስልጠና በልዩ ልዩ የትምሕርት ተቋማት ውስጥ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ የቴክኒክ ክፍተቶችን ለመሸፈን የቴክኒክ እና የሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ጠቃሚ ሚና እንዲጫወቱ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ ዩኒቨርስቲዎች ደግሞ ለሌሎች ባለሙያዎች እንደየ ሙያቸው ተስማሚ የሆኑ ስልጠናዎችን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ብሔራዊ አመራር ኮሚቴው ከልዩ ልዩ የሳኒቴሽን አያያዝ ጉዳዮች አንጻር ዩኒቨርስቲዎች የልቀት ማዕከል መሆናቸውን ማረጋገጥ እና ከክልሎች እና ከከተሞች ጋር ማስተሳሰር ይኖርበታል፡፡ ብሔራዊ የአመራር ኮሚቴው የስልጠናዎቹን የአሠራር አፈጻጸም ሊያወጣና ስልጠናዎቹን ለማካሄድ የሚያስችል የገንዘብ ድጋፍ የሚገኝበትን መንገድ ሊያመቻች ይገባዋል፡፡

## 6.6. የአዳዲስ ፈጠራዎች ምርምር እና ስርጸት

አጠቃላይ የውኃ፣ ሀይጅን እና ሳኒቴሽን አገልግሎቶችን እንዲሁም ደግሞ በተለየ ሳኒቴሽንን ተግባራዊ ማድረግ ቀጣይነት ያለው ምርምር እና አዳዲስ ጉዳዮችን ለማካተት ፈጠራ የታከለባቸውን ሀሳቦችን መጨመር በእጅጉ ያስፈልጋል፡፡ ይህም በሀገሪቷ ውስጥ ከሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች እና የምርምር ተቋማት ጋር በቅርበት ሆኖ በትብብር መሥራትን ይጠይቃል፡፡

በፍሳሽ እና የዓይነ ምድር ዝቃጭ ሳኒቴሽን ሰንሰለት ውስጥ ፈተኛውን ድርሻ የሚዙት በሁሉም የማህበረሰብ አባላት ጥቅም ላይ የሚውሉት መጸዳጃ ቤቶች ናቸው፡፡ የሳኒቴሽን መገልገያዎች የአካል ጉዳት ላለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በአብዛኛው አመቺ አይደሉም፡፡ በተመሳሳይ ስርዓተ ጾታን ያማከሉ አገልግሎቶች፣ በተለይም የወር አበባ ንጽህና አጠባበቅን በተመለከተ የተሰጠው አትኩሮች አነስተኛ ነው፡፡ ስርዓተ ጾታን እና የተጋላጭ ግለሰቦችን ፍላጎት ለማማሏት በሚያስችል መልኩ የግል፣ የሕዝብ እና የጋራ መገልገያዎች እንዲሁም በንግድ እና ተቋማዊ ሕንጻዎች ውስጥ በአነስተኛ ዋጋ ሊገነቡ የሚችሉ አማራጭ የሳኒቴሽን መገልገያዎችን በመለየት እና በመገምገም ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡

የኢትዮጵያ ትላልቅ እና ትናንሽ ከተሞች በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት "የውኃ እጥረት" ስላለባቸው ከፍተኛ የውኃ መጠን ከደረቅ ይዘት ሬሽዬ የሚያስፈልገው መደበኛ የፍሳሽ አወጋገድ ለማከናውን በእጅጉ ያስቸግራል፡፡ ይህም በምርምርና፣ ሌሎች ጥናቶችን በመመርኮዝ እና አዋጭ የሆኑ አሠራሮችን በተግባር በማሳየት ላይ የተመሰረተ ወጪ ቆጣቢ እንዲሁም በልዩ ልዩ ማዕከላት የተሰራጨ የፍሳሽ ቆሻሻ የማከም ሂደት መጠቀምን ይጠይቃል፡፡

መልሶ ለመጠቀም አመቺ የሆኑ ምርቶች ለማውጣት ከማለም ጋር ማእከላዊ ያልሆነ የቆሻሻ ፍሳሽ ውኃ ማከሚያ ግንባታ የሳኒቴሽን ሰንሰለቱ አንድ አካል ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፣ ሌሎቹም የሳኒቴሽን ሰንሰለት ክፍሎች እኩል ወይም የበለጠ ትኩረት ይፈልጋሉ፡፡ አስቸኳይ እና በግልጽ ትኩረት የሚፈልገው ስራ የታከመውን ፍሳሽ ከተመረተበት ስፍራ ለጥቅም ወደሚውልበት በተገነቡት ስፍራዎች መካከል ወይም ውስጥ ወደሚገኙ አረንጓዴ አካባቢዎች ወይም ፓርኮች የማጓጓዙ ሂደት ነው፡፡ ይህም ፓምፕ ከማድረግ፣ የቱቦ መስመር ዝርጋታ፣ ክፍት ቱቦዎች ለመጠቀም፣ ለብዙ ጥቅም የሚውሉ የጎርፍ ማሳለፊያ ቱቦዎች፣ ክምችት እና ከመሳሰሉት ጋር የተያያዙ ወሳኝ የቴክኒክ እና መሬት አሰጣጥ ሁነቶችን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም በማያሻማ የውል ስምምነት ላይ የተመሠረተ በባለ ድርሻ አካላት መካከል የወጪ እና የትርፍ ክፍፍል ሂደት ሊኖር ያስፈልጋል፡፡

ለአብዛኛዎቹ የከተማ ነዋሪዎች የሚሆን  የደረቅ መጸዳጃ ቤቶችን እንዲሁም አነስተኛ መጠን ያላቸው ቤቶች ውስጥ የተገነቡና አብዛኛውን ጊዜ የሚያፈሱ  የደረቅ  መጸዳጃ ቤቶችን ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ባዶ ለማዲረግ የሰገራ ማጠራቀምያ (ሴስፑል) የስትራቴጂው ጠቃሚ ክፍል ነው፡፡ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት መሳሪያ ሳይጠቀሙ በእጅ በሚከናወን የመጸዳጃ ቤት ጉድጓድ ባዶ የማድረግ ዘዴ ፈር ቀዳጅ ከመሆናቸውም ባሻገር ሞዴሎቹን ለማስፋፋት እቅድ አላቸው፡፡ በእጅ በሚከናወን መንገድ የመጸዳጃ ቤት ጉድጓድን ባዶ ማድረግ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገጥመው ችግር የቴክኒክ ሳይሆን፤ ከአመለካከትና ሁኔታውን ካለማወቅ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ስለዚህ የሳኒቴሽንን ገጽታ ከፍ ማድረግ፣ ሰርቶ ማሳያ ፕሮጀክቶችን ማከናወን፣ ከሌሎች ሀገራት ጋር የልምድ ልውውጥ ጉብኝቶችን ማካሄድ እና የግብይት ማስታወቂያዎችን መስራት ያስፈልጋል፡፡ ተጨማሪ መሣሪያ ሳይፈልግ በእጅ በሚሠራ መንገድ የመጸዳጃ ቤት ጉድጓዶችን ባዶ የማድረግን ማኅበረሰባዊ አቀባበል ለማሳደግ ትንሽ መጠን ባለው ሞተር አማካኝነት (እንደ ባጃጅ ባሉ) የዓይነ ምድር ዝቃጭ አወጋገድን መሞከር ጠቃሚ ሆኖ ይገኛል፡፡

የደረቅ ቆሻሻ አያያዝን እንዲሁም መጠናቸው ከፍ ያለ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎችን በተመለከተ ግን ለስራ ክንውኑ የሚሆነው ቴክኖሎጂ በሚገባ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያን ሁኔታ በሚገባ ያገናዘበ የቆሻሻ አወጋገድ ስራ የሚከተሉትን በማሟላት መሰራት አለበት፡፡ ሀ) ጥሌት ቆሻሻ (ከደረቅ ቆሻሻ ማሰወገጃ ቦታዎች የሚወጣ ፋሳሽ ቆሻሻ) ወደ ወራጅ እና በመስመር የሚያልፉ ውኃዎች ውስጥ እንዳይቀላቀሉ ለመከላከል፣ ለ) ፍሳሽ በማያሰርግ ሽፋን አማካኝነት ማብላያዎችን በመከለል ቆሻሻ እንዳይሰርግ እና በሽታ አስተላላፊዎች (እንደ ወፍ፣ አይጥ፣ ውሻ፣ ነፍሳት እና ለመሳሰሉት) ምቹ አለማድረግ እና ሐ) ለሁሉም መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ሰራተኞች ተገቢውን የጤና እና ደህንነት ሥራዎች እንዲያከናውኑ መመሪያ ማስቀመጥ፡፡

በቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት ላይ የሚሰሩ እንደ ስነ-ውኃ (ሀይድሮሎጂ)፣ ሀይድሮ ኬሚካል፣ ሲቪል ምህንድስና፣ የአከባቢ ጤና ፣ ሜካኒካል ምህንድስና እና የፕሮጀክት አያያዝ ግብአት ያሉ ሥራዎች ላይ የሚሠሩ ባለሙያዎች ለመጀመሪያ ግንባታ እና የሜካኒካል እቃዎች ግዢ እንዲሁም ቀጣይነት ያለው ጥገና እና የስራ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልግ ካፒታል መሟላት አለባቸው፡፡ አቅም ግንባታ እና የንግድ ሥራ እቅድ የልማቱ ዓይነተኛ ክፍሎች ናቸው፡፡

በተጨማሪም የቴክኒክ ፈጠራ፤ ቀዳሚ የሥራ ኃይልን በማሰባሰብ፣ ደረቅ ቆሻሻን ማጓጓዝ እና ጊዜያዊ ክምችት፣ ቀድሞውኑ ሥራቸውን እየከወኑ ባሉ ስራ ፈጣሪ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች

ዘንድ የታዩ መልካም ተሞክሮዎችን ተመርኩዞ በመቀጠል ላይ አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል፡፡ ለደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጥሩ የአሰራር ምሳሌ ከሚሆኑት ውስጥ ደረቅ ቆሻሻዎችን ከየቤቶቹ ሰብስበው በአዲስ አበባ፣ ባህር ዳር፣ መቀሌ፣ ጎንደር፣ ውቅሮ፣ አዋሳ እና ሌሎች ከተሞች ወደሚገኙ የቆሻሻ ማዘዋወሪያ ቦታዎች ከተሞች የሚያስተላልፉ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ይገኛሉ፡፡

## 6.7. የሁለገብ ጉዳዮች ስትራቴጂ

### 6.7.1. ፍትሐዊነት

ተደራሽነትን ለማስፋፋት ይቻል ዘንድ የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂው አብዛኛውን ጊዜ በከተማ ውስጥ ተጠጋግተው በችግር ከሚኖርባቸው እና ከከተማ ወጣ ባሉ ቦታዎች የሚኖሩ አገልግሎት ያላገኙ የማህበረሰቡ ክፍሎች ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡ ይህም በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ሴቶችን፣ ህጻናትን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ እድሜያቸው የገፉ ሰዎችን፣ እስከ መጨረሻው በማይድን ወይም ለመዳን እረጅም ጊዜ በሚወስድ ስር የሰደደ በሽታ የሚሰያዩ ሰዎችን፣ እንዲሁም ለመድረስ አዳጋች በሆኑ እና/ወይም ወጣ ባሉ ቦታዎች የሚኖሩ፣ እና ጎዳና ላይ የሚኖሩ ሰዎችን ያካትታል፡፡ ጥራት በሌላቸው የኪራይ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ፣ በከተማ አስተዳደር እና ሃይማኖታዊ ተቋማት አማካኝነት በተሰጣቸው ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች እንዲሁም እስረኞች ጥራት ያለው የሳኒቴሽን አገልግሎት ላያገኙ ይችላሉ፡፡ የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂው ይህን የተደራሽነት ጉዳይ ለማሻሻል ለሁሉም የሚከተሉትን አካሄዶች ይከተላል፡-

- የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን መርሀ-ግብር አጠቃላይ የአገልግሎት ተደራሽነትን ለማመቻቸት በሁሉም የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን አገልግሎት ላይ ያለውን ያለመካተት ሁኔታ መፍታት ይጠበቅበታል፡፡
- ሁሉም ከከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶች፣ የተግባቦት ሥራዎች እና የልማት መርኃ ግብሮች የአካል ጉዳት ያለባቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች ችግር ለመፍታት የተሻለ ትኩረት መስጠት አለባቸው፡፡ ለሁሉም ሰው፤ በተለይም የአካል ጉዳተኞችን ሴቶች/ልጃገረዶችን፣ አዛውንቶችን እና የመሳሰሉትን ጨምሮ አገልግሎቱን

ማዳረስ እንዲቻል የተለያየ አገልግሎትን የሚሰጡ ልዩ ልዩ ተቋማት ላይ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያስፈልጋል፡፡

- የሕዝብ መጸዳጃ ቤት፣ የገላ መታጠቢያ፣ እና ሁሉንም የሕዝብ መገልገያዎች ጨምሮ አገልግሎት በመስጠት ላይ ወይም በግንባታ ላይ ያሉ መገልገያዎች ልዩ ልዩ ተጠቃሚዎች ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ሊገለገሉ እንደሚችሉ ሆነው መዘጋጀታቸውን ማጣራት ያስፈልጋል፡፡ በሕዝብ መገልገያ ቦታዎች እና እንደ ሆቴል፣ መጠጥ ቤት፣ ት/ቤት፣ እና የጤና ጣቢያዎች ያሉ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ የሚኖሩ የሳኒቴሽን መገልገያዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ጥራቸውን የጠበቁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የሃይጅን እና ሣኒቴሽን መገልገያዎች የሁሉንም፣ በተለይ ደግሞ የአካል ጉዳተኞችን ደህነንት እና ምቾት ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
- ስትራቴጂው የሴቶችን ፍላጎት እንዲሁም ከኤችአይቪ- ኤድስ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች የሳኒቴሽን መገልገያ ተደራሽነትን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂ የትግበራ እቅድ የሚከተሉትን ያገናዘበ ነው፡-
    - በሕዝብ፣ በማህበረሰብ መሰብሰቢያዎች፣ በጤና ተቋማት፣ ት/ቤት እና ሌሎች ተቋሞች ውስጥ የውኃ አቅርቦት ቀጣይነትን (መጠን ወይም መገልገያ ወይም ሁለቱንም) ለመጨመር የሚያስችሉ አማራጮች መኖር አለባቸው፡፡
    - እንደ መወጣጫ ደረጃ፣ ጠባብ መግቢያዎች፣ የሚያንሸራትቱ ወለሎች እና የመሳሰሉ ለሀይጂንና ሳኒቴሽን አገልግሎት የማያመቹ ቁሳዊ መሠረተ ልማቶችን ማስተካከል
    - ለአካል ጉዳተኞች እንዲያመች የሚወጡ ፖሊሲዎችን 74/ስራቴጂዎችን፤ እውቀት፣ ክህሎት፣ መረጃ፣ ተገቢ ዲዛይን እና ማማከር አካሄዶችን በሀላፊነት የሚይዙ፣ አካላትን ማቋቋም እና፣
    - በቤተሰቦች ላይ የሚደርስን መገለል፣ መድልዎ፣ ንቀት፣ ከተገቢው በላይ የሆነ ከለላ፣ የተሳሳተ መረጃ እና ማሳፈር ለመከላከል የሚያስችል የሕግ ከለላ እና የማህበረሰባዊ ነባራዊ ሁኔታ እንዲኖር ማስቻል

- ሁሉም የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች፣ አዛውንቶች የሚሰበሰቡባቸው ስፍራዎች እና ልጆች የሚጫወቱባቸው አካባቢዎች፣ ት/ቤቶች፣ ሀይማኖታዊ ተቋማት፣ እና ክፍት ስፍራዎች ንጹህ እና ለመገልገል የሚያመቹ መሆን አለባቸው

- በከፍተኛ ድህነት ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች የፍሳሽና የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ መገልገያዎችን ያካተተ የተሻሻለ ሳኒቴሽን ተደራሽነትን እውን ለማድረግ የታሰበ የተለየ የገቢ እርዳታ አሰባሰብ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህ የማዘጋጃ ( የድጎማ) ፈንድ ለተቸገሩ ዜጎች አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ ግልጽ በሆነ የውል ስምምነት እና አገልግሎቱን አካባቢያዊ በሆኑ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ውክልና አማካኝነት በማድረስ ሂደት በሚመለከተው አካል አማካኝነት ተግባራዊ ማድረግ ይችላል፡፡

- የሳኒቴሽን አገልግሎት አሠራር የተቸገሩትን ለማገዝ እና በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በስራ ፈጠራ ሊሳተፉ ለሚችሉ አካላት የገቢ ምንጭ ሆኖ ማገልገል አለበት፡፡

### 6.7.2. ስርዓተ- ጾታ

የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂው በአጠቃላይ በስርዓተ ጾታ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን የተያዘውን እሴት ያገናዘበ ነው፡፡ ከከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ እና የጤና/ የሴቶች ልማት ቡድን ንቁና ገንቢ ተሳትፎ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂው የሚከተሉትን አላማዎችን ይዟል፡-

- የከተማ ሳኒቴሽን መርሀ ግብሮች እቅድ ላይ የሴቶችን ተሳትፎ መጨመር፤ ይህም በአንጻሩ መብቃትን፣ አካባቢያዊ የባለቤትነት መንፈስን እና ብቃት ለማሳደግ ይጠቅማል

- እንደ የተለየ የሳኒቴሽን መገልገያ እና የወር አበባ ንፅህና መጠበቂያ ያሉ ለሴቶች እና ታዳጊ ልጃገረዶች ፍላጎት የሚያስፈልጉ ለከተማ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን መርሀ ግብሮች ላይ የሚሰጠውን ትኩረት መጨመር፣

- የከተማ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን መገልገያዎችን አዳጊ በሆነ የምጣኔ ሀብት አያያዝ አማካኝነት ሴቶችን ማብቃትና እና አቅማቸውን ማሳደግ፣

- ከሳኒቴሽን እና ሀይጅን ተያያዥ የሆኑ በሽታዎችን ከመከላከል ጋር የተያያዙ የልማት

ስራዎች ላይ ሴቶችና ታዳጊ ልጃገረዶች ተሳታፊ የሚሆኑበትን ዕድል መጨመር

- ከከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮችን በተመለከተ ሞዴል ሴቶችን እንደለውጥ ሰራዊት መጠቀም

- በስርዓተ ጾታ ላይ የሚሰሩ የሴት ማህበራት፣ ፎረሞች እና ባለ ድርሻ አካላት ያላቸውን ተሳትፎ መጨመር

- ሥራ ፈላጊ የሆኑ ሴቶች፣ ትምሕርታቸውን ያቋረጡ ሴት ተማሪዎችና ወጣቶች በግንባታ ስራ፣ በንግድ ሥራ አያያዝ ተግባራት፣ በመጀመሪያ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ሂደት ላይ ከጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ጋር ተሳታፊ በመሆን፣ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ በማዋልና በድግመ-ዑደት (ሪዩዝ) ተግባራት፣ የሕዝብ መጸዳጃ ቤት አገልግሎቶች እና በዓይነ ምድር ዝቃጭ አያያዝ ላይ እንዲሳተፉ የሚያበረታቱ የሥራ ፈጠራ ዕድሎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

## 6.7.3. አካባቢ

ውጤታማ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ለሰው ልጅ ጤና፣ ለኢኮኖሚ፣ እና ማህበረሰባዊ ጥቅም እንዲሁም ስሱ የሆነውን አካባቢያዊ ስነ-ምህዳር ባለበት ሁኔታ ለመጠበቅ ወሳኝነት አለው፡፡ እንዲሁም በውኃ፣ አፈር እና አየር ብክለት ምክንያት የሚፈጠረውን ጉዳት ለመቀልበስ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡

በሳኒቴሽን አገልግሎት ላይ ያሉ አሳሳቢ ችግሮች፤ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስተላለፊያ መሰረተ ልማት እጥረት፣ በከተሞች ውስጥ በየቦታዉ የሚደረግ መጸዳዳት እንዲሁም ከኢንዱስትሪና ንግድ ቤቶች የሚወጣ ቆሻሻ ላይ የሚደረግ የቁጥጥር ማነስ፣ እጅግ አሳሳቢ የአካባቢ ጤና ችግሮችን እያስከተለ ነው፡፡

በአብዛኛም በትላልቅ እና ትናንሽ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ ወንዞች እና ምንጮች የቆሻሻ መጣያ በመሆናቸው ተቅማጥንና ሌሎች በሽታዎችን የማስተላለፊያ መንገዶች ሆነዋል፡፡ በተጨማሪም የውኃ ውስጥ ስነ ምህዳርን በመጉዳት የተበከለ ውኃን የማጣራት፣ የማጽዳት፣ ማናፈስ በካይነቱን የመቀነስ አቅም እንዳይኖራቸው አድርጓል፡፡

በዚህ ስትራቴጂ ውስጥ፤ የተጓደለ የከተማ ሳኒቴሽንና ኢንዱስትሪያዊ እና የንግድ እንቅስቃሴዎች

በአካባቢ ላይ የሚያስከትሉትን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የተለየ ትኩረት ይሰጣል፡-

- የአካባቢያዊ ተጽዕኖ ምዘናዎች (ግምገማዎች) በሁሉም አዲስ የከተማ ቤቶች፣ ተቋማት፣ የንግድና ኢንዱስትሪ እብቅስቃሴዎች ላይ በወጣው አዋጅ መሠረት በሚገባ መፈጸሙን ማረጋገጥ
- በሁሉም የልማት ተግባራት ውስጥ ለአካባቢያዊ ተጽዕኖ ምዘና (ግምገማ) የሚሆኑ አቅርቦቶችና የመከላከያ እርምጃዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ
- የፍሳሽ ቆሻሻ ማከም፣ የፍሳሽ መስመር፣ የውኃ አካላት፣ ስነ ምህዳር እና ሜዳዎች ላይ ቀጣይነት ያለው አካባቢያዊ ምዘና ማካሄድና የብክለት ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉትን ለይቶ ማጣራት
- የአካባቢያዊ ጥበቃ ቅድመ ሁኔታዎች ለሁሉም አዲስ እና ነባር የቤት፣ ተቋማት፣ ንግድ ሥራ እና ኢንዱስትሪ ግንባታዎች ውስጥ ተፈጻሚ መሆኑን ማረጋገጥ
- ነዋሪዎችን ቆሻሻን ከምንጬ እንዲቀንሱና ቆሻሻዎችን በድጋሚ ለመጠቀም ወይም ለድግመ-ውደት በሚያመች መልኩ ለይተው እንዲያጠራቅሙ ማበረታታት
- ፍሳሾችን እና ሌሎች ቆሻሻዎችን ለማስወገድ ደረጃዉን የጠበቀ አሠራርን መከተል ያስፈልጋል፡፡

ለአየር ንብረት ለውጥ የተለየ ትኩረት ሊሰጥ ያስፈልጋል፡፡ ያልተገመተ እና ከባድ የአየር ሁኔታ በከተማ ቦታዎች እድገት፣ በአካባቢ ይዘት እና በጤና ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ በተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂው አማካኝነት የሚዘረጉ ስርዓቶች እና መገልገያዎች የሚከተሉን ለማድረግ የሚያስችሉ መሆናቸው ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ 1) የቤተ እጽ (ግሪን ሃውስ ጋዝ) ልቀትን የሚያስከትለውን ተጽእኖ በመቀነስ በአካባቢ እና በአየር ንብረት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት መቀነስ እና 2) ከአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ ችግር የደረሰባቸው የማህበረሰቦች/ከተሞች መልሶ የመቋቋም አቅም መጨመር ተገቢ ነው፡፡

### 6.7.4. ጤና እና ደህንነት

ስትራቴጂው በከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን አገልግሎት በሚሳተፉ ላይ የሚደርስ ማንኛውም አይነት አደጋ፣ ጉዳት እና በስራ ምክንያት የሚገጥሙ ሕመሞችን ለመቀነስ እና ለማስቀረት ከፍተኛ ጥረት ጥረት እንዲደረግ ያመላክታል፡፡ ከትግበራዎች ጋር የተያያዙ የደህንነት አደጋዎችን ለይቶ ለማውጣት፣ ለማስወገድ ወይም ተገቢውን ጥንቃቄ ለማድረግ የሚከተሉትን ተግባራት በማከናወን ያላሰለሰ ጥረት የሚካሄድ ይሆናል፡-

- በከተማ ሳኒቴሽን አገልግሎት ስራ የሚሳተፉ በጤና እና ደህንነት እንዲሁም ከአገልግሎት አሰጣጡ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አደጋዎችን በተመለከተ ስልጠና ይሰጣቸዋል
- በሥራ ወቅት ደህንነትን ለመጠበቅ በጥቅም ላይ የሚውሉ መሣሪያዎች አቅርቦት እና የአጠቃቀም የአፈጻጸምበሥራ ክንውን ወቅት ለሚፈጠሩ ድንገተኛ ክስተቶች እና አደጋዎች አፋጣኝ፣ ውጤታማ እና እንክብካቤ የታከለበት ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር መገንባት
- ሁሉም አገልግሎት ሰጪዎች ከሙሉ የምርመራ እና ሪፖርት ሥነስርአት ጋር በተቻለ መጠን አደጋን በማያስከትል ሁኔታ ስራቸውን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ አደጋን ከመቀነስ ጋር የሚያያዙ ወጪዎች በተመለከተ ከፊሉ በክፍያ ታሪፍ ውስጥ በማካተት በአቅራቢዎች አማካኝነት ከፊሉ ደግሞ የከተማው አስተዳደር በድጎማ መልክ በሚያደርገው የገንዘብ ድጋፍ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

### 6.7.5. የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ

በሳኒቴሽን አገልግሎት ግንባታ እና አያያዝ እንዲሁም ድግመ-ዑደት ክንውኖች ውስጥ የግሉ ዘርፍ ሊሳተፍ የሚችልበት የተወሰነ ደረጃ አለ፡፡ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ በዋናነት በማማከር፣ የመገልገያዎች ግንባታ እና ቁጥጥር፣ የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ የሳኒቴሽን መገልገያዎችን ማምረት እና ማቅረብ ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ የእነዚህ  ተግባራት ቀጣይነት እንዳለ ሆኖ በሳኒቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የግሉ ሴክተር በተጨማሪ ተግባራት ላይ ተሳታፊ እንዲሆን ለንግድ ሥራ የሚያመች ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት እየተካሄደ ነው፡፡

ስትራቴጂው የግሉ ሴክተር በውል፣ በአቅርቦት ሰንሰለት እና በውክልና የሚሰጥ አስተዳደራዊ

መዋቅር ላይ መንደርደሪያ የሚሆኑ ጉዳዮችን ከግምት ዉስጥ አስገብቷል፡፡ የሰራተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ እና እንዲሁም የሕዝቡም ሆነ የአካባቢ ደህንነት የተጠበቀ እንዲሆን የጤና እና የደህንነት እርምጃዎች መወሰዳቸውን ማረጋገጥ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ በተመሳሳይም የግሉ ዘርፍ በትክክለኛው የደንብ መዋቅር ውስጥ መከናወኑንና አዋጭ ቢዝነስ ማካሄድ መቻሉን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው ቁልፍ የብቃት አመላካቾችን ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚያስችል እና የሚገመግም የአገልግሎት አስተዳደር ውል እና የውክልና አገልግሎት አስተዳደር ውሎች ሲኖሩ ነው፡፡

የግሉ ዘርፍ የሚከተሉትን ጨምሮ በሳኒቴሽን እና ሀይጅን የአቅርቦት ሰንሰለት አብዛኛው ክፍል ውስጥ አመቺ እና ተጠቃሚ ሆኖ ሊሳተፍ እንደሚችል ይታመናል፡-

- በሁለቱም በተጠቃሚ እና ተቋሚዊ ደረጃ የባህሪ ለውጥ ሊያመጡ በሚችሉ እና ግንዛቤ የሚፈጥሩ ጥናቶች እና የተግባቦት ስትራቴጂዎች
- በምርምርና ጥናት
- እንደ ተቋማዊ መሻሻል፣ የፋይናንስ ጥናት እና የንግድ ሥራ እቅድ፣ ማስተር ፕላን፣ የተፈጻሚነት ጥናት፣ ዲዛይን እና ውል ቁጥጥር ባሉ ሰፋ ያሉ ጉዳዮች ላይ የአማካሪነት አገልግሎት ማቅረብ
- ስርዓትን በመዘርጋት እና በመፈጸም ለሰልጣኞቹ እንዲያመች ተደርጎ የተዘጋጀ የአጭር ጊዜ ስልጠና በመስጠት የአቅም ግንባታ ስራ ማከናወን
- የመጀመርያ ደረጃ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ
- ሁለተኛ ደረጃ የደረቅ ቆሻሻ ክምችት፣ መለየት እና ማጓጓዝ
- የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ጣቢያ የሥራ ክንውን
- የድግመ-ዑደት ኢንዱስትሪ
- የመጸዳጃ ቤት፣ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስረጊያ ጉድጓድ፣ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ጋኖች፣ በእጅ ያለ መሣሪያ እገዛ ወይም በሜካኒካዊ ዘዴ በመጠቀም ቆሻሻን የማስወገድ ስራን ማከናወን

- የዓይነ ምድር ዝቃጭን ማከም እና የምርት ግብይት ሂደት
- እንደ በቅድመ-መመረት ደረጃ ያሉ መጸዳጃ ቤቶች እና የመጸዳጃ ቤቶ መገልገያ እቃዎች ያሉ የሳኒቴሽን ግብይት እቃዎችን ማምረት

እያንዳንዱ አሰራር እንዴት የግሉ ዘርፍ ወይም ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በምን ዓይነት መልኩ ቢሳተፉ ጥራት ያለውና ውጤታማ አገልግሎት ሊሰጡ እንደሚችሉ ለማየት የአጠቃላይ የንግድ ሥራ ሞዴል ተግባራዊነት ምዘና ይካሄዳል፡፡

የግሉ ዘርፍ በከተማ ሳኒቴሽን ሰንሰለት ውስጥ እንዲሳተፍ እና የድርሻውን እንዲያበረክት የሚመለከታቸው ባስልጣናት ማለትም እንደ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ድርሻ የሚከተሉት እንዲሆኑ ይጠበቃል፡-

- የግሉ ዘርፍ በሳኒቴሽን ሰንሰለት ውስጥ እንዳይሳተፍ የሚያደርጉ ማናቸውም አይነት ማነቆዎችን መፈተሽ
- ለግሉ ሴክተር ምቹ የሆነ ነባራዊ ሁኔታ ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ የአሰራር መመሪያዎችን ማሻሻል ወይም መፍጠር፡፡ የግሉ ሴክተር ከዚህ በፊት የማይሳተፍባቸው ተግባራት ላይ ለየት ያለ አሠራር ተግባራዊ ይደረጋል
- የተለያዩ የሳኒቴሽን አገልግሎት ይዘቶች በተደራጀ መልኩ እንዲከናወኑ ወይም በአንድ እንዲጠቃለሉ በማድረግ የንግድ ሥራ እድል መፈጠሩን ማረጋገጥ
- የግሉ ዘርፍ የገንዘብ አቅርቦት (ለኢንቨስትመንት ጥቅም የሚውል የተለየ የብድር አገልግሎት አሰጣጥ) እንዲያገኝ በማስቻል፣ የግብር መክፈያ ጊዜን በማራዘም እንዲሁም የሰራተኞችን አቅም በመገንባት ድጋፍ ማድረግ

### 6.7.6. የማኅበረሰብ ተሳትፎ እና ባለቤትነት

የከተማ ሳኒቴሽን አገልግሎት ስኬት በማኅበረሰቡ የተሳትፎ ደረጃ ይወሰናል፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት የማኅበረሰቡን ተሳትፎ ለመጨመር የተለያዩ አሠራሮችን በመፍጠር አስተዋውቋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በሰፊው ተግባራዊ የሆነው የፖለቲካ መሪዎችን እና የአካባቢው ማኅበረሰብ ፊት ለፊት ተገናኝተው ስለሚሰጡ የተለያዩ የፅዳት እና የአካባቢ ጥበቃ አገልግሎቶች፣ ደረጃ እንዲያወጡ፣ በክፍያ አወጣጥ

ላይ ሀሳብ እንዲሰጡ፣ የማኅበረሰብ እንቅስቃሴን እንዲያነሳሱ እና አፈፃፀሙን ክትትል እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ለማጠናከርና ለማስተዋወቅ የጤና ልማት ሠራዊት እና የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች እጅ ለእጅ ተያይዘው ማኅበረሰቡን ማገልገላቸዉን ሊቀጥሉ ይገባል፡፡ ዋነኞቹ የድጋፍ ሥራዎች ፡-ሀ) ማኅበረሰቡ የሳኒቴሽን መሰላል ግንዛቤ እንዲዳብር እና በዚያው መሠረት እንዲተገብር መምራት፣ ለ) የራሳቸውን ሳኒቴሽን መገልገያ እንዲገነቡ እና እንዲያዘጋጁ ማገዝ፣ ሐ) ለቅንጅት፣ ትብብር እና አጋርነት  የለውጥ አራማጅ መሆን፣ እና መ) ንጹህ አረንጓዴና ዘላቂነት ያላቸው መንደሮችና ከተሞችን  ለመፍጠር ኃላፊነትን መዉሰድ የሚጠቀሱ ሥራዎች ናቸው፡፡ አጠቃላይ የሳኒቴሽን ሥራዎችን ለማሳካት በእያንዳንዱ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች በዋናነት የሳኒቴሽን መገልገያዎችን ማሟላትና በጉልበት፣ በገንዘብ እና በቁሳቁስ አቅርቦት ላይ የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሚከተሉት ለማኅበረሰቡ ተሳትፎ የተቀመጡ ስልቶች ናቸው፡-

- በሀይጅን እና ሳኒቴሽን ኮሜቴ ውስጥ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተወካዮች  መኖር አለባቸው፡፡ ዋና ዋናዎቹ ተወካዮችም ከሴቶች ማኅበራት፣ ከወጣቶች ማኅበራት፣ ከአረጋውያን፣ ከግል ሠራተኞች፣ ከግል የንግድ ሥራ ተቋማት፣ ከሕዝብ ተቋማት፣ ከማኅበረሰብ ተቋማት፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት እና ከአካል ጉዳተኞች የተውጣጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

- ማኅበረሰቡ የሕዝብ እና የግል አገልግሎት ሰጪዎችን (በውኃ፣ ፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ) እና ውክልና የተሰጣቸው የአገልግሎት ሰጪዎችን ከአገልግሎት አስተዳደር ውል እና የውክልና አገልግሎት አስተዳደር ውል አንጻር እና በቁልፍ የክንውን አመላካቾች ሥራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን በመመዘንና በመከታተል ጠቃሚ ሚና ይጫወታል፡፡ የተጠቃሚዎችን ቅሬታ እና የመክፈል ፍቃደኝነት በእነዚህ ቡድኖች ክትትል በማድረግ ወጪ ቆጣቢ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲፈጠር ወሳኝ ድርሻ አላቸው፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ ኃላፊነት የሚሰማቸው ቡድኖች ስብሰባዎችን ለመካፈል በሚያስችላቸው መልኩ ከታሪፍ እና የአሰባሰብ ክፍያ ከሚገኘው ገንዘብ ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ወርሃዊ አበል ይቀበላሉ፡፡

- የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት የማኅበረሰቡ ተሳትፎ እና ውክልና ምን ሊመስል እንደሚገባ እንዲሁም የማኅበረሰብ መድረኮችን ለማቋቋም የሚያስችሉ መመሪያዎችን እና ማመሳከሪያ ዝርዝሮችን የማውጣት ኃላፊነት አለባቸው፡፡በተጨማሪም መድረኮቹ በትክክል እየተካሄዱ መሆኑን መከታተል እና ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

- ሁሉም ከተሞች በመመሪያው ላይ ከተዘረዘረው ሁኔታ ጋር በሚስማማ መልኩ የማኅበረሰብ ተሳትፎ መድረኮችን መፍጠር አለባቸው፡፡ ከተሞች የሚጠበቀውን አነስተኛ የሳኒቴሽን ደረጃ ለማሟላት እንዲረዳቸው የማስተዳደር እና የማኅበረሰቡን ተሳትፎ እንዴት  መጠቀም እንዳለባቸው የመወሰን እና ተፈፃሚ የሚሆንበትን ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ሙሉ ስልጣን አላቸው፡፡ የከተሞች የሳኒቴሽን አያያዝ ወይም የአስተዳደር ውጤታማነት በማኅበረሰቡ ግልጽ የተሳትፎ ደረጃ እንደሚወሰን ማወቅ አለባቸው፡፡

### 6.7.7 ዘላቂነት

ዘላቂነት ያለው የሳኒቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ አስፈላጊነት በሁሉም የኢትዮጵያ ከተሞች የሳኒቴሽን ልማት ላይ የሚታይ ቁልፍ ተግዳሮት ነው፡፡ ቀጣይነትን ለማረጋገጥ አጠቃላይ የተቋማዊ፣ ቴክኖሎጂ፣ ፋይናንስ እና አካባቢያዊ አቀራረብ በተላበሰ መልኩ የአገልግሎት ተጠቃሚዎችንና ማኅበረሰቡን ማዕከል ያደረገ የአገልግሎት እድገትን ማምጣትን ይጠይቃል ፡፡

ተቋማዊ ዘላቂነት የተጠቃሚዎችን ሙሉ ተሳትፎ ከምቹ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የደንብ ወይም የቁጥጥር አፈጻጸም ዘዴዎች ጋር የሚያካትት ሲሆን የቴክኖሎጂ ዘላቂነት ደግሞ አስፈላጊ መሣሪያዎችና ቀሳቁሶች እንዲሟሉ የአገልግሎት ሰጪዎችን ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡የፋይናንስ ጥናት ከሚሰጠው አገልግሎት ደረጃ፣ ተመጣጣኝ የሆነ ታሪፍ እንዲሁም የህዝብ አገልግሎት ዘላቂነትን ያማከለ ክፍያ ጋር በተያያዘ የንግድ ሥራውን አዋጭነት ለመተንተን የሚያስችል ሲሆን፣ አካባቢያዊ ዘላቂነት ደግሞ በአካባቢ ጥበቃ ሕጎች እና መመሪያዎች አማካኝነት ከአካባቢያዊ አስተዳደር ዕቅድ ጋር መጣጣም ማለት ነው፡፡

ዘላቂነት ለሥራ፣ ጥገና እና መልሶ ማልማት ከሚውለው አቅርቦት መጠን እና በጥቅም ላይ ከሚውለው የፋይናንስ ስርዓት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው፡፡ መንግስት ላቀረበው የሕዝብ አገልግሎት የወጪ ሽፋና እንዲካሄድ የሚፈልግ ቢሆንም፤ እውነታው ግን ለደረቅ ቆሻሻ፣ የዓይነ ምድር ፍሳሽ አሰባሰብ፣ ማከም እንዲሁም ማስወገድ ተብሎ የሚወጣው ታሪፍ እና ክፍያ ከአጠቃላይ ወጪው

ጥቂት ክፍልፋይ ብቻ የሚሸፍን መሆኑ ነው፡፡ አብዛኞቹ የውኃ አቅርቦት ተቋማት ለውኃ አቅርቦት የሚያወጡትን ወጪ እንኳ ለመሸፈን ይከብዳቸዋል፡፡ ነገር ግን የንጹህ ውኃ አቅርቦት ተጠቃሚ ለመሆን እና ለዚህም አገልግሎት ክፍያ የመክፈሉ ፍቃደኝነት ለሳኒቴሽን ካለው ፍላጎት የበለጠ ነው፡፡ ስለዚህ የውኃ አቅርቦት አገልግሎት መሻሻል ሳኒቴሽንን ለመደጎም ምቹ መንገድን ይፈጥራል፡፡ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ተቋማት የሁለቱም የውኃ እና ሳኒቴሽን አገልግሎቶች የማቅረብ ኃላፊነት ያለባቸው ስለሆኑ የውኃ አቅርቦት ከተሻሻለ (ለምሳሌ በተደራጁ ማዘጋጃ ቤቶች) በአካባቢያዊ ደረጃ ከውኃ አቅርቦት የሚገኘው ገቢ የሳኒቴሽን ወጪዎችን ለመደጎም ይረዳል፡፡

ቁልፍ የዘላቂነት ስትራቴጂዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ሁለቱም የፋይናንስ እና አካባቢያዊ ዘላቂነት ሶስቱን የቆሻሻ አወጋገድ ስልቶች ማለትም ይዘቱን በመቀነስ-፣ መልሶ መጠቀም፣ ድግመ ዑደት አማካኝነት ተፈጻሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ዘላቂነት ያለው የአገልግሎት አቅርቦት በከፍተኛ ሁኔታ የሚወሰነው በእጅጉ በወጪ ቆጣቢ ሆኖም ግን ሥራ በጥብቅ ሊከናወን በሚችልባቸው ዘዴዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ በሚገኙ አካባቢያዊ ማከሚያ እና ማዘዋወሪያ ጣቢያዎች የሚደረገውን ጉዞ ማሳጠር፣ ብዙ ኃይል የማይፈልግ የማከም ሂደት፣ አካባቢያዊ መልሶ መጠቀም፣ ግልጽ የሆነ ንዑስ የሥራ ተቋራጭነት ሁኔታ እና ጥብቅ ተፈጻሚነት ባላቸው ደንቦች አማካኝነት ነው፡፡

- ዘላቂነት ያለው የሳኒቴሽን አገልግሎት አቅርቦት ከአጭር እስከ መካከለኛ ጊዜ ድረስ እርዳታ፣ ብድር እና ድጎማ እንደሚያስፈልገው ይጠበቃል፡፡ ይህም ማለት ዘላቂነቱ በተወሰነ መልኩ በሳኒቴሽን አገልግሎት ገቢ ከማይተዳደሩ የገቢ ምንጮች በሚገኝ የረዥም ጊዜ የድጋፍ እና የድጎማ ስምምነት ላይ ይወሰናል ማለት ነው፡፡

- የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂ ሁሉም የዘርፉ ተሳታፊዎች በሁሉም ጥናት እና ፕሮግራም አፈፃፀሞች ለዘላቂነት ቅድሚያ እንዲሰጡ ያበረታታል፡፡

- ልዩ ልዩ ኃላፊነት ያለባቸው የፌዴራል እና ክልል ተቋማት ከግሉ ዘርፍ ጋር በመተባበር ዘላቂነት ባለው እና በተገቢው መልኩ በሁሉም የአሠራር ሂደት ውስጥ እንዲካተት በየደረጃው ያሉ የመንግሥት አወቃቀሮችን የቴክኒክ እና አስተዳደራዊ አቅም ይገነባሉ፡፡

- በሁሉም ከተሞች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማሻሻልና ስምምነት ከተደረሰባቸው አነስተኛ ደረጃዎች በለጥ ወደሚል ደረጃ አገልግሎቱን ለማድረስ በቂ በጀት መመደብና ሁሉም የሚያስፈልጉ የቴክኒክ ሥራዎች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡ የፌዴራልና ክልል መንግሥታት ከተሞች እንዴት የማኀበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ ጥናት እንዲሁም ፋይናንስ ትንተና እንደሚያደርጉ እና ከተጠቃሚው የመክፈል አቅም ጋር አገልግሎቱ የሚጣጣምበት ደረጃ ላይ ለማድረስ ምክር ይሰጣሉ፡፡ የሳኒቴሽን አገልግሎት ክንውን እና የሳኒቴሽን የመገልገያዎች ጥገና ወጪ ቢያንስ በሚገኘው ገቢ እና ስምምነት በተደረገባቸው የድጎማ ሥርዓቶች ድምር መሸፈን አለበት፡፡

- ከተሞች የከተማ ሳኒቴሽን ደረጃዎችን ከሀገሪቷ የሳኒቴሽን ደረጃ እና አማራጭ ጋር በሚጣጣም ሁኔታ ያወጣሉ፡፡ የሚመለከታቸውና ኃላፊነት ያለባቸው የፌዴራል እና ክልል ተቋማት ለከተሞች ዘላቂነት ወይም ቀጣይነት ያለው፣ አቅምን ያገናዘበ እና ተቀባይነት ያላቸው የሳኒቴሽንና ሃይጅን አቅርቦቶችን የማስተዋወቅ ሥራዎችን ይሠራሉ፡፡

- በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ላይ ላሉ እና ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተገቢ የሳኒቴሽን አገልግሎት እንዲኖር ለማስቻል የሳኒቴሽንና ሃይጅን መገልገያ ድጎማዎች በየአካባቢያዊው የአገልግሎት መስጫ ደረጃ ተግባራዊ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡ በውክልና በሚሰጡ ክንውኖች ውስጥ የአካባቢው አስተዳደር ባልደረቦች ተሳታፊ መሆናቸው ከፍተኛው እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ግለሰቦች እና ቤተሰቦች ለመለየት ያግዛል፡፡

- የማኀበረሰብን የባለቤትነት ስሜት ለመፍጠር በከተማ ሀይጅን እና ሳኒቴሽን ጉዳይ አጠቃላይ ሂደት ማለትም በዕቅድ ዝግጅት፣ በአፈፃፀም፣ በክትትልና ግምገማ ላይ ማኀበረሱን ማሳተፍ ያስፈልጋል፡፡

## 6.8. ፋይናንስ ለሳኒቴሽን እና የታሪፍ ትመና

### 6.8.1. ፋይናንስ ለሳኒቴሽን

ፋይናንስ ለሳኒቴሽን ተለይተው በተወሰኑ መርሆች እና ማበረታቻዎች ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡ ሳኒቴሽን በሕዝብ እና በግሉ ዘርፍ ላይ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ ማኀበራዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ

ጥቅሞች አሉት፡፡ ምንም እንኳ የቆሻሻ አይነታቸው ቢለያይም እና በማስወገድ ሂደት ላይ የሚያወጡት ወጪ በቂ ባይሆንም ቤተሰቦች፣ ተቋማት፣ የንግድ ድርጅቶች እንዲሁም ኢንዱስትሪዎች የቆሻሻ ምንጮች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በመኖሪያ ቤቶች፣ ተቋማት እና ኢንዱስትሪዎች አማካኝነት የሚሸፈነው ወጪ አብዛኛውን ጊዜ ለክምችት እና ማጓጓዝ አገልግሎት የሚውል ነው፡፡

የወጪ ቆጣቢ እርምጃዎች፣ የሥራ ኃይልን የሚፈልጉ ተመራጭ ቴክኖሎጂዎችን በጥቅም ላይ መዋል እንዲሁም የንግድ ሥራ ዕቅድ የላኛውን የሳኒቴሽን ሰንሰለት (ደረቅ ቆሻሻን ቤት ለቤት እየሄዱ መሰብሰብ እና የጉድጓድ መጸዳጃዎችን እና ማጠራቀሚያ ጋኖችን ማጋባት/) እንዲሁም አካባቢያዊ የዓይነ ምድር ዝቃጭ አወጋገድን ተገቢ፣ ተመጣጣኝ ታሪፍ እና ክፍያ ባለበት እና የገንዘብ ድጋፎችን በውጤታማነት መሰብሰብ እና መጠቀም በሚቻልበት ሁኔታ - በአጭር ጊዜ ከገንዘብ አንጻር አዋጪ እንደሚያደርጋቸው ይታሰባል፡፡ ነገር ግን ብዙ ካፒታል በጀት የሚያስፈልጋቸው የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶች፣ የደረቅ ቆሻሻ የማዘዋወሪያ ጣቢያዎች፣ ሁለተኛ ደረጃ የረጅም ርቀት ማጓጓዣ፣ አግባብ ያለው የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ፣ ማእከላዊ ያልሆነ የቆሻሻ ውኃ እና የዓይነ ምድር ዝቃጭ ሕክምና፣ እንዲሁም የፍሳሽ ማስተላለፊያ እና ማከሚያ ወጪዎችን ሙሉ በሙሉ ለመሸፈን ረጅም ጊዜ ይወስዳል፡፡

ይህ ስትራቴጂ ለሳኒቴሽን አገልግሎት ዑደት የሚያስፈልገውን የገንዘብ አቅም እንዴት ማግኘት እንደሚቻል አቅጣጫ ያመላክታል፡፡ ለአጠቃላይ የሳኒቴሽን ሰንሰለት ወጪ ከአንድ ምንጭ ብቻ የሚገኝ ሳይሆን ከተለያዩ ዘዴዎች ነው፡፡ የሚከተሉት የከተማ ሳኒቴሽን ወጪዎች ሊሸፈኑ የሚችሉባቸው ስልቶች ናቸው፡-

- ሁሉም ባለድርሻ አካላት የራሳቸው ድርሻ የመወጣት እና የሚያወጡትን የቆሻሻ መጠን መቀነስ እንዳለባቸው ማሳወቅ፤ “የበከለው አካል መክፈል አለበት” የሚለው መርህ በሁሉም የከተማ ሳኒቴሽን ሰንሰለት ተፈጻሚ እንዲሆን በማድረግ፡፡

- በአሁኑ ጊዜ የሳኒቴሽን አገልግሎቶች የሚሠጡት በኪሳራ በመሆኑ ለመካከለኛ ጊዜ የሚዘልቅ በተለይ ለመነሻ ወጪዎች (capital costs) ድጎማ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የሳኒቴሽን መነሻ ወጪዎች በተለይም ለማከሚያ እና የሳኒቴሽን ማብላያ ተቋማት የሚሆነው ወጪ ቀደም ብሎ ለፍሳሽ ማስተላለፊያ እና ፍሳሽ ማከሚያ ሰሚውለው በተጠቀሰው አግባብ እርዳታና ብድርን ይፈልጋሉ፡፡

- የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ለተወሰነ ጊዜ በቀጥታ ከሚሰበሰበው ገቢ የሚበልጡ ሲሆን፣

ወጪውን ለመሸፈን ድጎማ በማድረግ የተወሰነውን ክፍል መሸፈን ወይም ለመክፈል ፈቃደኝነት ባለበት ስፍራ የወጪ መጋራት ዘዴን ተግባራዊ ማድረግ

- በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና በመንደር/ቀበሌ አመራሮች የተረጋገጠ እና በተለየ ሁኔታ እጅግ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ፣ በከባድ የአካል ጉዳተኝነት ወይም በሌሎች ተመሣሣይ አሉታዊ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ ካልሆነ በስተቀር በመርህ ደረጃ ለመኖሪያ ቤቶች መጸዳጃ ቤት ግንባታ ድጎማ አይሰጥም፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የከተማው ምክር ቤት "በእራሱ ስልጣን" ድጎማ ለመውሰድ የሚያበቁ ቅድመ ሁኔታችን በማዘጋጀት የተሻሻለ የሀይጅን እና ሳኒቴሽን የገንዘብ አቅርቦት ያዘጋጃል፡፡

- በቤተሰብና በተቋማት የሳኒቴሽንና ሃይጅን መገልገያዎችን እንዲገነቡና እንዲያሻሽሉ ለማበረታታት አነስተኛ ብድሮችን እና የተለዩ ስጦታዎች ከማድረግ ባሻገር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መሥራት ይገባል፡፡ አነስተኛ የብድር እና ቁጠባ አቅራቢ ተቋማት እና ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የገንዘብ አቅርቦትን ለማመቻቸት እና ከምጣኔ ሀብት አንጻር ተመጣጣኝ የሆኑ እና ማኅበረሰባዊ ተቀባይነት ያላቸው አገልግሎቶችን እውን ለማድረግ የድርሻቸውን እንዲወጡ የሚተሣሠሩበት መንገድ መፍጠር፡፡

- ለክላስተርና ለነጠላ ከተሞች የሚደረግ የከተማ ሳኒቴሽን የገንዘብ አቅርቦት ምደባ ከሕዝብ ሀብት ተወዳዳሪያዎች በሚያቀርቡት የድጋፍ መጠየቂያ ቅጽ ጥራት እና ቀጣይነት ያለው የአገልግሎት ተደራሽነትን ለማስፈጸም ያለውን የአያያዝ እና የክንውን ተነሳሽነት ግምት ውስጥ በማስገባት ለውድድር የሚቀርብ ይሆናል፡፡ የገንዘብ አቅርቦት ጨረታ ማመልከቻ አቅራቢው ተወዳዳሪ፣ ከፍተኛ ደረጃ ያለው የፕሮግራምና ፕሮጀክት ዝግጅት ሊኖረው የሚያስፈልግ ሲሆን፣ ዝግጅቱም የምጣኔ ሀብት፣ የማኅበራዊ፣ የፋይናንስ እና የታሪፍ ጥናቶችን ያካታትል፡፡ ይህንንም ለማሳካት ስትራቴጂው የተደራጁ ማዘጋጃ ቤቶችን ለማገዝ የሚያስፈልጉ የቴክኒክ እገዛ መስጠትን ያካትታል፡፡

- ሁሉም የተቀናጁ የከተማ ሳኒቴሽን ፕሮግራሞች የተጠቃሚውን አቅም፣ የመክፈል ፍቃደኝነት እና ለገንዘብ የሚሰጠውን አመለካከት ግምት ውስጥ በማስገባት የሁሉንም የአገልግሎት አሰጣጥ አማራጮችን (እያንዳንዱ በራሱ ወጪ) ለማመጣጠን የፋይናንስ

ትንተና እንዲሠሩ ይጠበቃል፡፡

- በፋይናንስ ትንተና ውጤት መሰረት ኃላፊነት ለተሰጣቸውና በተናጠል ወይም በቡድን ሥራዎችን በሚያከናውኑ አካላት አማካኝነት የሚሠራ ለእያንዳንዱ የሳኒቴሽን ሰንሰለት ትግበራ የሚያገለግል የንግድ ሥራ ዕቅድ ይቀርባል፡፡ ይህ የንግድ ሥራ ዕቅድ የዋጋ ቅናሽን መሠረት በማድረግ የቀጣይነት አገልግሎትን ዓላማ የሚያሟላ፣ ከጤና እና አካባቢያዊ ግቦች ጋር የሚጣጣም እና ዝቅተኛ የሆነውን የተጠቃሚውን ፍላጎት የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

- ለከተማ ሳኒቴሽን የሚመደበው በጀት የሚወሰነው በሚቀርበው ዕቅድና የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን ስትሪንግ ኮሜቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት በፌዴራል የገንዘብ እና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፣ በክልል የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ወይም በከተማው ምክር ቤት አማካኝነት ይሆናል፡፡

- ለጋሾች፣ የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች የሁለትዮሽ/ብዙኃን ለጋሾች ጥምረት አካላት ከፌዴራል የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፣ ከክልል የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ እና የከተማ ምክር ቤቶች ጋር ድጋፍ ለማድረግ የተስማሙበትን የበጀት መጠን መክፈል ይጠበቅባቸዋል፡፡ መንግሥት በተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽንና ሃይጅን ሥራዎች ላይ የሚወጣውን ወጪ እና የተመደበውን በጀት በቀላሉ ለመከታተል እንዲመች ከጠቅላላ በጀት በቀመር ለሳኒቴሽንና ሃይጅን በጀት የሚመደብበት መንገድ መፍጠር አለበት፡፡ ይህም የከተማ ፕሮግራሞች ላይ የሚሳተፉና የሚያስተዳድሩ የሕዝብ ተቋማትን እንደሚያግዝ ይጠበቃል፡፡

- የንብረት ባለቤትነት ጉዳይ በከፍተኛ ደረጃ የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ የውኃ እና ሳኒቴሽን ግንባታ አቅርቦቶች (ቋሚ ንብረቶች) መንግሥት የወከለው የከተማው አስተዳደር ንብረት ይሆናሉ ስልጣኑ የተሰጣቸው የሕዝብ አገልግሎት አቅራቢዎች ወይም ሠራተኞች ንብረቶቹን በውል ስምምነት መሰረት ባለቤቱን ወክለው ያስተዳድራሉ፡፡ አገልግሎት አቅራቢዎቹ/ሠራተኞቹ እንደ መኪና፣ የማከሚያ ኬሚካሎች እና የመሳሰሉት ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ባለቤት ናቸው፡፡

- የውኃ ሀብት ልማት ፈንድ የተመሰረተው[6] የውኃ ሀብትንና የሳኒቴሽን ፕሮጀክቶችን “የወጣውን ወጪ ሊተካ በሚችል(Cost recovery principle)” መርህ መሰረት ፋይናንስ ለማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ለመሆን የሳኒቴሽን ፕሮጀክቱ በፋይናንስ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችል እና ከምጣኔ ሀብት አንጻር ምክንያታዊ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የውኃ ሀብት ልማት ፈንድ ለከተማ ሳኒቴሽንና ሃይጅን ምንጭነት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡ የክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ እና የግል ዘርፎች ድጋፍ ለቅርንጫፍ ማዘጋጃ ቤቶችና ለከተሞች የውኃ አገልግሎት የፕሮፖዛል ዝግጅት ድጋፍ በማድረግ ከውኃ ሀብት ልማት ፈንድ ብድር እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡

- የከተማ ሳኒቴሽንና ሃይጅን ቁልፍ ማነቆዎችን ለመፍታት መንግሥት የሳኒቴሽን ገንዘብ ማፈላለጊያ ቢሮ ማቋቋም ሊያስፈልገው ይችላል፡፡የዚህ የሳኒቴሽን ገንዘብ ማፈላለጊያ የአሠራር ሥርዓትም ከሌሎች የገንዘብ ማፈላለጊያ የአሠራር ሥርዓቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ማጥናት ያስፈልጋል፡፡

- ለአጭር ጊዜ ስምምነት ተደርሶባቸው ለተዘጋጁ የንግድ ሥራ ሞዴሎች የሕዝብ እና የግል አጋርነትን በመጠቀም ተጨማሪ ሀብት ማፈላለግ ይቻላል፡፡

- የከተማ ሳኒቴሽንና ሃይጅን ችግሮችን ለመፍታት በማኅበረሰብ ውይይት ወይም የማኅበረሰብ ምክክር መድረኮችን የገንዘብ ድጋፍ ማፈላለጊያ ዘዴ አድርጎ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

### 6.8.2. ለከተማ ሳኒቴሽን ታሪፍ ትመና

የሚከተሉት የከተማ ሳኒቴሽን ታሪፍ ትመናን ለመወሰን ተግባራዊ የሚሆኑ መሠረታዊ ስራቴጂዎች ናቸው፡-

- የከተማ ሳኒቴሽን የታሪፍ ትመና እንደየአካባቢው ሁኔታ የተለየ መሆን አለበት፡፡ የሳኒቴሽን ታሪፍ የሚወሰነው በፋይናንስ ትንተና፣ በአገልግሎቱ ደረጃ የመከፈል አቅም፣ በድኅማ መኖር እና ደረጃ እንዲሁም በተጠቃሚዎች የመክፈል ፍቃደኝነት (በአገልግሎቱ ጥራት መሰረት) ነው፡፡

[6] አዋጅ ቁጥር 581/2008፣ የውሃ መዋለ ንዋይ ልማት ፈንድ መመስረቻ እና ማስተዳደሪያ አዋጅ

- ታሪፍ የሚሰጡ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ አገልግሎቶችን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡ በተጨማሪ ለአገልግሎቱ የመክፈል አቅም የሌላቸውን (ለምሳሌ በማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ጥናት መሰረት በመጨረሻው ደረጃ "የመክፈል አቅም" ላይ ያሉ) ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

- ለድሃ ወይም ለተቸገሩ ሰዎች የሚሰጡ የአገልግሎት ክፍያዎች የሚሸፈኑት ከማኅበረሰቡ በታሪፍ ከተሰበሰበው ወይም በማዘጋጃ ቤት ከሚገኙ ከተለያዩ የገንዘብ አቅርቦቶች አማካኝነት ይሆናል፡፡

- የተለያዩ ዓይነት አገልግሎቶች የተለያየ ታሪፍ ያላቸው ሲሆን የሚሰበሰቡበት መንገድም ለሁሉም ተጠቃሚ ግልጽ መሆን አለበት፡፡ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቱቦዎች ክፍያ በሜትር የተለካ የውኃ አጠቃቀም ላይ የተመሠረተ መሆኑ የተለመደና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን የፍሳሽ መምጠጥ አገልግሎት ክፍያ የሚወሰነው በአጠቃላይ በሚለቀቀው መጠን፣ በሚተላለፍበት ቦታ/ማከሚያ ርቀት ወይም በሚወገድበት ቦታ እና በማከሚያ ወጪ መሰረት ነው፡፡ እንዲሁም የደረቅ ቆሻሻ ክፍያ የሚወሰነው በብዛት፣ ዓይነት፣ የሚሰበሰብበት ጊዜ ተደጋጋሚነት እና ተፈጻሚነት ነው፡፡

- የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ታሪፍ የሚጣለው በቀጥታ በሚሰበሰብበት ስፍራ ወይም ከሌሎች የማዘጋጃ ቤት ክፍያዎች ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ታሪፉ የሚሰበስቡትን ሰዎች ጤና እና ደህንነት እንዲሁም በእያንዳንዱ የሰንሰለት ደረጃ የሚወጣውን ወጪ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

- የተለዩ ታሪፎች የፍላጎት እና ውጣውረድ የተሻለ ግንዛቤ ባላቸው በአካባቢው የሚገኙ የሥራ አስፈጻሚዎች በሚወከል የክንውን አካል አማካኝነት በተሻለ ሊተዳደር ይችላል፡፡

- የታሪፍ ለውጥ የሚደረገው ከተጠቃሚ ተወካዮች ጋር በሚደረግ ምክክር እና በከተማው ምክር ቤት ወይም በተወከሉ ባለስልጣናት በሚሰጥ ሙሉ ፍቃድ ነው፡፡

## 6.9. የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂን ለመፈፀም የሚያስፈልጉ ተቋማዊ አደረጃጀቶች

የከተማ ሳኒቴሽን ተቋማዊ አደረጃጀት የከፍተኛ ደረጃ ኃላፊዎችን ትብብር፣ቅንጅትና ስምምነት

በፌደራል፣ በክልልና በከተማ ደረጃ ያስፈልጋል፡፡ በሁሉም ደረጃ ያሉ ተቋማዊ አደረጃጀቶች የፈፃሚዎችንና የተቆጣጣሪዎችን ሚና እና ኃላፊነት በግልጽ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂ ፈራሚ ሚኒስትሮች (የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፣ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ፣ የዉሃ መስኖና ኤክትሪክ ሚኒስቴር እና የአከባቢ ደንና የአየር ለዉጥ ሚኒስቴር) የቅንጅት ሥራዎችን በመፍጠር ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም እንደ ባህልና ቱሪዝም፣ ኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ የሴቶች እና ወጣቶች ጉዳይ ያሉ ዘርፎች የራሳቸውን አስተዋጾ ያደርጋሉ፡፡ በሁሉም የአስተዳደር ደረጃዎች ግንባር ቀደም ተቋሞች ሀገራዊ ወይም ክልላዊ የበላይ አመራር ኮሚቴ እና የቴክኒክ አማካሪ ቡድን በማቋቋም የዕቅድ፣ የበጀት ዝግጅት የአፈፃፀም ሥራዎችን በማየትና በመከታተል ውሳኔዎችን ይሰጣሉ፡፡

በፌዴራል ደረጃ ስልጣን እና ኃላፊነት በግልጽ ለማስቀመጥ እንዲረዳ በተሳታፊ አካላት መካከል የፌዴራል የስምምነት ሰነድ መፈረም አለበት፡፡ ጥራት ያለው አገልግሎትን ለማረጋገጥ እና ከተቀመጡ ደረጃዎች ጋር ለመጣጣም የደንብ እና አስፈጻሚ አካላት በፌደራል፣ ክልል እና ከተማ ደረጃዎች ሊቋቋሙ ይገባል፡፡

ሀገራዊና ክልላዊ የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂ የበላይ አመራር ከሚቴዎች የከተማ ሳኒቴሽን መረጃዎችን ለማሻሻል ቁልፍ አካላት ናቸው፡፡ በከተማ ደረጃ የሚፈለገውን ለውጥ ለማምጣት በብሔራዊ የአንድ ቋት የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ፕሮግራም እና ከአስፈላጊ ዘርፍ መሥሪያ ቤቶች ለምሳሌ የከተማ ማኅበራት ጋር በቅርበት መሥራት ያስፈልጋል፡፡ የባለድርሻ አካላት ዝርዝር ሚና እና ኃላፊነት በተዘጋጀው ስልታዊ የትግበራ እቅድ እና የመግባቢያ/ስምምነት ሰነድ ላይ በግልጽ ይቀመጣል፡፡ ነገር ግን መሰረታዊው መዋቅር ከዚህ በታች እንደተገለጸው ይሆናል፡-

| | |
|---|---|
| ሰብሳቢ | በመጀመርያ ስብሰባ ላይ የሚወሰን ሲሆን የጤና ዘርፍ የመጀመሪያውን ስብሰባ ለመጥራት መሪነቱን ይወስዳል |
| ፀሀፊ | በመጀመሪያው የኮሚቴ ስብሰባ ላይ ይወሰናል |
| አባላት | ጤና፣ ውኃ መስኖና ኤሌክትሪክ፣ ከተማ ልማት እና ቤቶች፣ አካባቢ ጥበቃ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ፣ እና ባህልና ቱሪዝም |
| ተጋባዥ ተሳታፊዎች | የልማት አጋሮች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ዩኒቨርስቲዎች እና ሌሎች |

| | |
|---|---|
| ሚና እና ኃላፊነት | • በከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን አስተዳደር ላይ የሴክተር ለሴክተር ግንኙነት/ተሳትፎ እንዲኖር የተለያዩ መድረኮችን ማመቻቸት<br>• ሀገራዊ/ክልላዊ የስትራቴጂ ልማት ዕቅድን እና የዓመታዊ ቋት የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ዕቅድ እና በጀትን መገምገምና ማጽደቅ<br>• አጠቃላይ ስምምነት የተደረገባቸውን ሥራዎችና የተቀመጡ መለኪያዎችን አፈፃፀም መመልከት/መገምገም<br>• በሀገር አቀፍ፣ ክልል፣ ከተማ እና ቀበሌ ደረጃዎች ተፈጻሚ የቅንጅት የአሠራር ሥርዓቶች መፈጠራቸውን ማረጋገጥ<br>• በከተማ ሳኒቴሽን አስተዳደር የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማሻሻል የሚቋቋሙ ጠንካራ ሀገር አቀፍ ተቋሞች እና ስርዓቶችን መምራት<br>• በዓመት ሁለት ጊዜ የሚደረጉ ስብሰባዎች፣ ውይይቶች እና መሻሻሎች መፈጸማቸውን ማረጋገጥ<br>• እንደ ብሔራዊ አንድ የውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሀይጅን ፕሮግራም የተቀነጀ ሃይጅንና ሳኒቴሽን ስትራቴጂ ከሌሎች አስፈላጊ ዘርፎች ጋር ከፍትኛ ቅንጅት መኖሩን ማረጋገጥ<br>• ለከተማ ሳኒቴሽንና ሃይጅን ተመጣጣኝ የሆነ ሀብት መመደቡንና እና ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ |

በሥራ ላይ የሚገኙ የዘርፍ የቴክኒክ የሥራ ቡድኖች እንዲሁም አዳዲስ የሚቋቋሙ አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ቡድኖች መረጃ ለማጋራት፣ ለከፍተኛ ውሳኔ ሰጪዎች የቴክኒክ ድጋፍ ለማድረግ እና አጠቃላይ የቅንጅት ሥራዎችን ለመሥራት ያስችላሉ፡፡

ዋነኛ የከተማ ሳኒቴሽንና ሃይጅን ኃላፊነቶች በከተማ አስተዳደሮች ላይ ያርፋል፡፡ በከተማ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶችን የማቀናጀት እና የማቅረብ አስፈላጊ ሁኔታዎችን የመፍጠር እና የመምራት

ሚና የከተማው ከንቲባ/የከተማ አስተዳደር/ ወይም የከተማው ማኔጀር ይሆናል፡፡ ቁልፍ ሥራዎች ከስር በሰንጠረዡ ላይ ተገልጸዋል፡-

| | |
|---|---|
| ሰብሳቢ | የማዘጋጃ ቤት ከንቲባ ወይም ተወካይ |
| የጸሐፊ አባል | የጤና ቢሮ ኃላፊ |
| አባላት | የውኃ አገልግሎት አቅራቢ፣ የትምህርት ቢሮ፣ የፋይናንስ ቢሮ፣ ከተማ ልማትና ቤቶች ቢሮ፣ የሴቶች ማኅበራት፣ የወጣቶች ማኅበራት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅት ተወካዮች፣ የልማት አጋሮች፣ የንግዱ ማኅበረሰብ፣ የጤና ተቋማት ተወካዮች እና አነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት ኃላፊዎች |
| | • ጎልተው የሚታዩ የሃይጅንና ሳኒቴሽን ተግዳሮቶችን ለማስወገድ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ጉዳዩችን እንዲሁም የልማት ዕቅዶችን መተንተን<br>• በሳኒቴሽን ማሕቀፍ መሪ ዕቅድ ሰነድ መሰረት የበጀት፣ የጋራ የድርጊት መርሐ ግብር ዕቅድና ኃላፊነቶችን ያካተተ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ማስተዋወቂያ ሥራዎችን ይፋ ማድረጊያ የአጭር እና ረጅም ጊዜ ዝርዝር ዕቅድ ማዘጋጀት<br>• በከተሞች ለሚገኙ ማኅበረሰቦች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ጤናና ሌሎች ተቋማትን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመከታተልና ተጨማሪ የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት የክትትል ቡድን ማቋቋም<br>• ለሥራዎች ቀጣይነትና አፈፃፀም የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድና ሥራዎችን መከታተል |

| | |
|---|---|
| ሚና እና ኃላፊነት | • ዓመታዊ የስትራቴጂክ ዕቅድ/ የድርጊት መርሐ ግብር እና አጠቃላይ የሳኒቴሽን በጀትን በከተማው ምክር ቤት እንዲጸድቅ ማቅረብ<br>• አስፈላጊው መረጃዎችን እና ውሳኔዎችን ለማጋራት ከክልል የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን አስተባባሪ ኮሚቴ ጋር መቀናጀት<br>• ለፕሮግራሙ ውጤታማነት የሀብት ማፈላለጊያ እና የባለድርሻ አካላት ትንተና መሥራት<br>• የፕሮግራም ዕቅድ ለማዘጋጀትና እና የዘርፍ ሥራዎችን አፈፃፀም ለመገምገም  በየሩብ ዓመቱ ስብሰባ ማካሄድ<br>• እንደአስፈላጊነቱ የግኝት እና የፈጠራ ሥራዎችን በመጠቀም የሃይጅንና የሳኒቴሽን ሥራዎች እንዲጠናከሩ ማድረግ<br>• የክልሉ የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ማስተባበሪያ ቢሮ ከብሔራዊ የአንድ ቋት የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ፕሮግራም ጋር የሚጣጣሙ ተጨማሪ ሥራዎችን  በማውጣት መተግበር |

የከተሞች ተቋማዊ አደረጃጀት እንደ ከተማው ስፋት እና ከተማው ይሰጠዋል ተብሎ እንደሚፈለገው የአገልግሎት አይነት ይለያያል፡፡ ነገር ግን የፌዴራል መንግሥት እና የክልል መንግሥታት ተቋማት ከተሞች አቅማቸውን ያገናዘበ ተቋማዊ አደረጃጀቶችን እንዲመሰርቱ የማገዝ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የክልል የቴክኒክ  የሥራ ቡድን በተለያዩ የከተማ ክላስተሮች ደረጃቸውን የጠበቁ ተቋማዊ አደረጃጀቶችን እንዲያዘጋጁ መሪነቱን ሊወስዱ ይችላሉ፡፡

በቀበሌ ደረጃ ተመሳሳይ መዋቅር በሚከተለው ሰንጠረዥ መሰረት መመስረት አለበት፡-

| | |
|---|---|
| ሰብሳቢ | የቀበሌ ሊቀመንበር/የቀበሌ አስተዳዳሪ |
| ጸሐፊ | ለቀበሌ ጤና ኬላ የተመደበች የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ |
| አባላት | የውኃ አገልግሎት፣ የትምህርት ቢሮ፣ የከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደርና አረንጓዴ ቢሮ፣ የጤና ልማት ሰራዊት፣ የሴቶች ማኅበር፣ የወጣት ማኅበር፣ የንግድ ማኅበረሰብ፣ የጤና ተቋማት፣ አነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት ተወካዮች |
| ሚና እና ኃላፊነት | • የቀበሌ የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን መረጃዎችን ማዘጋጀትና ወቅታዊ ማድረግ<br>• ጎልተው የሚታዩ የሃይጅንና ሳኒቴሽን ተግዳሮቶችን ለማስወገድ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ጉዳዮችን እንዲሁም የልማት ዕቅዶችን መተንተን<br>• በሳኒቴሽን ማሕቀፍ መሪ ዕቅድ ሰነድ መሰረት የበጀት፣ የጋራ የድርጊት መርሐ ግብር ዕቅድና ኃላፊነቶችን ያካተተ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ማስተዋወቂያ ሥራዎችን ይፋ ማድረጊያ የአጭር እና ረጅም ጊዜ ዝርዝር ዕቅድ ማዘጋጀት<br>• በቀበሌ ለሚገኙ ማኅበረሰቦች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ጤናና ሌሎች ተቋማትን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመከታተልና ተጨማሪ የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት የክትትል ቡድን ማቋቋም |

| | |
|---|---|
| | • ለሥራዎች ቀጣይነትና አፈፃፀም የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድና ሥራዎችን መከታተል<br>• ዓመታዊ የስትራቴጂክ ዕቅድ/ የድርጊት መርሐ ግብር እና አጠቃላይ የሳኒቴሽን በጀትን በከተማው ምክር ቤት እንዲጸድቅ ማቅረብ<br>• አስፈላጊው መረጃዎችን እና ውሳኔዎችን ለማጋራት ከክልል የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን አስተባባሪ ኮሚቴ ጋር መቀናጀት<br>• ለፕሮግራሙ ውጤታማነት የሀብት ማፈላለጊያ እና የባለድርሻ አካላት ትንተና መሥራት<br>• የፕሮግራም ዕቅድ ለማዘጋጀትና እና የዘርፍ ሥራዎችን አፈፃፀም ለመገምገም በየሩብ ዓመቱ ስብሰባ ማካሄድ<br>• በየቀበሌዎች ማኅበረሰቡ ስለሃይጅንና ሳኒቴሽን አገልግሎቶች ለመወያየት የሚያስችል የማኅበረሰብ የምክክር መድረክ ማዘጋጀት<br>• እንደአስፈላጊነቱ የግኝት እና የፈጠራ ሥራዎችን በመጠቀም የሃይጅንና የሳኒቴሽን ሥራዎች እንዲጠናከሩ ማድረግ<br>• የከተማዉ የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ማስተባበሪያ ቢሮ ከብሔራዊ የአንድ ቋት የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ፕሮግራም ጋር የሚጣጣሙ ተጨማሪ ሥራዎችን በማውጣት መተግበር |

ያለውን የገንዘብ አቅርቦ በአግባቡ ለመጠቀም እና ከአገልግሎት አቅርቦቱ ስራውን በማብዛትና የሚኘውን ትርፍ በመጨመር ጠቀሜታ ለማግኘት፤ የውኃ አቅርቦትን ያካተተ የተሻሻለ የሳኒቴሽን አገልግሎት አቅርቦት የተቀናጀ እቅዶች ለማቅረብ የአካባቢው ክላስተር በፍቃደኝነት ላይ ተመስርቶ ትላልቅና ትናንሽ ከተሞችን እንዲያካትት ይበረታታል፡፡ የመንግስታዊ እና ኢንተርናሽናል ፋይናንሺያል ኢንስቲቲዩሽን ልገሳዎችን እና ቀጣይነት ያለው ብድርን የሚሰቡ ቀጣይነት ያላቸው የፕሮጀክት እና አያያዝ/ኦፐሬሽን መዋቅሮችን እንዲያመጡ ስትራቴጂው የአካባቢውን አደረጃጀት የሚረዱ የውጪ ቴክኒካል እርዳታ እንዲያቀርቡ ይፈቅዳል፡፡

የከተማ ሳኒቴሽንን አስተዳደር ለማሻሻል ሊያግዙ የሚችሉ ማንኛውም የተቋማት አማራጮች ለምሳሌ

እንደ አገልግሎት አስተዳደር ኮንትራት ወይም ከግሉ ዘርፍ የተወከሉ አስተዳደሮች፣ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና እንደ የውኃ አቅራቢ ያሉ አገልግሎት አቅራቢ አደረጃጀት አይነቶችን ጥልቅ ጥናት ከተደረገባቸው በኋላ ተቀባይነት ኖሮዋቸው ወደ ሥራ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ውሳኔዎችም በፌደራል፣ ክልል እና ከተማ ደረጃ ባሉ የከተማ ሳኒቴሽን አስተባባሪ አካላት የሚደረግ ይሆናል፡፡

የጥቃቅንና የአነስተኛ ኢንተፕራይዞች እንዲሁም የግል ዘርፍ ሠራተኞች በፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ላይ ያላቸው ተሳትፎ እንደ ሥራ ፈጠራ ክፍል ይበረታታል፡፡

በክልል እና ከተማ ደረጃ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ የቆሻሻ አስተዳደር ስርዓት እና የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አስተዳደር የሚመራው በባለሙያ፣ በድርጅት እና ገለልተኛ በሆኑ የፋይናንስ ተቋማት አማካኝነት ሲሆን ተጠያቂነታቸው ለቦርድ ይሆናል፡፡ የሥራውን መጠን በመጨመር ትርፋማነትን በማሳደግ የሚገኙ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ እና የሰው እና ቁሳዊ ሀብትን ለመጋራት፤ የዋና ከተሞች የአደረጃጀት ማመልከቻዎች እና የአነስተኛ ከተሞችን ውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ለማገናኘት፤ በምህንድስና፣ በግዢ፣ ክፍያ፣ የላብራቶሪ አገልግሎት፣ ስልጠና፣ የሰው ኃይል አስተዳደር፣ የፕሮጀክት ዝግጅት ጋር መፈጸም አለበት፡፡

ያልተማከለ የሃይጂን እና ሣኒቴሽን የአገልግሎት አሰጣጥን በአግባቡ ለመፈፀም ዋና ዋና ኃላፊነቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የፍሳሽ ቆሻሻ እና የዓይነ ምድር ዝቃጭን ማከም የሚሠራው በከተማው የውኃ አቅራቢ ነው፡፡ የውኃ አቅራቢዎች የሚጠበቅባቸውን ሚና ለመወጣት መዋቅራቸውን እና ሰራተኞች አቅማቸውን እንዲያሻሽሉ ይጠበቃል፡፡ ብዙ ሰው በሚኖርባቸውን በትልልቅ ከተሞች ላይ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ጥቅም እና ጉዳትን ከግምት ውስጥ በማስገባት እና ዝርዝር ጥናት በማድረግ የተቋማዊ አደረጃጀትን መለያየት ይቻላል፡፡

- በከተማ ደረጃ የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አስተዳደር ሥራ የከተማው ማዘጋጃ ቤት ሥራ ሲሆን፤ እንደ ከተማው ደረጃ ለደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ/አሐድ ወይም መሪ ይኖራል፡፡ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር የሚመለከተው ተቋም ከውኃ አቅርቦት አገልግሎት እና ከጤና ቢሮ ጋር በቅርብ እንዲሰራ ይጠበቃል፡፡ በከተማው አስተዳዳሪ ወይም ተወካይ የሚመራ እና የከተማ ውኃ አቅራቢ እና ሳኒቴሽና እና የጤና ቢሮ የተወከሉበት ቦርድ መኖር አለበት፡፡

- ሀይጅንና ሳኒቴሽንን የማስተዋወቅ እና የተግባቦት ሥራዎች የጤናው ዘርፍ ሚና ሲሆን በከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አማካኝነት ይፈፀማል፡፡ የሚሠሩ ሥራዎችን ውጤት ለማሳደግ፣ ቀስ በቀስ የተቋማትን ጥራትና አገልግሎትን ለማሻሻል እና ቁልፍ ተግዳሮቶችን ለመለየት የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በማኅበረሰቡ ውስጥ ከቀበሌ አስተዳደሮች፣ ከውኃ አቅራቢዎች እና ከደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር አሐድ ጋር በቅርበት እንዲሠራ ይጠበቃል፡፡

- የደንብ እና አፈጻጸም ሥራ በዋነኛነት በአካባቢ ጥበቃ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ዘርፍ እና በምግብ መድኃኒት የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣ እና በጤና ዘርፍ የሚሠራ ይሆናል፡፡

የሚከተለው ሰንጠረዥ በተለያዩ ደረጃዎች ያሉትን ተቋሞች ዝርዝር የሥራ ድርሻ እና ኃላፊነት ያሳያል፡-

| | ተቋማት/ አጋሮች | ሚና እና ኃላፊነት |
|---|---|---|
| | በፌደራል ደረጃ | |
| 1 | የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር | በሀገር አቀፍ ደረጃ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ትግበራን ከታች የተገለጹት ተግባራት ላይ ትኩረት በማድረግ ማቀናጀት እና መከታተል ይጠበቅበታል፡-<br>• በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አማካኝነት ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መሥራት<br>• በሰው ኃይል ልማት፣ በግብዓት፣ በሳኒቴሽን መገልገያ እቃዎች አቅርቦት እና የመሳሰሉትን በሚመለከት የአቅም ግንባታ ሥራዎችን መሥራት |

| | | |
|---|---|---|
| | | • በቤተሰብ፣ በጤና እና በሌሎች ተቋማት የሃይጅንና የሳኒቴሽን መገልገያዎችን ግንባታ ማሳደግ<br>• ከሌሎች ዘርፍ መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር/ በመወያየት የተለያዩ ደረጃዎችን ማውጣት<br>• የከተማ ሳኒቴሽንና ሃይጅን ዕቅድ ለማዘጋጀት፣ እድገትን ለመከታተልና የቁጥጥር ሥራዎችን ለመሥራት ስምምነት በተደረሰባቸው መለኪያዎች መሰረት፤ በኅብረተሰብ ጤና ላይ መረጃ መሰብሰብ እና እድገቱን መከታተል |
| 2 | የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር | • በሀገር አቀፍ ደረጃ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ትግበራን ማስተባበርና እና መከታተል<br>• የሰው ኃይል የአቅም ግንባታ ሥራዎችን መሥራት፣ መልካም ተሞክሮዎችን ማጋራት<br>• ከሌሎች ዘርፍ መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር/ በመወያየት የተለያዩ ደረጃዎችን ማውጣት<br><br>በሀገር አቀፍ ደረጃ የውኃ አቅርቦት፣ የፍሳሽ ቆሻሻ እና የዓይነ ምድር ዝቃጭ አያያዝ ትግበራን ማስተባበርና መከታተል ዋና ዋና ተግባራቱም:- |

| | | |
|---|---|---|
| 3 | የውኃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር | • ብሔራዊ የአንድ ቋት የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ፕሮግራምን ማስተባበር (የበላይ አመራሩ ኮሚቴዎች ሌላ ሚኒስትሪ እንዲያዘጋጅ እና እንዲያስተባብር ሀሳብ እስከሚያቀርብ ድረስ)<br>• መደበኛ የፍሳሽ አገልግሎት በሚሰጥበት እና የቆሻሻ ውኃን ሽፋን ለማፋጠን የቆሸሸ ውኃን በማከም ለከተማ ግብርና፣ ግንባታ፣ የመኪና እጥበት ወዘተ ለመጠቀም የሚያስችል ያልተማከለ የቆሻሻ ውኃን ማከሚያ ስርዓትን ማስተዋወቅ<br>• ባዮ ጋዝ ማምረት እና ከበሽታ አምጪ ተህዋስያን ነጻ የሆነን የደረቀ የዓይነ ምድር ዝቃጭ ለአፈር ማበልጸጊያነት መጠቀም የሚያስችሉ አካባቢያዊ የዓይነ ምድር ዝቃጭ ማከሚያ እና በምህንድስና የተዘጋጁ የዓይነ ምድር ዝቃጭ ማምረቻ መደቦች አዘገጃጀትን ማስተዋወቅ<br>• የውኃ አካላት ጥበቃን ጨምሮ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ማካሄድ<br>• በደረጃዎችን በማውጣት ሂደት ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ |
| 4 | የአካባቢ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር | በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጡ የሳኒቴሽን አገልግሎትን የተመለከቱ የአካባቢያዊ ደረጃዎች ላይ ያተኮሩ ደንቦችን አፈጻጸም ማስተባበር እና መቆጣጠር |

| | | |
|---|---|---|
| 5 | የባህል እና ቱሪዝም ሚኒስቴር | በቱሪዝም ማዕከላት የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ደረጃዎችን ለማሟላት ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በሕብረት መሥራት |
| 6 | ዩኒቨርስቲዎች እና የምርምር ተቋማት | ዩኒቨርስቲዎች በሳኒቴሽን ላይ የሚሰሩ የተለያዩ ተቋማትን በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊያሳትፉ እና ሊያግዙ ይችላሉ፡-<br>• ፍላጎትን መሠረት ያደረጉ እስከ ሶስት ወር ድረስ የሚወስዱ ስልጠናዎችን ማዘጋጀት<br>• ዩኒቨርስቲዎቹ በሚገኙበት አካባቢ ለከተሞች የቴክኒክ እገዛ የሚደረገበትን መንገድ ማመቻቸት እና ማስተባበር<br>• ትግበራ/ውጤት ተኮር የሆኑ ምርምሮችን ማከናወን<br>• በልዩ ልዩ አማካሪዎች የሚዘጋጁ ጥናቶች እና ንድፎችን ለመገምገም ድጋፍ ማድረግ |
| 7 | ሌሎች ተቋማት/ አጋሮች | በተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ስትራቴጂ ድርጊት መርሐ ግብር ዕቅድ ላይ በተለዩ ጉዳዮች እና በዋና ዋና ባለ ድርሻ አካላት አማካኝነት በተፈረመ የጋራ ስምምነት የተለዩ ሚናዎችን መጫወት |

| በክልል ደረጃ | | |
|---|---|---|
| 8 | የውኃ ሀብት ልማት ቢሮ | • ለሳኒቴሽን ዕቅድ ዝግጀት፣ አፈፃፀም፣ ክትትል እንዲሁም የሳኒቴሽን አገልግሎት አሰጣጥን ለመከታተል ለከተሞች ውኃ አገልግሎት ስልታዊ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያግዛል፡፡<br>• አዳዲስ አካሄዶችን ማስተዋወቅ፣ በጀት ማፈላለግና አፈፃፀሙን ማገዝ<br>• የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የቆሸሸ ውኃ አወጋገድና የውኃ አቅርቦትን የተመለከቱ መመሪያዎችን እና ደረጃዎችን ማውጣት፣ በሥሩ ካሉ ተቋማት ጋር በመተባበር ስልጠናዎችን ማካሄድ<br>• የቆሸሸ ውኃን ጥራት በመተንተን እና ለውጦችን ከጊዜ ወደ ጊዜ በመከታተል የውኃ አገልግሎቶችን ድጋፍ ማድረግ፤ እንዲሁም የትንተናውን ሪፖርት ማጋራት |

| | | |
|---|---|---|
| 9 | የጤና ቢሮ | • ከፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሚጠቅሙ መመሪያዎችንና ባህሪ ለውጥ ተግባቦት መሳሪያዎችን ማጣጣም<br>• በክልል ከተሞች ተፈፃሚ የሚሆኑ የከተማ ሳኒቴሽን መገልገያ ተቋማት ደረጃዎችን፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎችን እንዲያዘጋጁ ኃላፊነቱ ያለባቸውን የክልል ተቋማትን ማስተባበር<br>• መሠረታዊ የመረጃ ስርዓትን ለማቋቋም፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፣ በጤና ተቋማት፣ በሴቶች የልማት ሰራዊትና ማኅበረሰቡን መሠረት ባደረጉ የተለያዩ ስርዓቶች ሥራዎችን ለመሥራት ጤና ቢሮ ባለሙያዎች ስልጠናዎችን ማካሄድና የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን መሥራት<br>• የተገኙ ስኬቶችን እንዲሁም የተስተዋሉ ተግዳሮቶችን ለመገምገም የሚያግዙ ስብሰባዎች በዓመት ሁለት ጊዜ እንዲካሄድ ማስተባበር<br>• ክልላዊ የተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን የበላይ አመራር ኮሚቴን ማስተባበር |

| | | |
|---|---|---|
| 10 | የትምህርት ቢሮ | • በሁሉም የክልል ከተሞች ት/ቤቶች የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን አገልግሎት አቅርቦት መኖሩን ማረጋገጥ<br>• የከተማ የትምህርት ጽህፈት ቤቶች ከከተማው ሳኒቴሽን አያያዝ አገልግሎት ጋር የሚጣጣም የት/ቤት የውኃ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን አገልግሎት ደረጃዎችን እንዲያወጡ እገዛ ማድረግ<br>• በትምህርት ቤቶች የሚሰጠውን አገልግሎት በጥራት እንዲያከናውኑ እና ደረጃውን ጠብቆ እንዲቀይ ለማድረግ እንዲችሉ የሚያግዝ የክትትል ስርዓት መፍጠር<br>• የት/ቤት የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን መገልገያ ተቋማትን የተመለከተ የመረጃ ስርዓት መዋቅር (ዳታቤዝ) ማዘጋጀት እና የትምህርት መረጃ ሥርዓት አስተዳደር ሥርዓት አካል ማድረግ<br>• በት/ቤት ሳኒቴሽን ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች ስልጠና ማዘጋጀት<br>• ትምሕርት ቤቶች እንደ ዓይነ ምድርን ማስወገድ፣ ደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ እና ሌሎች ተመሣሣይ አገልግሎት ዓይነቶችን የሚያገኙበትን አሠራር መቀየስ |

| | | |
|---|---|---|
| 11 | የንግድ፣ ኢንዱስትሪ እና ከተማ ልማት/ የከተማ እቅድ ቢሮ | • በክልል ደረጃ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ አፈጻጸምን ማቀናጀት እና መቆጣጠር<br>• የሰው ሃይል አቅም ግንባታ እና የመልካም ተሞክሮዎች ልምድ ልውውጥ ማካሄድ<br>• ከሌሎች ዘርፎች ጋር በመመካከር ደረጃዎችን ማውጣት<br>• የቆሻሻ አወጋገድ የከተማ ልማት ማስተር ፕላን እና የአካባቢያዊ የልማት እቅዶች አካል መሆኑን ማረጋገጥ<br>• ከተሞች በሳኒቴሽን አቅርቦት እና አገልግሎት ላይ የመረጃ መዋቅር ስርዓት (ዳታ ቤዝ) እንዲመሰርቱ ማገዝ እና መከታተል |
| 12 | የአካባቢ ጥበቃ ቢሮ | • በክልል ደረጃ ከሳኒቴሽን አገልግሎት ጋር ግንኙነት ያላቸው የአካባቢያዊ ደረጃ ደንቦችን ማቀናጀት እና መከታተል<br>• በከተማ ደረጃ የከተማ ሳኒቴሽን ደንቦች፣ ግምገማ እና ክትትል የሚያካሂዱ ተቋማት መኖራቸውን ማረጋገጥ<br>• በከተማ ደረጃ ተፈጻሚ የሚሆኑ የሰው ሀይልን የማሳደግ አቅም ግንባታ፣ በከተማ ደረጃ ተግባራዊ የሚሆኑ የደንብ እና የግምገማ አፈጻጸሞችን አቅም ግንባታ መከታተል<br>• በማስተዋወቅ እና ትግበራ ላይ ኃላፊነት ካለባቸው ሌሎች የዘርፉ አካላት ጋር በትብብር የሚሰራበትን የስራ አካሄድ መቀየስ |

| | | |
|---|---|---|
| 13 | የጤና ሳይንስ ኮሌጆች | • ደህንነቱን የጠበቀ የዓይነምድር አወጋገድ፣ የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ፣ የሳኒቴሽን ቴክኖሎጂ፣ መልሶ መጠቀም እና የመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ለአያሌ ተደራሽ ቡድኖች የሚሰጡ ስልጠናዎችን ማገዝ |
| 14 | የቴክኒክ እና የሙያ ተቋማት | • የከተማ ውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን የትምህርት መርኃ ግብር ላይ ትኩረት በማድረግ መሥራት |
| 15 | የልማት አጋሮች/ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | • የገንዘብ እርዳታ በማቅረብ እና አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦችን በማመንጨት የከተማ አስተዳደሩን ማገዝ<br>• የብድር እና ቁጠባ ሰጪ ተቋማት ለማኅበረሰቡ፣ በሴቶች አማካኝነት ለሚተዳደሩ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም ለውጣቶች ቡድን ቀላል የብድር አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል ተመላሽ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ማገዝ<br>• ማኅበረሰቡ የተገለጹትን ዓይነት ልዩ ልዩ ቆሻሻዎች እንዲያስወግድ የሚያግዙ የውሀ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣ ተግባራዊ ማድረግ እና ማስተዋወቅ<br>• ማህበረሰቡ በሁሉም የውሀ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ጉዳዮች ላይ ራሱን እንዲችል ማገዝ<br>• ስልጠናዎችን ለኢንተርፕራይዞች፣ የእጅ ሙያ ላላቸው ሠራተኞች፣ ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ ለጤና ልማት ሠራዊቶች በማቅረብ ማገዝ |

| | | |
|---|---|---|
| 16 | የብድርና ቁጠባ አገልግሎት አቅራቢ ተቋማት | • በቁጠባ እና ቀላል ብድር አካሄዶች የማህበረሰቡን፣ በሴቶች አማካኝነት የሚተዳደሩ ኢንተርፕራይዞች እና ወጣት ቡድኖች የትግበራ አቅም በቁጠባ እና የቀላል ብድር አማካኝነት ማበረታታት |
| **በከተማ ደረጃ** | | |
| 17 | የከተማ አስዳደሮች | • በከተማ ደረጃ የስትራቴጂውን አፈጻጸም ማስተባበርና  እና መከታተል<br>• አቅርቦቶችን መመደብ እና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን መቆጣጠር<br>• ነዋሪዎች በሳኒቴሽን አገልግሎት ማደግ ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑበት እና ሂደቱን የሚደግፉበት እድል እንዲኖራቸተው የሚያስችል መድረክ መኖሩን እና በአግባቡ የሚከናወን መሆኑን ማረጋገጥ |
| 18 | የውኃ አገልግሎት ሰጪዎች | • ደህንነቱ የተጠበቀ ለመጠጥ የሚሆን የውኃ አቅርቦት፣ የቆሸሸ ውኃ እና ዓይነ ምድር አወጋገድ አገልግሎቶችን ተደራሽነትን ማሻሻል |
| 19 | የጤና ቢሮዎች | • በከተማ የጤና ኤክስቴንሽን መርሀ ግብር አማካኝነት የባህሪ ለውጥ በማምጣት እና የሀይጅን እና ሳኒቴሽን መገልገያ ተቋማትን ዘላቂ ጥቅም በማስተዋወቅ ማኅበረሰቡ እና ተቋማት የሳኒቴሽን እና ሀይጅን መገልገያ ተቋማት አገልግሎት ተጠቃሚነታቸውን ከማሻሻል አንጻር ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ |

| | | |
|---|---|---|
| 20 | የትምህርት ጽሕፈት ቤቶች | • በትምሕርት ቤት የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ክበባት አማካኝነት ከማህበረሰቡ ጋር ንቁ ግንኙነት በማድረግ በትምሕርት ቤቶች ውስጥ የሳኒቴሽን አገልግሎት ተደራሽነት እንዲሻሻል እና የባህሪ ለውጥ እንዲመጣ አስተዋጾ በማድረግ ቁልፍ ሚና አላቸው:: |
| 21 | የፋይናንስ ቢሮዎች | • በተከታታይ የገንዘብ አቅርቦትን አፈላልጎ በማቅረብ እና የፋይናንስ አያያዝ ላይ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ |
| 22 | የከተማ ልማት ቢሮ/ ማዘጋጃ ቤት | • የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድን ከከተማው ማስተር ፕላን ጋር በየጊዜው ማናበብና ማሻሻል ይጠበቅባቸዋል:: |
| 23 | ማህበረሰቡ | • ማህበረሰቡ በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን መርሀ ግብር እና ሌሎች የመጀመሪያ ጤና ክብካቤ  አሐድ ባለሙያዎች አማካኝነት በሚቀበለው መመሪያ መሰረት፣ ከሚመለከታቸው አካላት በሚገኝ የግንባታ ፍቃድ እና በየከተማው በሚገኝ የሳኒቴሽን ግብይት መሰረት የራሳቸውን መጸዳጃ ቤቶች ይገነባሉ/ያሻሽላሉ |
| 24 | ተቋማት | • ተቋማት በአካባቢው አስተዳደር በተቀመጠው ደረጃ መሰረት መጸዳጃ ቤቶቻቸውን ይገነባሉ/ያሻሽላሉ |

| | | |
|---|---|---|
| 25 | አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች፣ ሴቶች ወይም የወጣቶች ቡድን | • የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆን እና አስፈላጊውን ስልጠና በመውሰድ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ አቅማቸውን ያጠናክራሉ<br>• በሕዝብ መጸዳጃ ቤቶች እና የሕዝብ መታጠቢያ ቤቶች አያያዝ እና የድግመ-ውደት ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ |
| 26 | መካከለኛ ኢንተርፐራይዞች | • የደረቅ ቆሻሻ ከቆሻሻ ማከማቻዎች ተወስዶ ቆሻሻ ተቀብሮ ወደ ብስባሽ ወደሚለወጥባቸው ስፍራዎች እንዲጓጓዝ የሁለተኛ ደረጃ የመጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣሉ |
| 27 | ሌሎች | • በተቀናጀ የከተማ ሳኒቴሽን እና የአንድ ቋት ውሀ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ብሄራዊ መርሀ ግብር መሰረት እንዲከናወኑ የሚፈለጉ ስራዎች ላይ ተሳታፊ ይሆናሉ |

## 6.10 የደንብ አፈጻጸምና ተግባራዊነት

የከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ደንብ ውጤታማ እንዲሆን ከፍተኛ የአፈጻጸም ብቃት ያስፈልጋል፡፡ የሕዝብ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ዘርፍ ባለ ድርሻ አካላት (በተለይም በከተሞች ደረጃ የሚገኙት) ተግባራዊ እንዲሆኑ በየደረጃው የወጡ ደንቦች፣ አፈጻጸማቸውን እና የአፈጻጸም ክትትል ዘዴዎችን በሚገባ ሊገነዘቡ ያስፈልጋል፡፡

የወጡ ደንቦች አፈጻጸም ከየኢንዱስትሪዎቹ ጋር በተናጠል በሚደረግ ውይይት ላይ የተመሰረተ ስምምነት እና በሕግ አስፈጻሚ አካላት አማካኝነት በግልጽ በተቀመጠ የቅጣት ድንጋጌ የሚደገፍ "የበከለ ይከፍላል" መርሆን በመተግበር ተፈጻሚ ሊሆን ያስፈልጋል፡፡

ከወጡት ደንቦች ጋር እኩል ጥቅም ያላቸው ነገር ግን ተፈጻሚ ያልሆኑ ደንቦች ማለትም የቤት/

ተቋም ባለቤቶች የተሻሻለ የሀይጅን ባህሪን የሚያንጸባርቁ የተሻሻሉ የሳኒቴሽን ተቋማት እና/ወይም አገልግሎቶች ይኖሩ ዘንድ መዋዕለ ነዋይ ማፍሰስ የሚጠበቅባቸው መሆኑን የሚያመላክቱ ፈራሚ በሆኑ ሚኒስቴሮች አማካኝነት የተረቀቁ ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት ለሚያጋጥሙት እነዚህን እና ተመሳሳይ ተግዳሮቶች መፍትሔ ለመፈለግ የሚከተሉት ተግባራት ዓይነተኛ ናቸው፡-

- በከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ላይ የወጡትን ደንቦች ነቅሶ ማውጣትና ባሉት ክፍተቶች እና የአፈጻጸም ድግግሞሾች ላይ የመፍትሔ እርምጃ መውሰድ
- በአፈጻጸም ስልቶች እንዲሁም እነዚህን ደንቦች በታችኛው የመዋቅሩ ክፍል ላይ ተፈጻሚ የሚያደርጉ ኃላፊነት ያለባቸው ተቋማትን በተመለከተ ስምምነት ላይ መድረስ
- ለከተማ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን የዘርፍ ባለድርሻዎች እና ለማኅበረሰቡ እንደ በካይ ይከፍላል ያሉ መርሆች ያሉ ደንቦችን እና የአፈጻጸማቸውን ሂደት በተመለከተ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ መርኃ ግብሮችን ማዘጋጀት

## 6.11 ግምገማና ምዘና

ግምገማ ያለውን የመሻሻል ሂደት ለመከታተል እና ፣ በዘርፉ ሊተገበሩ የሚቻሉ ውሳኔዎችን እና አቅርቦቶችን ለማፋጠን ያስችላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የግምገማ ውጤቶች ተጨማሪ አቅርቦቶችን የማስገኘት አቅም ይኖራቸዋል፡፡ ከታች ከተገለጹት በሀገር እና ክልል ደረጃ የተቀናጁ ጥረቶች ባሻገር፣ በፈቃደኝነት በተደራጁ ማዘጋጃ ቤቶች አማካኝነት የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች ሁሉ ለሁለቱም ተጠቃሚ ተቋማት እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉ ተቋማት መረጃን የሚያስጨብጡ የግምገማና ምዘና መዋቅሮችን እንዲያካትቱ የቴክኒክ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

ግምገማና ምዘና ለሚያስገኘው ጥቅም እውቅና ከመስጠትና የሳኒቴሽን ዘርፉ ተአማኒ እና ዘላቂ የሆነ የግምገማና ምዘና ስርዓት ባለ መኖሩ የተነሳ የሚገጥሙትን ተግዳሮቶች በመገንዘብ የሚከተሉት ስልቶች ተግባራዊ ይሆናሉ፡-

- የከተማ ሳኒቴሽን ግምገማና ምዘናው ከእያንዳንዱ አባወራ አንስቶ እስከ ፌደራል ድረስ በሁሉም ደረጃዎች ተሳታፊ በሆነ ተቋማት አማካኝነት ሊካሄድ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ተቋማት የከተማ ሳኒቴሽንን ለመገምገም እና ለመመዘን የሚያስችል አንድ አሐድ ወይም ክፍል ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በልዩ ልዩ ክፍሎች ትብብር ስምምነት ላይ

በተደረሰባቸው ጠቋሚዎች፣ የብቃት ደረጃዎች እና የጊዜ ሰሌዳዎች አማካኝነት መረጃን መለዋወጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ዓመታዊው የዘርፈ ብዙ ባለ ድርሻ አካላት ፎረም ከአብዛኛው የዘርፉ የግምገማ ሂደት ጋር በተጣጣመ መልኩ ዓመታዊ ክትትል እና ሪፖርት ተግባራዊ እንዲሆን ማመቻቸታቸውን ይቀጥላሉ፡፡ እንደዚህ ያሉት በከፍተኛ ደረጃ የሚካሄዱ ስብሰባዎች የዘርፉ ንዑሳን ክፍላት በስልታዊ የትግበራ ዕቅዱ በተቀመጡት ግቦች መሠረት በየደረጃው በሚያዘጋጇቸው ዓመታዊ የክንውን ዘገባዎች የታገዙ ይሆናሉ፡፡

- በየከተማው፣ ክልል እና ፌደራል ደረጃ በሚገኘው እያንዳንዱ መዋቅር ድጋፍ የታከለበት ማማከርና ቁጥጥር ማካሄድ የእያንዳንዱን ሠራተኛ ብቃት እንዲሁም፣ ሁሉም ባለ ድርሻ አካላት የተቀመጡ ግቦችን ተግባራዊ ከማድረጋቸው፣ የተዘረዘረው ትግበራ እና ቁልፍ አመላካቾች ከመከወናቸው አንጻር እጅግ ጠቃሚ ነው

- ሁሉም ተቋማት ግምገማ እና ምዘናውን ለማካሄድ ሠራተኞችን ለይተው መመደብ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ግምገማና ሪፖርት እንዲያጠናቅሩ የሚመደቡ ሠራተኞች ተገቢው ስልጠና ሊሰጣቸው እና በየደረጃው ምን ዓይነት ቅድመ-ሁኔታ እንዳለ ሊገነዘቡ ያስፈልጋል፡፡

- በየደረጃው ሊሰበሰብ የሚያስፈልገው የመረጃ ዓይነት በየ ደረጃው በሚገኙት ተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሊሆን ያስፈልጋል፡፡ መረጃው በየደረጃው ያለውን መረጃ አጠቃልሎ ለማቅረብ በሚያመች መንገድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

- በከተማ ወይም በንዑስ ከተማ ደረጃ የመረጃ መዋቅር ስርዓት (Data base) ሊኖር ያስፈልጋል፡፡ ስትራቴጂው በሁሉም ከተሞች ተግባራዊ በሚሆንበት ጅማሬ ቀጣይ እድገትን ለመገምገም የሚያስችል የመረጃ መዋቅር ስርዓት(Data base) ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡ ሁሉም የልማት አጋሮች እንዲሁም መንግሥት ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አቅርቦት ሊያዘጋጁ ያስፈልጋል፡፡

- የግምገማና ምዘና ስርዓቱ ሊያተኩርባቸው የሚገባ አቅጣጫዎች የገንዘብ፣ ተቋማዊ፣ ቴክኒካዊ፣ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሲሆኑ፣ ለየ ሁኔታው ተገቢ የሆኑ ዕድገትን አመላካች ጠቋሚዎች በተግባር ላይ ይውላሉ

- መመሪያዎች ተዘጋጅተው እስከ ታችኛው የመጨረሻ መዋቅር ድረስ ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባል፡፡ መመሪያዎች የእድገት ጠቋሚዎችን እና ከመሰብሰብ አንስቶ መልሶ እስከ መጠቀም ድረስ የመረጃ አሰባሰቡን ገጽታ፣ እንዲሁም እያንዳንዱ ተቋም ያለውን ሚና እና ኃላፊነት በግልጽ የሚያስቀምጡ መሆን አለባቸው፡፡

- የግምገማና የምዘና ስርዓቱ ቀድሞ ካሉት እንደ ጤና የግምገማ ስርዓት፣ ብሔራዊ የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ግምገማ፣ የአንድ ቋት የውሀ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ብሔራዊ የግምገማና ምዘና መድረክ፣ ሀገር-አቀፍ ቅኝት እና ግምገማ ስርዓት እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ከሚካሄደው የዘርፈ ብዙ ባለ ድርሻ አካላት የውይይት መድረክ እና ዘርፈ ብዙ አቀፍ የምዘና ሂደት ጋር ተስማሚ ሊሆን ያስፈልጋል፡፡

- ግምገማና ምዘናው የልማት እቅዱ አካል እና ክፍል ሲሆን፣ ሌሎቹን የልማት ክንውኖች ያገናዘበና ተገቢው አቅርቦት የተመደበለት ሊሆን ያስፈልጋል፡፡ የግምገማ አመላካች የሚሆነው የብሄራዊ መረጃ አይነት ከብሄራዊ አንቀሳቃሽ ኮሚቴው ጋር በመስማማት የሚወጣ ሊሆን ያስፈልጋል፡፡ ይበልጥ ዘርዘር ተደርጎ የሚቀመጠው ለመረጃ በሚመለከታቸው ወሳኝ የፌዴራል ተቋማት አማካኝነት ሊተዳደር እና ሊሰራጭ ይችላል፡፡

- ውጤታማ የሆነ የቅስቀሳ እና እቅድ ሂደት እንዲከናወን ለማስቻል ቁልፍ የሀይጅን እና ሳኒቴሽን ቅድሚያ አመላካቾች የውሀ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ምዘናዎችን በየዕለቱ በማከናወን በብሔራዊ የሳኒቴሽን እና ሀይጅን ግብረ ኃይል አማካኝነት ሊተገበር ያስፈልጋል

- በየከተማዎቹ ለሚገኘው የሳኒቴሽን አገልግሎት የሪፖርት ቅጽ በማዘጋጀትና በየጊዜው ክለሳ በማካሄድ ብሔራዊ የሀይጅን እና አካባቢ ጤና ግብረ ኃይሉ ወይም በወኪልነት የሚሰራው አካል የውሀ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን ምዘናዎችን በየወቅቱ ሊያከናውን እና የሳኒቴሽን ዋና ዋና አመላካቾች ላይ ክትትል ሊያደርግ ያስፈልጋል፡፡

# ማጣቀሻዎች


1. AAWSA (2002) Wastewater Masterplan. Volume I Executive Summary.
2. Addis Continental Institute of Public Health. (2014). "Situational Analysis of Urban Sanitation and Waste Management". Commissioned for John Snow, Inc. (JSI)
3. Central Statistical Agency. (2011). "Ethiopia Demographic and Health Survey", Preliminary Report, Addis Ababa, Ethiopia.
4. Central Statistical Agency. (2011). "Ethiopia Demographic and Health Survey", ICF International, Claverton, Maryland, USA.
5. Central Statistical Agency [Ethiopia]. 2014. Ethiopia Mini Demographic and Health Survey 2014. Addis Ababa, Ethiopia.
6. Chattisgarth Urban Sanitation Strategy. (2010).
7. Christian Riuji Lohri, Ephraim Joseph Camenzind, Christian Zurbrügg. (???). "Financial sustainability in municipal solid waste management – Costs and revenues in Bahir Dar, Ethiopia".
8. Cities & Citizens Series. (???). "Urban Inequities Report: Addis Ababa", Addis Ababa, Ethiopia.
9. CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA ADDIS ABABA WATER AND SEWERAGE AUTHORITY, (2011). "AAWSA – Business Plan 2011 – 2020", FINAL REPORT, Addis Ababa.
10. CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA, Housing Construction

Project Office, Bole Bulbula Housing Projects. (2013). "Final Design Report FOR SEWERAGE SYSTEM".

11. Community Development Research. (2011). "Ethiopia Solid Waste & Landfill', Country Profile and Action Plan.

12. Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 55 (1) of the Food, Medicine and Health Care Administration and Control Proclamation No. 661/2009. (2014). "Food, Medicine and Health Care Administration and Control Council of Ministers Regulation No. 299/2013", Federal Negarit Gazeta.

13. EU Water Initiative (November 2006) Financing Strategy for the Water Supply and Sanitation sector, Ethiopia, Executive Report, Final.

14. Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Health. (2010). "Health Sector Development Program IV In line with GTP 2010/11 -2014/15".

15. Federal Democratic Republic Of Ethiopia, MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT and HOUSING (2014). "Ethiopian Cities Prosperity Initiative", Building Green, Resilient and Well Governed Cities, 2013/14-2025, Addis Ababa

16. Federal Democratic Republic of Ethiopia. (2011). "Ethiopia's Climate-Resilient Green Economy", Green economy strategy,

Addis Ababa, Ethiopia.

17. Federal Democratic Republic of Ethiopia (2013), ONE WASH NATIONAL PROGRAM - A Multi-Sectoral SWAp, Program Document, Final August 2013
18. FMOH. (2013) Sanitation and Hygiene Strategic Action plan (SAP) final edited version
19. FMOH. (2009) , Health and Health Related Indicators
20. FMOH. (2013) , Health and Health Related Indicators
21. FMOH. (2013/14),HSDP IV Woreda Based Health Sector Annual Core Plan
22. FMOH. (2014),Mini Demographic Health Statistics (DHS)
23. Gebre G (2009), Urban water pollution and irrigated vegetable farming in Addis Ababa. 34th WEDC International Conference, Addis Ababa, Ethiopia, 2009.
24. MoFED. 2010b. Ethiopia: 2010 MDGs Report: Trends and Prospects for Meeting MDGs by 2015. Addis Ababa, Ethiopia: Ministry of Finance and Economic Development.
25. MoUDH. 2008. Available: http://moud.gov.in/nusppolicy.
26. MOUDH (2014), PPP, Municipal Solid Waste Management Practices and Challenges in Ethiopia
27. MoWIE(2011), National WaSH Inventory (NWI)

28. MoWIE(2011) Universal Access Plan (UAP), parts 2,3 &4

29. MoWIE (2013), One WaSH National Program (OWNP)

30. OWNP. 2014. One WaSH National Program: Program Operational Manual for the Consolidated WaSH Accounts. The Federal Democratic Republic of Ethiopia.

31. PLANET Integrated Water Resources Development PLC. (2013). "DESIGN O F EXTERNAL WATER SUPPLY, WASTEWATER COLLECTION AND DISPOSAL SYSTEM AND STORM WATER DESIGN AT KILINTO SITE", Final Design Report", Addis Ababa.

32. Population Affairs Coordination Sub process Finance and Economic Development Bureau. (2009). "ADDIS ABABA POPULATION IMAGES".

33. The Federal Democratic Republic of Ethiopia. (2014). "Program Operational Manual (POM) for the Consolidated WASH Account's", Final.

34. The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Health. (2008). "Strategic plan for Ethiopia Health Sector", HMIS Reform Team.

35. The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Health. (2010). "Health Sector Development Program IV", 2010/11 – 2014/15, Addis Ababa, Ethiopia.

36. The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Health. (2011). "National Strategic Action Plan for Improved Hygiene and

Sanitation", Final, Ethiopia.

37. The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Industry. (2014). "ESMF for Bole Lemi II and proposed Kilinto Industrial Zones Competitiveness and Job Creation Project", Draft report. Ethiopia.

38. The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Water and Energy. (2011)."Urban Sanitation Universal Access Plan', Part IV, Addis Ababa.

39. The Federal Democratic Republic of Ethiopia. (2011). "National WaSH Implementation Framework", Summary, Ethiopia.

40. The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Water Resources. (2001)."Ethiopia Water Sector Strategy.

41. The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development and Housing. (2014). "Municipal Solid Waste Management Practices and Challenges in Ethiopia".

42. The Federal Negarit Gazeta of the Federal Democratic Republic of Ethiopia. (2002)."Environmental Protection organs Establishment proclamation No. 295/2002", Addis Ababa, Ethiopia.

43. The Federal Negarit Gazeta of the Federal Democratic Republic of Ethiopia. (2002)."Environmental Pollution control Proclamation No. 300/200", Addis Ababa, Ethiopia.

44. The Federal Negarit Gazeta of the Federal Democratic Republic of Ethiopia. (2010)."Food, Medicine and Health Care Administration and Control Proclamation No. 661/2009", Addis Ababa, Ethiopia.

45. UNEP/GRID-Arendal (2002), Water availability in Africa. UNEP/ GRID-Arendal Maps and Graphics Library.

46. UNICEF Ethiopia. (2013). "DFID One WASH PLUS Proposal", 2013-2018.

47. UNICEF. (2013). "The Quarter Million Intiative", DFID One WASH Proposal.

48. United Nations Human Settlements Programme (UN-Habitat). (2014). "STRUCTURAL TRANSFORMATION IN ETHIOPIA: THE URBAN DIMENSION", Building 'Economically Productive, Socially Inclusive, Environmentally Sustainable & Well Governed' Cities, Addis Ababa, Ethiopia.

49. United Nations Human Settlements Programme. (2011). "Gender mainstreaming Impact Study", Water and Sanitation Trust Fund Impact Study Series, Nairobi, Kenya

50. UN-Habitat (2008). "Ethiopia Urban Profile", pp 1-36.

51. UN-Habitat (2005) Situation Analysis of Informal Settlements in Addis Ababa.

52. United Nations Human Settlements Programme. (2014). "STRUCTURAL TRANSFORMATION IN ETHIOPIA: THE URBAN DIMENSION", Building Economically Productive, Socially Inclusive, Environmentally Sustainable & Well Governed, Cities, Nairobi, KENYA

53. United States Agency for International Development/Ethiopia, Catholic Relief Services/Ethiopia. (2003). "GUIDELINES FOR THE DEVELOPMENT OF SMALL-SCALE